# የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት

*የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ*

# የሉቃስ መጽሐፍ

የትምህርቱ አዘጋጅ፡- *ጆን ኤም ፈውለር*
ትርጉም፡- *በወርቅነህ ያዶሬ*

ይህ የጎልማሶች የሰንበት ትምህርት በጀነራል ኮንፈረንስ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት የጎልማሶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቢሮ ሥር እየተዘጋጀ በሰንበት ትምህርት ኅትመት አስተዳደር ንዑስ ኮሚቴ ቦርድ አመራር *(ADCOM)* ለኅትመት ይበቃል፡፡ የኅትመት ውጤቱ ዓለም ዓቀፍ የግምገማ ኮሚቴውን አስተዋፅኦ የሚያንጸባርቅ እና የሰንበት ትምህርት ኅትመት ቦርድ አዎንታን የተቸረ በመሆኑ የትምህርቱን አዘጋጅ/አዘጋጆች ግላዊ አመለካከት አይወክልም፡፡

በኢትዮጵያ አድቬንቲስት ማተሚያ ቤት ታተመ

*2ኛ ሩብ ዓመት*

ከመጋቢት 19 - ሰኔ 19 2007 ዓ.ም





## ማውጫ

| | አርዕስት | ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 1. | የኢየሱስ ምፃት | ከመጋቢት 19-25 2007 ዓ.ም | 5 |
| 2. | ጥምቀቱና ፈተናዎቹ | ከመጋቢት 26-ሚያዝያ 2 | 14 |
| 3. | ኢየሱስ ማን ነው? | ከሚያዝያ 3-9 | 23 |
| 4. | የደቀ-መዝሙርነት ጥሪ | ከሚያዝያ 10-16 | 34 |
| 5. | ክርስቶስ የሰንበት ጌታ | ከሚያዝያ 17-23 | 44 |
| 6. | በኢየሱስ አገልግሎት የሴቶች ሥፍራ | ከሚያዝያ 24-30 | 54 |
| 7. | ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስና ፀሎት | ከግንቦት 1-7 | 64 |
| 8. | የኢየሱስ ተልዕኮ | ከግንቦት 8-14 | 74 |
| 9. | ኢየሱስ ታላቁ መምህር | ከግንቦት 15-21 | 84 |
| 10. | በየዕለቱ ኢየሱስን መከተል | ከግንቦት 22-28 | 93 |
| 11. | የእግዚአብሔር መንግሥት | ከግንቦት 29-ሰኔ 5 | 102 |
| 12. | ኢየሱስ በኢየሩሳሌም | ከሰኔ 6-12 | 112 |
| 13. | የተሰቀለውና የተነሳው | ከሰኔ 13-19 | 122 |

# መግቢያ

አስገራሚ በሆነ መልኩ መልዕክተኛውና ሀኪሙ ለጓደኛው ለቴዎፍሎስ አስደናቂ ውድና እጅግ በተከበሩ ቃላት ባይጽፍለት ኖሮ አንሰማውም ነበር፡፡

የዶክተሩ (የሀኪሙ) ስም ከአህዛብ ወገን ወደ ክርስትና የተመለሰው ሉቃስ ነው፡፡ መልዕክቱም የሉቃስ ወንጌል ነው፡፡ ከወንጌሉ በተጨማሪ ሉቃስ የሐዋሪያትን ሥራ መጽሀፍ ጽፏል፡፡ ለጳውሎስ የጉዞው አገር በመሆኑ በታላቁ የሮማውያንን ግዛት ያጥለቀልቅ በነበረው የክርስቶስ ወንጌል እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊና ልባዊ በሆነ ፍላጎት ነገሮችን የሚከታተል ነበር፡፡ ይህ ከጳውሎስ ጋር የነበረው የቅርብ ወዳጅነት እንደ መለኮት ይታይ ዘንድ የሚፈልገውን የቄሳርን ፍላጎት የሚቃወመውን የቤተክርስቲያንን የከበረ ትርጓሜን እንዲረዳ ብቻ ሳይሆን እጅግ ከከበረ ምንጭ ከቤተክርስቲያን ጀርባ ስላለው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ በጥልቀት እንዲማር ረድቶታል፡፡ ስለዚህ ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት "የክርስቲያን ቤተክርስቲያን ታሪክና መሠረት" ተብሎ የሚጠራውን ሁለት ታላላቅ ጥራዝ መፃህፍት ጽፏል፡፡

የዚህ ሥራ የመጀመሪያ ክፍል የሐዋሪያት ሥራ ከመጻፉ በፊት ለቴዎፍሎስ ተጽፎ ተሠጠው (ሐዋ. 1፡1)፡፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ወንጌል ከ 61 – 63 ዓ.ም እንደተፃፈ ይናገራሉ፡፡

ሉቃስ መልዕክቱን የፃፈው ክርስትናን ለተቀበለው ለግሪካዊው ለቴዎፍሎስ በመሆኑ ትኩረቱ ሁሉ ግሪካውያን ለሆኑ አህዛቦች ቢሆንም የአይሁድ ዝሪያ ያላቸውን የክርስቶስን ወገኖች ወደጎን የተወ አልነበረም፡፡ * ማቴዎስ በቅድሚያ የፃፈው ለአይሁዶች ሲሆን የሱስን መሲህ ብሎ ጽፎአል፡፡ * ማርቆስ የፃፈው ለሮማውያን ሲሆን ክርስቶስ በምድሪቱ አቋርጦ የወንጌልን ዜና በግዛቱ ሲናገር እናያለን፡፡ * ዩሐንስ በጥልቀት አሳቢ ሲሆን ክርስቶስን፤ ቃል፤ ፈጣሪ ፤ የእግዚአብሔር ልጅ በማለት ወንጌሉን ይጀምራል፡፡ ነገር ግን ሉቃስ የፃፈው ትኩረቱን በአህዛብ ላይ በማድረግነው፡፡ ለእነርሱም ክርስቶስን የሰው ልጅ የዓለም አዳኝ እና የሰብዓዊ ዘር ወዳጅ አድርጎ አቀረበላቸው፡፡ ድነት ዓለም አቀፋዊ የሁሉ መሆኑ የዚህ ወንጌል መሪ ሐሳብ ነው፤ ስለዚህ እርሱ የክርስቶስን የዘር አመጣጥ ወደ ኋላ ወስዶ





ከአብረሃም እና ከእግዚአብሔር ጋር ሲያያይዘው ፤ ማቴዎስ ያስቀመጠው የዘር ሐረጉ የአይሁዶች አባት ከሆነው አብርሃም ጋር በማድረስ ያቆማል፡፡ (ሉቃስ 3፡23-38 እና ማቴ. 1፡ 1-17ን ያወዳድሩ)፡፡

የሉቃስ ወንጌል በአዲስ ኪዳን ትልቁ ነው፡፡ አንዳንድ ተዓምራቶች ልጇ እንደሞተባትና የሱስ ልጇን ከሞት ያስነሳት ፤ የነይን ባልቴት ታሪክ (ሉቃስ 7፡ 11-18) እና የሊቀ ካህናቱን ባሪያ ጆሮ መፈወስ (ሉቃስ 22፡ 50-51) ሌሎች ተዓምራቶችን ሉቃስ 5፡4-11 ፤ 13፡11-17 ፤ 14፡1-6 ፤ 17፡11-19 ን ይመልከቱ፡፡ ብዙዎቹ ምሳሌዎች አንዳንድ ታዋቂ የሆኑትን ጨምሮ በሉቃስ ወንጌል ብቻ የሚገኙ ሲሆኑ መልካሙ ሳምራዊ (ሉቃስ 10፡30-37) ፤ ፈሪሳዊውና ቀራጩ (ሉቃስ 18፡10-14)፤ ሐብታሙ ሰነፍ ሰው (ሉቃስ 12፡16-21) ፤ የጠፋው ልጅ (ሉቃስ 15፡11-32) ፤ የሀብታሙ ሰውና የአልአዛር ታሪክ (ሉቃስ 16 ፡19-31) እንዲሁም የዘኪዎስ ታሪክም (ሉቃስ 19፡1-10) የሉቃስ መጽሐፍ ወንጌል አስተዋጽኦ ነው፡፡

በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሉቃስ ታሪካዊ ዕቃዎችን ፈልጎ እንዳገኘና የዓይን ምሥክሮችን ቃለ መጠይቅ እንዳደረገ (ሉቃስ 1፡2) ፤ በተጨማሪም ሁሉንም ነገር በትክክል በመረዳት ለአንባቢያን ክርስቶስንና የእርሱን ወንጌል ዜና እርግጠኝነቱን እንዲያውቁ ነገሮችን በቅደም ተከተላቸው ጽፏል፡፡( ቁጥር3፡4 )

ጀምስ ዳኒ የተባለ ታላቅ የስነ-መለኮት ተመራማሪ ስለ ክርስቶስ ጥሩ የህይወት ታሪክ ሲጠየቅ "ሉቃስ የፃፈውን ሞክራችሁታል" በማለት ነበር መልስ የሰጠው፡፡

ይህ መልካም ሐሳብ ነው፡፡ እስቲ እንደ ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን በዚህ ሩብ ዓመት ይህን ትምህርት አብረን እንማረው፡፡

ጆን ኤም ፋውለር ለ53 ዓመታት የቤተክርስቲያን ቄስ፤ የፍልስፍናና የስነ-መለኮት መምህር ፤ አራሚና የትምህርት አስተዳደር በመሆን አገልግለዋል፡፡ እንደ ብዙ ዓምዶች መጻህፍት ፀሀፊነታቸው ሁለት የጎልማሶች የሰንበት ትምህርት ጥናት ጽፈዋል፡፡ እነርሱም የክርስቶስና የሰይጣን ውጊያ በዓለማት (2002) እና ኤፌሶን የግንኙነት ወንጌል (2005) ፡፡

# 1ኛ ትምህርት

ከመጋቢት 19 - 25 2007 ዓ.ም

# የክርስቶስ ምፃት

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት ጥናት፡-** ሉቃስ 1፡2፡3 ፤ 2ጢሞ. 3፡16 ፤ ሉቃስ 1፡5-22፤ ዘዳግም 18፡15 ፤ ሉቃስ 2፡9-12 እና 22-32 ያንብቡ፡፡

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡-** "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና" *(ሉቃስ 1፡37)፡፡*

የሉቃስ ወንጌል በመጀመሪያ የተጻፈው ለአህዛብ ነበር፡፡ (በቆላ. 4፡10-14) ተጽፎ እንደሚገኘው መልዕክቱ እንደተፃፈለት እንደ ቴዎፍሎስ ሁሉ እርሱም ከአህዛብ ወገን ነበር፡፡

ሉቃስ ከሐኪምነቱ በተጨማሪ ታሪክን በጥልቀት የሚጽፍ ሰው ነበር፡፡ ወንጌሉንም ሲያስተዋውቅ ሉቃስ ኢየሱስን በትክክለኛ የታሪክ አቀማመጥ በእርሱም ዘመን የታሪክ አውድ መሠረት ያቀርበዋል፡፡ ሔሮድስ የይሁዳ ንጉስ ነበር (ሉቃስ 1፡5) አውጉስጦስ ቄሳር በሮማ ግዛት ንጉሥ ነበር (ሉቃስ 2፡1) እና ካህኑ ዘካሪያስም በኢየሩሳሌም ቤተ-መቅደስ በተራው አገልግሎት እየሰጠ ነበር (ሉቃስ 1፡5-9)፡፡ በምዕራፍ 3 ሉቃስ ስድስት ጊዜያት የመጥምቁን ዩሐንስ አገልግሎት የሚያሳዩ ነገሮችን ይጠቅሳል፡፡

ስለዚህ ሉቃስ የክርስቶስን ታሪክ ከጥንት ታሪኮች ሀሳብ የተለየ እንደሆነ በአፃፃፉ ለመለየት ትክክለኛና እውነተኛ የጊዜ ቅደም ተከተልን በመግለጽ አስቀምጦታል፡፡ የእርሱ አንባቢዎችም የሱስ እውነተኛ መሆኑንና "በአዳኙ በኢየሱስ ክርስቶስ" በኩል እግዚአብሔር የአለምን ታሪክ ያዳረሠ መሆኑን በማየት በመደነቅና በአክብሮት ይደመማሉ፡፡





**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለመጋቢት 26 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

**እሁድ** *መጋቢት 20 2007 ዓ.ም*

## የታሪኩ ቅደም ተከተል *(ሉቃስ 1፡1-3 ፤ ሐዋ. 1፡1-3)*

ሐዋ. 1፡1 የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ከመጻፉ በፊት ፀሐፊው "ሌላ መጽሐፍ" መፃፉን ይነግረናል፡፡ ይሁንና ሁለቱም መልዕክቶች ለቴዎፍሎስ የተፃፉ የመሆናቸው እውነታ የሁለቱም መልዕክት ፀሀፊ አንድ ስለመሆኑ ድምዳሜ ላይ እንዲደረስ ያደርጋል፡፡ ሁለቱ መልዕክቶችም "የክርስቲያን ቤተክርስቲያን ታሪክ መነሻ" የመጀመሪያና ሁለተኛ ክፍል እንደሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል "የሉቃስ ወንጌል" የክርስቶስ ህይወትና ተግባርን የሚተርክ ሲሆን ክፍል ሁለት "የሐዋሪያት ሥራ" ስለ ክርስቶስ መልዕክት መስፋፋትና የጥንቷ ቤተክርስቲያን ይነግረናል፡፡

*ወንጌሉ የተፃፈው እንዴት ነበር? ሉቃስ 1፡2-3 እና 2ጢሞ. 3፡16ን ያንብቡ፡፡*

ሉቃስ የኢየሩሳሌምን ከተማ ስላናወጠው ክስተትና ከዚያም በላይ ስለ ኢየሱስ ብዙዎች መጻፋቸውን የተረዳ ሰው ነበር፡፡ የእነዚህ ጽሁፎች ምንጭም የዓይን ምስክሮችንና የቃሉ አገልጋዩችን የሚያጠቃልል ነበር፡፡ (ሉቃስ 1፡2) ይህም በክርስቶስ ዘመን የነበሩንና ደቀ-መዛሙርቶቹን በግልጽ የሚያጣቅስ ሲሆን ሉቃስ ራሱ ከእነዚህ የዓይን ምሥክሮቹና አገልጋዩች ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቷል፡፡ ለምሳሌ ከጳውሎስና ከሌሎች የሐዋሪያት መሪዎች ጋር ተገናኝቷል፡፡ ማቴዎስና ማርቆስ የፃፉትን ወንጌላትንም አግኝቷቸዋል፡፡ ሉቃስ በእርግጥ የክርስቶስ ታሪክ የዓይን ምሥክር አይደለም ነገር ግን እውነተኛና ለማመን በሚያስችል ሁኔታ ወደ ክርስቶስ የተመለሰ ነበረ፡፡

ማቴዎስ የፃፈው ለአይሁድ ምዕመናን በመሆኑ ክርስቶስን ታላቅ መምህር የትንቢት ፈፃሚና የአይሁድ ንጉሥ በማለት አቅርቧል፡፡ ብዙውን ጊዜ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች በክርስቶስ መፈጸማቸውን አገናዝቧል፡፡ ማርቆስ ስለ ኢየሱስ ለሮሜ ሰዎች ሲጽፍ የተግባር ሰው እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ዶክተሩ ሉቃስ ለግሪኮችና ለአህዛብ(አረማውያን) ስለ ኢየሱስ ሲጽፍ የዓለሙ አዳኝ በማለት ገልጾታል፡፡ ሉቃስ የእርሱ መጽሐፍ በሁለት ዓላማ እንደተፃፈ ይነግረናል፤ "ቅደም ተከተሉን የጠበቀ መልዕክት" (ሉቃስ 1፡3) እና የአዲሱን ምዕተ ዓመት

ዘመን ታላቅ ትምህርት በእርግጠኛነት ለማቅረብ ነበር፡፡ የእርሱ ወንጌል ግቡ በክርስቶስ የነበረውን ያንኑ እውነት እርግጠኛ ስለመሆኑ ማሳየት ነው፡፡

በመንፈስ ቅዱስ የተመራው የቅዱስ ቃል ጸሐፊ ሉቃስ በፅሁፉ ውስጥ ሌሎች አስፈላጊ ትኩረት የሚሹ ጉዳዩችን ተጠቅሟል፡፡ ይህ በጣም ደስ የሚያሰኝ ሲሆን በግልጽ እንደሚታየው እነዚያን ሌሎች ምንጮችን መጠቀሙ ከመንፈስ ምሪቱ ጋር ምንም ተቃራኒነት አያሳዩም፡፡ ይህ ለእኛ እንደሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን በመንፈስ የተመሩ ፀሐፊያን ላይ ስለሚነሳው ጥያቄ ምን ትምህርት ይሠጠናል፡፡

## ሰኞ *መጋቢት 21 2007 ዓ.ም*

# "ስሙን ዩሐንስ በለው"

ከነቢዩ ሚልክያስ በኋላ 400 ለሚሆኑ ዓመታት ለእሥራኤል የእግዚአብሔር ዝምታ የታሪካቸው መገለጫ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህም የመጥምቁ ዩሐንስንና የክርስቶስን መወለድ በማብሰር ዝምታው የተሠበረ ይመስላል፡፡

የመጥምቁ ዩሐንስና የኢየሱስ ትውልድ ታሪካቸው ተመሳሳይነት አለው፡፡ ሁለቱም ተዓምራዊ ናቸው፤ የዩሐንስ እናት ኤልሳቤጥ ልጅ የመውለድ ጊዜዋ አልፎ ነበር፤ የክርስቶስን ደግሞ ስናይ ድንግል ልጅ ልትወልድ ነው፡፡ የሁለቱንም የመወለድ ተስፋ ያበሰረው መልአኩ ገብርኤል ነበር፡፡ ሁለቱም የመወለድ ተስፋዎች በመደነቅ መንፈስ በደስታና ፍቃድን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመስጠት ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡ ሁለቱም ህፃናት የሚያድጉና በመንፈስም ጠንካራ እንደሚሆኑም ተናገረ፡፡ (ሉቃስ 1፡80 ፤ 2፡40)

ነገር ግን የሁለቱ ተዓምራዊ ህፃናት ተልዕኮና አገልግሎታቸው የተለያየ ነበር፡፡ ዩሐንስ ለኢየሱስ መንገድ የሚጠርግ ወይም የሚያዘጋጅ ነበር፡፡ (ሉቃስ 1፡13-17) የሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ (ቁ. 35) እናም የመሲሁ ትንቢት መፈጸሚያ ነው፡፡ (ቁ.31-33)፡፡

*ሉቃስ 1፡5-22 ን ያንብቡ፡፡ ምንም እንኳን ዘካሪያስ "እድፈት የሌለበት" እንደሆነ ቢናገርም መልኣኩ የነገረውን መልዕክት አለማመኑ ተግሳፅ አምጥቶበታል፡፡ ታዲያ "እድፈት የሌለበት" የሚለው ሐሳብ ለአማኝ ምን ማለት እንደሆነ ለማስተዋል ይህ እንዴት ይረዳናል?*





ልክ እንደ አብርሃም ልጅ መውለድ፣ የዘካሪያስም ልጅ መውለድ፣ እንዲሁም የማሪያም ልጅ መውለድ እኛ ለመማር የዘገየንበትን ታላቅ እውነትና ሁሌ የምንረሳውን ታላቅ መንፈሳዊ እውነት ለማስተማር ነው፡፡ እኛ በራሳችን ማንኛውንም መልካም ነገር ለማድረግ አንችልም ፤ ሆኖም ለኛ የማይቻለው በእግዚአብሔር ኃይል ራሱን ለሚሠጥና ለሚያምን ተስተካክሎ ይቀርብለታል፡፡ የተስፋው ልጅ የተሠጠው በእምነት ነበር፡፡ መንፈሳዊ ህይወት ለእግዚአብሔር በመንፈስ የተሠጠ የሚሆነውና እኛም የፅድቅን ሥራ ለመሥራት የምንችለው በእምነት ነው፡፡ *Ellen G.White, The desire of Ages, p.98.*

እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ለነበረው ጉዳይ የዩሐንስ ተዓምራት ወሳኝ የሆነ ዓላማ ነበረው፡፡ አራት መቶዎቹ ነቢያት ያልነበሩባቸው የእሥራኤል ታሪክ ዓመታትን ዩሐንስ ወሳኝ በሆነ መልዕክትና ኃይል ሰብሮ ገባ፡፡የዩሐንስ ተልዕኮና መልዕክት የነበረው "ህዝቡን ለጌታ የተዘጋጀ ማድረግ ነበር" (ሉቃስ 1፡17) እርሱ ለኢየሱስ ተልዕኮ መንገድ ለማዘጋጀት ከመሲሁ ፊት የሚሄድ ነበር፡፡

## ማክሰኞ *መጋቢት 22 2007 ዓ.ም*

# "ስሙን ኢየሱስ ትይዋለሽ"

የክርስቶስ አወላለድ በተለመደ ሁኔታ አልነበረም፡፡ እርሱም በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ የጊዜ ሠሌዳ የተዘጋጀ ነበር፤ የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ልጁን ላከ (ገላ. 4፡4) ፡፡ ይህም መጀመሪያ ኃጢአት ወደ ዓለም በገባ ጊዜ እግዚአብሔር የገባው ቃል ኪዳን ፍጻሜ ነው፡፡ (ዘፍ. 3፡15)

*የሚከተሉትን ጥንድ ጥንድ ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ በእያንዳንዱ ውስጥ የኢየሱስ መወለድ የትንቢት አሥገራሚ ፍፃሜ የሚሆነው እንዴት ነው? ይህ እኛ የእግዚአብሔርን ተስፋዎች በሙሉ ማመን እንደሚገባን ምን ያስተምረናል? ዘዳ. 18፡15 ፤ ሐዋ. 3፡22-24፤ ኢሳ. 7፡14 ፤ ማቴ. 1፡22-23 ፤ ሚክ. 5፡2 ፤ ሉቃስ 2፡ 4-7*

__________________________________________________________

__________________________________________________________

የዩሐንስን መወለድ ለዘካሪያስ ከተናገረ ከስድስት ወር በኋላ መልአኩ ገብርኤል ደግሞ ከዚያ የሚበልጠውን ተዓምር ድንግል እንደምትጸንስ ለናዝሬቷ ማሪያም ነገራት፡፡ ድንግልም ወንድ ልጅ ትወልዳለች ስሙም ኢየሱስ ይባላል፡፡ (ሉቃስ 1፡31)

ኢየሱስ ከድንግል መወለዱ ከተፈጥሮ ሁሉና ተፈጥሮአዊ ከሆነ ፍልስፍና ሁሉ ጋር የሚቃረን በመሆኑ መግለጫ መስጠት አይቻልም፡፡ ማሪያም ራሷ እንኳን ጥያቄ ነበራት፡፡ "ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል" (ቁ. 34) መልአኩም ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን አረጋገጠላት (ቁ. 35) እናም ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም"፡፡ (ቁ. 37) ማሪያምም በፍጥነት በእምነት መቀበሏ የሚያስደንቅ ነበር፡፡ "ለባሪያህ እንደቃልህ ይሁንልኝ"፡፡ (ቁ. 38) የእያንዳንዱ ሰው ጥያቄ ተፈጥሮዓዊና ሚዛናዊ ሆኖ ለእግዚአብሔር ምላሽ ደግሞ ሥፍራ መስጠትና መገዛት ያስፈልጋል፡፡

ፍጥረት ሆነ መስቀል፤ የክርስቶስ ሥጋ መልበስ ሆነ ትንሳኤ፤ መናን ከሰማይ ማውረድ ሆነ መንፈስ ቅዱስን ማፍሰስ በእነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍላጎት የሰዎችን አቀባበልና ራስን ለእርሱ ፈቃድ ማስገዛትን የሚጠይቅ ነው፡፡

ማሪያም ለእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ዓላማና ታላቅነት ራሷን በማስገዛት የራሷን ጥያቄ ስትመልስ ቅዱስ ገብርኤል ደግሞ በሌላ ቃላት ማረጋገጫ መልስ ሰጣት፡፡ "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑል ኃይልም ይፀልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል"፡፡ (ቁ. 35)

*አንዳንድ አለማዊ ባህሎች እያንዳንዱ ነገር ተፈጥሮአዊና ሳይንሳዊ ገለጻ አለው የሚለው እምነት አሸንፏቸዋል፡፡ እንዲህ ዓይነት ጥራዝ ነጠቅና ጠባብ አመለካከት ለነገሮች እውነተኛ ሁኔታቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚታሰበው ለምንድን ነው?*

**ራቡዕ** መጋቢት 23 2007 ዓ.ም

# የቤተ-ልሔሙ በረት

ሉቃስ የቤተ-ልሔምን በረት ታሪክ የሚጀምረው በታሪክ ዝርዝር ነው፡፡ ዩሴፍና ማሪያም ከናዝሬት ወጥተው ቄሳር ባወጣው የህዝብ ቆጠራ አዋጅ መሠረት ወደ ቤተልሔም የሄዱት ቄሬኔዎስ የሶሪያ አገረ ገዥ በነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የታሪክ ዝርዝር የመጽሐፍ





ቅዱስ ተማሪዎች ሉቃስ የኢየሱስን ሥጋ መልበስ በዝርዝር ለመዘገብ ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ያስረከበ በመሆኑ ሊደነቅ ይገባል፡፡

*እስቲ በሉቃስ 2፡7 በታየው መሠረት ስለ ኢየሱስ ድህነት ተወያዩ፡፡ "የመጠቅለያ ልብሱን" ፤ "የበረቱን" ፤ እና "በእንግዶች ማረፊያ ሥፍራ አለመገኘቱን" ፤ እነዚህን ነገሮች ጳውሎስ በፊል. 2፡5-8 ክርስቶስ ራሱን ዝቅ ስለ ማድረጉ ከሚናገረው ጋር አወዳድሩ፡፡ ኢየሱስ በእኛ ፋንታ የተራመደው ምን ዓይነት መንገድ ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

የሰማዩ ጌታ ራሱን በሥጋ ለመግለጥ ያለፈበት አሳዛኝ የታሪክ ፍሰት የሚቀጥለው የመጀመሪያዎቹ የበረቱ ጎብኚ በሆኑ እረኞች ነበር፡፡ "ታላቁ የምሥራች ዜና" ሉቃስ 2፡10 የመጣው ሀብታምና ሃይለኛ ወደ ሆኑት ፤ወደ ፈሪሳውያንና ወደ ፀሐፊዎች ፤ ሀገሩን በሙሉ ያጥለቀለቀ ታላቅ ኃይል ወዳላቸው ገዥዎች ሳይሆን ራሳቸውን ዝቅ ወዳደረጉትና ወደ ተናቁት ነበር፡፡

የመልዕክቱን ታላቅነትና ቀለል ብሎ መቅረቡን አስተውሉ፤አዳኝ ተወልዶላችኋል፡፡ በዳዊት ከተማ እርሱም የተቀባው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱም በመጠቅለያ ተጠቅልሎ ታገኙታላችሁ የሰማይ እጅግ ውዱ ሥጦታ እንዲህ በመሰለ ቀለል ባለ ሁኔታ ቀርቧል፡፡ነገር ግን ይህ ስጦታ "ለእግዚአብሔር ክብርን ያመጣል"፤ "በምድር ሰላምን" እናም "ለሰዎች በጎ ፈቃድን" (ቁ. 4)

ሉቃስ ስለ መልአኩ የዘገበው (ሉቃስ 2፡ 9-12) በስነ-መለኮት ትምህርት ሦስት ዋና ዋና ጉዳዩችን ያመጣል፡፡ የመጀመሪያው የወንጌል መልካም ዜና ለሰዎች ሁሉ፣ በኢየሱስ አይሁድና አህዛብ ሁሉ አንድ የእግዚአብሔር ህዝብ ሆነዋል፡፡ ሁለተኛ ከክርስቶስ በቀር ሌላ አዳኝ የለም፡፡ ሦስተኛ የሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው፡፡ እነዚህ ሦስቱ ዋና ሐሳቦች በሉቃስ ወንጌል በቅድሚያ ተገልፀዋል ይህም በኋላ ለሐዋሪያት በተለይም ለጳውሎስ ስብከት መሠረት ሆኗል፡፡

*እንደ ክርስቲያን የምናምነውን አስቡ፤ የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ (ዮሐ. 1፡1-3) እንደ ሰብዓዊ ፍጡር በመሆን ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ የኖረውን አስቸጋሪ ህይወት ያም በመስቀል ፍጻሜ*

*ያገኘን ህይወት ኖሯል፡፡ ይህን በትክክል የምናምን ከሆነ የህይወታችን ሁሉ አቅጣጫ ለዚህ እውነት በመገዛት መሆን ያለበት ለምንድን ነው? የትኛው የህይወትዎ ክፍል ነው የክርስቶስን ታሪክ የሚያንፀባርቀው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

### ሐሙስ *መጋቢት 24 2007 ዓ.ም*

# የክርስቶስ ምሥክር

ምንም እንኳን መልዕክቱ በቅድሚያ የተፃፈው ለአህዛብ ቢሆንም የአይሁዶችን የብሉይ ኪዳን ቅርስ አስፈላጊነት የተረዳ ነበር፡፡ የአዲስ ኪዳንን ታሪክ ከብሉይ ኪዳን ጋር በጥንቃቄ በማገናኘት ማሪያምና ዩሴፍ ህፃኑን ኢየሱስን እንደ አይሁዳዊያን ህግ በስምንተኛ ቀን ማስገረዛቸውና ወደ ቤተ-መቅደስ መውሰዳቸው ደስ በሚል ሁኔታ ተተርኳል፡፡ (ሉቃስ 2፡ 22-24)

ሉቃስ 2፡25-32ን ያንብቡ፡፡ ስምዖን ለእይታ የሚያቀርባቸውን ሦስቱን የመዳን ስነ-መለኮታዊ ነጥቦችን ልብ ይበሉ፡፡ መዳን በኢየሱስ በኩል ብቻ ነው ፤ መዳን የተዘጋጀው በእግዚአብሔር ነው ፤ መዳን ለሁሉም ህዝብ ነው ለአረማውያን እንዲሁም ለእስራኤል፡፡ ይህ ከራዕይ 14፡6-7 የመጀመሪያው መልአክ መልዕክት ጋር እንዴት ነው የሚገናኘው?

የስምዖን ትንቢት የክርስቶስን አገልግሎት ሁለት በጣም ጠቃሚ ባህሪያትን ተንብዮዋል፡፡ የመጀመሪያው ኢየሱስ በእሥራኤል ላሉ ለብዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሳታቸው ምልክት እንዲሆን ተሾሞአል፡፡ ሉቃስ 2፡34 አዎን ክርስቶስ ብርሃንና መዳንን ለሰው ሁሉ ያመጣ ቢሆንም ነገር ግን ከተቀባዩ ምንም ዋጋ አይጠይቅም ማለት አይደለም፡፡

በክርስቶስ ዘንድ እርሱን መቀበል ወይም መቃወም እንጂ በመሐል ምንም ሥፍራ የለም ፤ መዳንም የሚወሰነው በምርጫው ትክክለኛነት ላይ ነው፡፡ ክርስቶስ ሚናችንን እንድንለይ ይፈልጋል፡፡ በእርሱ መጽናት ወይም መተው፣ በእርሱ የሚፀኑት ይነሱና የመንግሥቱ ክፍል ይሆናሉ፤ እርሱን የሚቃወሙ ወይም ከእርሱ እንደተለዩ የሚቀሩ በምድር ወድቀው ያለ ተስፋ ይቀራሉ፡፡ በክርስቶስ ያለን እምነት ለድርድር የሚቀርብ አይደለም፡፡





ሁለተኛው የስምኦን ትንቢት "በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፉል"፡፡ (ሉቃስ 2፡35) ያለ ጥርጥር ይህ የሚያመለክተው ማሪያም የምትመሰክረውን የመስቀሉን ሥቃይ ነው፡፡ ማሪያምም ሆነች ሌሎች ተከታይ ትውልዶች መዳን ያለ መስቀሉ ሊሆን እንደማይችል ያስታውሳሉ፡፡ መስቀል ሌሎቹ የመዳን ዕቅዶች ሁሉ የሚሽከረከሩበት ማዕከል ሆኖ ይቀጥላል፡፡

*መዳን ሥጦታ በመሆኑ እርሱን ለማግኘት ማንም እንዲሠራ አይጠበቅበትም፡፡ ሆኖም የራሳቸው ማድረግ ለሚፈልጉ አሁንም ውድ ዋጋ ይጠይቃል፡፡ ምንም እንኳን መዳን እርካሽ ቢሆንም፤ ክርስቶስን መከተል የሚያስከፍለው ዋጋ ምንድነው ? ይህ የሚሆነውስ ለምንድን ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

### አርብ *መጋቢት 25 2007 ዓ.ም*

**ለተጨማሪ ጥናት፡-** ሉቃስ የወንጌሉ ፀሐፊ በህክምና የሚያገለግል (ሐኪም) ነበር፡፡ በቆለስያስ 4፡14 የተወደደው ሐኪም ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ የእርሱን የህክምና ባለሙያ መሆን ሲሰማ እግዚአብሔር የተለየ ተግባርና ኃላፊነት እንደሠጠው አመነ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከቦታ ቦታ በሚያደርገው ጉዞ አብሮት እንዲሆን በማድረግ አብሮነቱን አጠበቀው፡፡ ከጊዜ በኋላ ጳውሎስ ሉቃስን በመቄዶንያ ተወው፡፡ በዚህም ሥፍራ ሉቃስ በህክምናውና በወንጌል ሰባኪነቱ የተወሰኑ ዓመታትን ኖረ፡፡

በህክምና ሥራው የታመሙትን እያገለገለ የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል በተጨነቁት ላይ እንዲሆን ይፀልይ ነበር፡፡ ስለዚህም የወንጌል በር ክፍት ነበር፡፡ የሉቃስ ህክምና ስኬት በአህዛብ ዘንድ ክርስቶስን ለመስበክ መልካም ዕድሎችን እንዲያገኝ ረድቶታል፡፡ የክርስቶስ ደቀ-መዛሙርት እንዲሠሩ እኛም እንደንሠራ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው፡፡ *Ellen G. White, The Ministry of Healing ; p-140,141*

## የውይይት ጥያቄዎች፡-

❶ *ሉቃስ ወንጌሉን ሲጽፍ ቀድሞ የነበሩትን ጽሁፎች በግንዛቤ ውስጥ ካስገባ እኛ የቅዱሳን መጻህፍትን መገለጥ እንዴት እንረዳለን? (2ጢሞ 3፡26) መገለጥ (inspiration of the prophetic writers) የሚሰራው እንዴት ነው? የትንቢት ጸሐፊዎች መገለጥ የሚለውን መጽሐፍ ያንብቡ፡፡ Select message book; p 15-23*

❷ *የድንግል መውለድ በሚስጢር፣ በታላቅነት እና በተልዕኮ የተገለፀ የእግዚአብሔር አሠራር ነው፡፡ ደግሞም በእውነት ከሰው ማስተዋል በላይ ነው፡፡ ነገር ግን ጥያቄው "ስለዚህ ምን" በተመሳሳይ ሁኔታ ስንት መንፈሳዊ ያልሆኑ ነገሮች ናቸው ከሰው ማስተዋል በላይ የሆኑት እግዚአብሔር እስካለ እርሱም ዓለማትን የመፍጠርና የማኖር ኃይል እስካለው ለምንድን ነው እንደ ማሪያም ልጅ መውለድ የመሳሰሉ ነገሮች ለሰው ከማስተዋል በላይ የሚሆኑት? በዓለም ነገሮች ላይ ያላቸው ማስተዋል በተፈጥሮ ህግ ላይ ብቻ የሆኑ ሰዎች የድንግልን መውለድ ሊቀበሉት አይችሉም፡፡ ነገር ግን በተቃራኒው የዓለምንና የተፈጥሮን ህግ ከተፈጥሮ በላይ ከሆነው ኃይል ጋር በአንድነት የሚቀበሉ ብቻ ይህን ለመቀበል እምቢ አይሉም፡፡ በመጨረሻ መልአኩ ለማሪያም ያለውን እንይ "ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም" (ሉቃስ 1፡37)*

❸ *አንድ የአሜሪካ ቴሌቪዥን ቃለ መጠይቅ አቅራቢ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ዕድሉን ቢያገኝ ሊያነጋግረው የሚፈልገው ሰው ክርስቶስ እንደሆነና ሊጠይቀውም የሚፈልገው ብቸኛ ጥያቄ አንተ በእውነት የድንግል ልጅ ነህ? ያ ጥያቄ ለምን አስፈለገ? የጥያቄው መልስ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?*





# 2ኛ ትምህርት ከመጋቢት 26-ሚያዝያ 2 2007 ዓ ም

# ጥምቀቱና ፈተናዎቹ

### ሰንበት ከሰዓት

**ለዚህ ሳምንት፡-** ሉቃስ 3 1-14 ፤ ሮሜ 6፡1-6 ሉቃስ 3፡21፣22፤ ሉቃስ 4፡5-8 ፤ ኢሳ. 14፡13-14፤ ሉቃስ 4፡9-13 ን ያንብቡ፡፡

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡-** "መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ በአንተም ደስ ይለኛል" *(ሉቃስ 3፡22)*

ባለፈው ሳምንት እንዳየነው ሉቃስ ያቀረባቸው ታላቅ ታሪካዊና ታዋቂ የሆኑ የሁለቱ ሰዎች የኢየሱስና የዩሐንስ የታሪክ አፃፃፍ የታሪካቸውን እውነተኛነት እንድንቀበልና እንድንረዳ አድርጎናል፡፡

ነገር ግን እነዚህን ኃይለኛና ታላቅ ተፅዕኖ ያላቸውን ሰዎች ለመጥቀስ ሌላ አስፈላጊ ምክንያት አለ፡፡ ይህም እነርሱን (ሃይለኞቹን ሰዎች) ከምድረ-በዳው ራሱን ዝቅ ካደረገው ትሁት ሰው መጥምቁ ዩሐንስ ጋር ለማነፃፀር ነው መጥምቁ ዩሐንስ በሰው ልጆች ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ ከታዩ ክስተቶች ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ለሆነው ክስተት መንገድ ጠራጊ፤ ነበረ ይህም ታላቅ ክስተት ዓለሙን የሚዋጀው የኢየሱስ ወደዚህ ምድር መምጣት ነበረ፡፡ እግዚአብሔር ይህን የመሲሁን መምጣት ለማወጅ የዚህን ዓለም ታላላቅ ሰዎች ሳይሆን በጣም ዝቅ ያለውን መምረጡ እንዴት አስደናቂ ነው፡፡

በእውቀት የበለፀጉ ሰዎች እነዚህን ባለ ታሪኮች አንድ ላይ (ዩሐንስ መጥምቁና ኢየሱስ) የአገልግሎታቸውን ጅምር 27 ወይም 28 ዓ.ም እንደሆነ ያስቀምጣሉ፡፡ ይህም በሮማ ግዛት ታሪካዊ ጊዜ ውስጥ ክርስቶስ እንደተጠመቀና ሰማያዊ የሆነን ማረጋገጫ ከእግዚአብሔር እንዳገኘ ይነግረናል፡፡ "የምወድህ ልጄ" (ሉቃስ 3፡22) ሉቃስ ይህንን እውነታ ቅደም ተከተል ያለውን የክርስቶስን ተልዕኮና አገልግሎት ከማቅረቡ አስቀድሞ በፊት ገጹ ላይ አቅርቦት እናገኘዋለን፡፡

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለሚያዚያ 3 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

## እሁድ  *መጋቢት 27 2007 ዓ.ም*

# የጌታን መንገድ አዘጋጁ

*መጥምቁ ዩሐንስ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ልዩ በሆነውና በመዳን ታሪክ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ በሆነ ሁኔታ ይታያል፡፡ የዩሐንስን ስብከት በተመለከተ ማንም ምንም ቢል እርሱ ህዝቡን ለማስደሰት ምንም በስኳር የተቀመሙ ቃላትን አልተጠቀመም፡፡*

ሉቃስ 3፡1-4 በቃል ብቻ የሚገለጽ አስተሳሰብ አይደለም፡፡ እርሱ የአኗኗር ሁኔታ ነው፡፡ ቃሉም *(Metanoia)* የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም **የአእምሮ ለውጥ** ፤ ይህም ለውጥ ደግሞ ወደ አዲስ ህይወት የሚመራ ማለት ነው፡፡

“ማጥመቅ” ማለት በጥልቁ ውኃ ሙሉ በሙሉ ማጥለም ማለት ነው፡፡ ማጥለም በጣም ጥልቅ ትርጓሜ ያለው ነው፡፡ ከዩሐንስ ጊዜ በፊትም አይሁዳውያን የጥምቀትን ትርጉም በጥልቅ ከመጥለም ጋር አያይዘውታል፡፡ ይህም አረማውያን ወደ አይሁድ እምነት በፍላጎታቸው በሚመለሱበት ጊዜ የሚደረግ የተለመደ ሁኔታ ነበር፡፡

መጥምቁ ዩሐንስ አይሁዳውያንን ለጥምቀት ሲጋብዛቸው አዲስ መርሆ እያስቀመጠ ነበር ፤ ጥምቀት አንድን ያረጀ ኃጢአተኛ ህይወት መተውን በህዝብ ፊት ማወጅና ራስን ለሚመጣው መሲህ ማዘጋጀት ነው፡፡ መጥምቁ ዩሐንስ እያስተዋወቀ ያለው ኃጢአትን በመተው እንደ መሲሁ መንግሥት ዜጎች ተመርቆ አዲስ ህይወትን የሚጀመርበት ምልክት ነው፡፡ መጥምቁ ዩሐንስ እርሱ የሚያጠምቀው በውኃ ብቻ እንደሆነና ከእርሱ በኋላ





የሚመጣው “በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃል” (ሉቃስ 3፡16) በማለት ጨምሮ ያስተምር ነበር፡፡ ስለዚህም አንድ በጣም ወሳኝ የሆነ ነጥብ ተገልጿል፡፡ በጥልቅ ውኃ የመጠመቅ ድርጊት የውስጥ ለውጥ መግለጫ ውጫዊ ምልክት ብቻ ሲሆን ይህም ለውጥ እያደር በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መታተምን የሚያመጣ ነው፡፡

*ሮሜ 6፡1-6 ንያንብቡ፡፡ጳውሎስ ምን መንፈሳዊ መልዕክት ነው ከዚህ ሥፍራ እያወጣ ያለው በጥልቅ ውኃ ጠልሞ መውጣትን ለኃጢአት ከመሞት እና ለፅድቅ ህያው ከመሆን ጋር ሲያነፃፅረው ልብ ይበሉ፡፡ የዚህን አዲስ ህይወት እውነታ በህይወትዎ የተለማመዱት እንዴት ነው? አሁንም ያልተወገደ ምን ይቀራል?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## ሰኞ  *መጋቢት 28 2007 ዓ.ም*

# "የምወድህ ልጄ ነህ"

በሉቃስ 2፡41-50 ማሪያምና ዩሴፍ በኢየሩሳሌም ኢየሱስን የረሱበትን ታዋቂ ታሪክ እናነባለን፡፡ በተለይ በዚህ ታሪክ የሚያስደንቀው ማሪያም የሱስን በገሰፀችው ጊዜ የመለሰው መልስ ነው (ቁ 48) የኢየሱስ መልስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆኑን ማንነት ማረጋገጡ ነበር፡፡ "እርሱም ሰለምን ፈለጋችሁኝ በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንደሚገባኝ አታውቁምን? አላቸው" (ቁ 49) የሚቀጥለው ቁጥር እንደሚነግረን ማሪያምና ዩሴፍ የሱስ የተናገረው ስለምን እንደሆነ አለመረዳታቸውን ያሳየናል፡፡ *ደቀመዛሙርቱ ከእርሱ ጋር ዓመታትን አብረውት ቆይተው በትክክል እርሱ ማን እንደሆነ ምን ለመሥራት እንደመጣ ያልተረዱትን ማሪያምና ዩሴፍም እንዴት ሊያስተውሉት ይችላሉ?*

ለምሳሌ ኢየሱስ ከትንሳኤው በኃላ ከሁለት ደቀ-መዛሙርት ጋር በኤማሁስ መንገድ ይነጋገር ነበር፡፡ ከእነርሱ አንዱ ስለ ኢየሱስ ሲናገር እንዲህ አለ "በእግዚአብሔር እና በህዝቡ ፊት በቃልና በሥራ ብርቱ ነብይ" (ሉቃስ 24፡19) በእርግጥ ኢየሱስ ከነብይ በእጅግ ይበልጥ ነበር፡፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እንኳን እርሱ ማን እንደሆነና ምን ለመሥራት እንደመጣ አላወቁም ነበር፡፡

*ማቴ. 3፡13-17 ፤ ዮሐ. 1፡29-34 እና ሉቃስ 3፡21-22 ን ያንብቡ፡፡* ***የኢየሱስ መጠመቅ አስፈላጊነቱ ለምን ነበር?***

____________________________________________________________

____________________________________________________________

በእርሱ ጥምቀት፤ ሰማይ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መስክሯል፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስ የተጠመቀው ጥምቀት ንስሐን ተከትሎ የመጣ ድርጊት መሆኑን ለማሳየት ሳይሆን ለሌሎች ምሳሌን ለማሳየት ነበር (ማቴ. 3፡14-15)፡፡ የኢየሱስን ጥምቀት በተመለከተ የሚታዩ ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች አሉ፡፡ **1ኛ** የአጥማቂው አዋጅ " እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" (ዮሐ. 1፡29) **2ኛ** ከፊቱ ላለው ተግባር በመንፈስ ቅዱስ መቀባቱ **3ኛ** እግዚአብሔር በእርሱ ደስ የሚሰኝበት ልጁ የሱስ መሆኑን ሰማይ ማወጁ ናቸው፡፡

*እድፈት የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ የዓለማት ፈጣሪ በተራ ሰው መጠመቁ የማዳን ዕቅድ ክፍል መሆኑን ያስቡበት፡፡ ይህ አስደናቂ የሆነ የኢየሱስ ዝቅ የማለት ድርጊት በሚፈጸምበት ጊዜ እኛ ራሳችንን ዝቅ ለማድረግና ለማዋረድ የሚጠቅመን ወይም ዋስትና የሚሆነን እንዴት ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## ማክሰኞ *መጋቢት 29 2007 ዓ.ም*

# "በእንጀራ ብቻ" አይደለም

"ኢየሱስም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ከዮርዳኖስ ተመለሰ በመንፈስም ወደ ምድረ በዳ ተመርቶ አርባ ቀን በዲያቢሎስ ተፈተነ" (ሉቃስ 4፡1-2)፡፡ እግዚአብሔር ለቀባው ተልዕኮ የተወለደ በጥምቀቱም ለሥራው የተወከለ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታጠቀው ጌታ በፊቱ ስለሚጠብቀው ሥራ ለማሰላሰል ወደ ምድረ በዳ ሄደ፡፡





በምድረ በዳ የነበረው ፈተና ሰይጣን በሰማይ ካመጠበት ጊዜ ጀምሮ በክርስቶስና በሰይጣን መካከል የነበረው ታላቁ ተጋድሎ ዋነኛ ክፍል ነው፡፡ በምድረ በዳ አዳኛችን አርባ ቀን ጾሞ ሲደክም ከፊት ለፊቱ ያለው ጉዞ አድካሚና አሰልቺ በመሰለ ጊዜ ሰይጣን በራሱ በመነሳሳት አደጋ ጣለ፡፡ "ሰይጣን ማሸነፍ ወይም መሸነፍ እንዳለበት ወሰነ የግጭቱ ሁኔታ በሥሩ ላሉ መላዕክት ለመተው ከሚችለው በላይ ሆነበት ጦርነቱን ራሱ በአካል ማካሄድ ነበረበት፡፡" *Ellen G.White, The desire of Ages, p.116.*

*ሰይጣን ለክርስቶስ ያለውን ያስተውሉ፤ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ይህንን ድንጋይ ዳቦ እንዲሆን እዘዝ" (ሉቃስ 4፡3) በዚህ ሥፍራ ሰይጣን ለማንጸባረቅ የሞከረው ነገር ምንድን ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

በዚህ ሥፍራ ዳቦ ማዕከላዊ ነገር አይደለም፡፡ አዎን አዳኛችን በምድረ በዳ ለ40ቀን በመጾሙ ተርቦ ይሆናል እና ሰይጣን ይህችን አጋጣሚ ለማታለያ ተጠቅሞባታል፤ ነገር ግን ሰይጣን ኢየሱስ የዓለማት ፈጣሪ መሆኑን ያውቃል፡፡ ዓለማትን ከምንም ለፈጠረ ለእርሱ ድንጋይን ዳቦ ማድረግ ትልቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ የዚህ ፈተና ዋናው ነገር የሚገኘው በመግቢያው ላይ ነው፡፡ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ"፡፡ *እግዚአብሔር ከሰማይ እርሱ ልጁ እንደሆነ ከተናገረ 40 ቀናት ብቻ አልፈውት ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነቱን ይጠራጠራል?* የእግዚአብሔርን ቃል መጠራጠር ወደ ፈተና መግቢያ የመጀመሪያው ደረጃ ነው፡፡ በሰማይ ሰይጣን የክርስቶስን ሥልጣን ተገዳድሯል፤ በዚህም በሰማይ ከሞከረው ይልቅ በረቀቀ መንገድ ተመሳሳዩን አደረገ፡፡

*የእግዚአብሔርን ተስፋዎች እንድንጠራጠር በማድረግ እኛን ሁላችንን ለማግኘት በሚያደርገው ዘዴው እንዳንረታ ከዚህ ምን እንማራለን?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ረቡዕ** መጋቢት 30 2007 ዓ ም

# "ለእኔ ወድቀህ ብትሰግድ"

*ሉቃስ 4፡4-8 ን ያንብቡ፡፡ ሠይጣን ክርስቶስ እንዲሰግድለት የፈለገው ለምንድን ነው? በዚህ ውርርድ ወሳኙ ነገር ምን ሊሆን ይችላል?*

________________________________________________________________

________________________________________________________________

አምልኮና ስግደት የእግዚአብሔር ዋንኛው ሥልጣኑ (መብቱ) ነው፡፡ ይህም ለዘላለም ፈጣሪንና ፍጥረትን የሚለያቸው ነው፡፡ ሉሲፈር በእግዚአብሔር ላይ አመፀ፡፡ ካነሳቸው ጉዳዩች አንዱ አምልኮ ነው፡፡ የሉሲፈር ምኞት በኢሳ. 14፡ 13-14 ጥሩ ተደርጎ ማጠቃለያ ተሠጥቶታል፤ ወደ ሰማይ ከፍ በማለት ዙፋኑን ከሰማይ ከዋክብት በላይ ለማድረግ በልዑልም ለመመሰል ተብሎ ተገልጾአል፡፡ ይህም ምንም ያህል ከፍ ያለ ቢሆንም ለእግዚአብሔር ብቻ የተገባን ሥልጣን ያለ አግባብ ለመውሰድ ያደረገው ሙከራ ነበር፡፡

በዚህ አውድ ስንመለከት በፈተናው እየተከናወነ ያለው ምን እንደሆነ በተሻለ ሁኔታ እንረዳለን፡፡ ጌታችን እየሱስ ዓለምን ዳግም ወደ እግዚአብሔር ባለቤትነትና ሥልጣን የመመለስ ተልዕኮውን ሲጀምር ሰይጣን እርሱን ወደ ተራራ ጫፍ በመውሰድ አስደናቂ የሆነውን የዓለምን መንግሥታት በማሳየት አንድን ቀላል ተግባር ብቻ ቢፈጽም ለእርሱ እንደሚሠጠው ተናገረ፤"ለእኔ ወድቀህ ብትሠግድ ይህ ሁሉ የአንተ ይሆናል" (ሉቃስ 4፡7)፡፡

ሰይጣን በዚህ ሥፍራ የክርስቶስን አመለካከት መለኮታዊ ቅድሚያ ከተሠጠው ነገር ዞር በማድረግ አንድ ጊዜ ብቻ ከመስገድ በማይበልጥ ሁኔታ ክብርን በማሳየት ለማታለል እየሞከረ ነበር፡፡ በዚህ ሥፍራ በሰማይ ያጣውን አምልኮና ሥልጣን ለማግኘት እየሞከረ ነበር፡፡

ክርስቶስ ፈታኙን በቀላል ንቀት ፈተናውን እንዴት እንዳለፈው ያስተውሉ " ከእኔ ራቅ አንተ ሰይጣን ቁ. 8 ፡፡ አምልኮና ከእርሱ ጋር የሚሄድ አገልግሎት ሁሉ የተገባው ለፈጣሪ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ እንደገና የእግዚአብሔር ቃል ረዳው፡፡ ለሙሴ የተሠጠው መገለጥ





"እሥራኤል ሆይ ስማ ፤እግዚአብሔር አምላካችን እርሱ አንድ ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላክህን ውደድ እርሱንም ፍራው እናም እርሱን ብቻ አምልክ" ዘዳ 6፡ 4.5.13)፡፡ በቀጥታ በእምነትና በመታዘዝ እግዚአብሔርን ለመከተል መወሰን ለሠይጣን ማታለያዎችና ውሸቶች ትክክለኛ መልስ ነው፡፡

*ማናችንም ቀላል በሆኑ ነገሮች እንኳን ሳይቀር እምነታችንን እንድናስተባብል ፈተና ይገጥመን ይሆናል፡፡ በሥራዎት፤ ወደ ዩኒቨርስቲ ለመግባት በሚደረገው ትግል፤ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማደግ ሰንበትን ማስተባበል የሚጠይቅ ይሆናል፡፡ በተሻለ አገር የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት ከእምነትዎ በተቃራኒ የስም ለውጥ ማድረግ ያስፈልግ ይሆናል፡፡ በየትኛው ነጥብ ላይ ነው ስምምነት የሚያደርጉት?*

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**ሐሙስ** ሚያዝያ 1 2007 ዓ ም

# አሸናፊው ክርስቶስ

ሉቃስና ማቴዎስ የ2ኛውን እና የሦስተኛውን ፈተና ቦታ ይለዋውጡታል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ግልፅ ባይሆንም የሚያስጨንቀን አይደለም፡፡ ዋነኛው ነገር በሁለቱም ወንጌላት የተጠቀሰው የኢየሱስ ፍጹም አሸናፊነት መታወጁ ነው፡፡ ስለ ክርስቶስ ፈተናዎች በማጥናት የሚገኘው ወሳኝ ጉዳይ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሰው እንደ እኛው የተፈተነ ነገር ግን ያለ ኃጢአት የሆነ መሆኑ ነው (ዕብ. 4፡15)፡፡ እያንዳንዱን ፈተና ድል በመንሳት በሰይጣን ላይ ድልን በመጎናጸፍ በአፉ በሚወጣውም የእግዚአብሔር ቃል ከሰማያዊው የኃይል ምንጭ ጋር በፀሎት በመገናኘት ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በማወጅ የመሲሁን ዘመን አስጀመረ (ከፊተ)፡፡

ሉቃስ 4፡9-13 እና ማቴ. 4፡4-7 ን ያንብቡ፡፡ ክርስቶስ የሰይጣንን ማታለያዎች ለማሸነፍ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ፈተናዎች የእግዚአብሔርን ቃል ተጠቀመ፡፡ አሁን ደግሞ በሦስተኛው ሰይጣን ልክ እንደ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ቃል በመጥቀስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃል ምን ያህል ትኩረት እንደሚሠጥ ለመፈተን ተጠቀመ፡፡ በዚህ ሥፍራ እየሆነ ያለው ምንድን ነው?ክርስቶስ ለዚህ ምን ምላሽ ሰጠ፡፡

ሰይጣን ኢየሱስን በአይሁዶች ታሪክ ውስጥ እጅግ ቅዱስ ወደ ሆነው የኢየሩሳሌም ቤተ-መቅደስ ጫፍ ላይ አወጣው፡፡ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር የሚኖርበት ሥፍራ፤ የፅዮን ከተማ አሁን ሰይጣን ኢየሱስን የሚገዳደርበት ሰፊ ጎዳና ሆነ፡፡ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ" የሚለው እንደገና የንግግሩ መግቢያ ነበር፡፡ ሰይጣን የሚለውን ተመልከቱ በእውነት እግዚአብሔር አባትህ ከሆነ እናም የአንተ ተልዕኮ በእውነት የእርሱ ትዕዛዝ ጥሪ ከሆነ ራስህን ከቤተ-መቅደሱ ራስ ላይ በመወርወር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሞክረው ማለቱ ነበር፡፡ በእርግጥ ይህ ሁሉ እውነት ከሆነ እግዚአብሔር እንድትጎዳ ዝም አይልም፡፡ ከዚያም እንዲህ በማለት ይጠቅሳል"ይጠብቁህ ዘንድ መላዕክቱን ስለ አንተ ያዛል፡፡" (ሉቃስ 4፡10)

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል ያውቃል ነገር ግን በስህተት ይተረጉማል፡፡ ዘዴውም ኢየሱስ እግዚአብሔርን ወደ መፈታተን ሊመራው ነበር፡፡ በእውነት እግዚአብሔር ይጠብቁን ዘንድ መላእክቱን ያዛል ይህም የእርሱን ፈቃድ በማድረግ ላይ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በዳንኤልና በጓደኞቹ ሁኔታ ውስጥ ይህን አድርጓል፡፡ ኢየሱስም ቅዱሳት መፃህፍትን በመጠቀም "እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፏል፡፡" (ቁ. 12) በማለት ቁርጥ ያለ ወሳኝ መልስ ሰጥቶታል፡፡

**በፈተናው ላይ አራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምሮዎችን አጢኑ (አስተውሉ)**

1. ማንም ከፈተና ነፃ አለመሆኑን
2. እግዚአብሔር እንድንፈተን ሲፈቅድ ፈተናውን ለመቋቋምና ለማሸነፍ ጸጋን እንደሚሠጥ
3. ፈተናዎች ሁል ጊዜ በተመሳሳይ መልኩ እንደማይመጡ
4. ማንም ከሚችለው በላይ እንደማይፈተን (1ቆሮ. 10፡13)

## ዓርብ ሚያዝያ 2 2007 ዓ.ም

**<u>ለተጨማሪ ጥናት</u>፡-** "ማሪያምና ዩሴፍ አእምሮአቸውን በፀሎትና ስለ እግዚአብሔር በማሰላሰል አቆይተውት ቢሆን የመታመናቸውን ቅድስና ባስተዋሉት ነበር፣ ክርስቶስም ከፊታቸው ባልጠፋባቸው ነበር፡፡ በአንድ ቀን ቸልተኝነት ያጡትን አዳኝ ለማግኘት ሶስት ቀን አስጨናቂ የሆነ የፍለጋ ጊዜ ፈጀባቸው እኛ ደግሞ በሥራ ፈትነት እና መጥፎ በመናገር ወይም ፀሎትን ችላ በማለት ጌታን በህይወታችን ለአንድ ቀን እናጣው





ይሆናል፤ ይህም እርሱን ለማግኘትና ያጣነውን ደስታ ለመመለስ ብዙ ኃዘን የተሞላባቸው ቀናት ይጠይቀናል፡፡ *Ellen G.White The Desire of Ages. P.83*

## የውይይት ጥያቄዎች፡-

❶ *ፈተና በራሱ ኃጢአት አይደለም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ፈተና ራሱ ቅድስናን የማጠንከር ኃይል አለው፡፡ መፈተን አንድ ነገር ሲሆን በፈተና መውደቅ ሌላ ነገር ነው፡፡ ፈተናን ለማስወገድ የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ የእኛ ኃላፊነት ምንድንነው?*

❷ *ፈላስፎችና የስነ-መለኮት ጠበብት ብዙውን ጊዜ ከሁሉም ጋር ግንኙነት አለው ከሚሉት መሠረታዊ መልዕክት ወይም የሌሎች ታሪኮች መገኛ ቅድመ ታሪክ ነው ብለው ስለሚያስቡት ዋና እውነት ይናገራሉ፡፡ በሌላ አነጋገር ለማስቀመጥ የታሪክ መነሻ የሚሉት የሌሎች ታሪኮች አውድ፤ የኋላ ታሪክ እና የሌሎች ክስተቶች ሁሉ ጅምር ነው፡፡ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬቲስት ታላቁን ተጋድሎ በምድር እየሆነ ላለው ብቻ ሳይሆን በሰማይም ለነበረው ሁሉ መነሻ እንደሆነ እናያለን፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ስለ ታላቁ ተጋድሎ እውነታ በግልጽ የሚነግሩን ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?*

❸ *የሚመጡብንንና የሚገጥሙንን ፈተናዎች እንደምናሸንፋቸው ተስፋ የሚሠጡን አንዳንድ ኃይለኛ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው? ታዲያ ለምንድንነው እነዚህ ተስፋዎች እያሉን እንኳን እስካሁን መውደቅ ቀላል የሚሆነው?*

❹ *ከዚህ ሳምንት ትምህርቶች በአንዱ "የእግዚአብሔርን ቃል መጠራጠር ወደ ፈተና ለመግባት የመጀመሪያ ደረጃ ነው"፡፡ የሚል መልዕክት አለው ይህ የሚሆነው ለምንድን ነው?*

❺ *ጣኦትን ማምለክ ከእግዚአብሔር ውጪ ለሌላ ነገር ጎንበስ ብሎ ከመስገድን እንደ ቀላል የሚታየው በምን ዓይነት መንገዶች ነው?*

# 3ኛ ትምህርት

ሚያዝያ 3-9 2007 ዓ.ም

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው?

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት ጥናት፡-** ሉቃስ 4፡ 16-30 ፤ 6፡5 ፤ ኤፌ. 1፡3-5 ፤ ሉቃስ 9፡18-27 ፤ 2ጴጥሮስ 1፡16-18ን ያጥኑ፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "እናንተስ እኔ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? ጴጥሮስም መልሶ ከእግዚአብሔር የተቀባህ ነህ አለ" *(ሉቃስ 9፡20)*

## *ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው?*

ይህ ጥያቄ ፍልስፍናዊ ወይም ማህበረሰባዊ የሆነ የሰዎችን ፍላጎት ለመቀስቀስ ለመማረክ የሚደረግ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ይህም ሰብዓዊ ወደ ሆኑ ሁሉ ልብ የሚገባ የማንነታቸውና ከዚያም አልፎ ዘለዓለም በውስጡ ስለ እነርሱ ምን እንደያዘ የሚናገር ነው፡፡

ሰዎች የኢየሱስን ሥራዎች ሊያደንቁ ፤ ቃሎቹን ሊያከብሩ ትዕግሥቱን በማሞገስ ሲናገሩ ወሳኝነቱን በጣም ሊያደንቁ ፤ ከራስ ወዳድነት ነፃ በመሆኑ ሊያመሰግኑት ይችላሉ፡፡ እናም ጨካኝ የሆነውን የህይወቱን አፈጻጸም ሲመለከቱም ቃላቶችን በማጣት ዝም ይላሉ፡፡ ምናልባትም ብዙዎች ክርስቶስን ነገሮችን ለማስተካከል ጥረት እንዳደረገ፤ ፍትህ ባልነበረበት ፍትህን ለማምጣት እንደታገለ፤ በሽታ ባለበት ፈውስን ለመስጠት እና መከራ





ባለበት መጽናናትን ለማምጣት እንደሞከረ ሰው ሊያስቡት ይችላሉ፡፡

አዎ ኢየሱስ በመምህርነት ከፍተኛ ለውጥ ያመጣ ፤ ከፍተኛ ችሎታ ያለው መሪ፤ እናም የሰውን ውስጥ በጥልቀት የሚፈትሽ የሥነ-አዕምሮ ጠቢብ የተባሉ ሥሞችን ሊያገኝ ይችላል፡፡ እርሱ የተጠቀሰውን ሁሉና ከዚያም ደግሞ የበለጠ ነው፡፡

ነገር ግን ከእነዚህ ሁሉ ኢየሱስ እራሱ የጠየቀውን ከሁሉ የሚበልጠውን ጥያቄ ለመመለስ የሚችል የለም፡፡ "እኔን ማን ነው ትሉኛላችሁ" (ሉቃስ 9፡20) የሰው ልጅ የሰብዓዊ ዘር ፍጻሜ የተመሰረተበት ዋና ሀሳብ ያለበት በመሆኑ የዚህ ጥያቄ ምላሽ ይፈልጋል፡፡

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለሚያዚያ 10 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

**እሁድ** ሚያዚያ 4 2007 ዓ.ም

## ለኢየሱስ የቀረቡ ምላሾች

ወንጌላትን ያንብቡ፡፡ አዲስ ኪዳንን ያንብቡ፡፡ በእነዚህ መጻህፍት ሁሉ ክርስቶስ ስላደረጋቸው ነገሮች ብቻ ሳይሆን የበለጠ ጠቃሚ የሚሆነው ክርስቶስ ማን እንደነበረም የሚገልጽ ድንቅ የሆኑ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ (በእርግጥ ኢየሱስ በታላቅ ኃይል የፈጸማቸው ነገሮች የእርሱን ማንነት መስክረዋል፡፡) እነዚህ ሁሉ ነገሮች ፤ እርሱ አምላክና አዳኛችን መሆኑ ፤ እርሱ ብቻ የዘላለም ህይወት መንገድ መሆኑ፣ እያንዳንዳቸው የሁሉንም ሰብዓዊ ዘር የፍጻሜ ውጤት የሚወስኑ በመሆናቸው ትኩረትን ይሻሉ፡፡

ሉቃስ 4፡16-30 የተወለደበት ከተማ የነበሩ አድማጮች በመጀመሪያ የሱስን በማየታቸው የደስታ ስሜት ፈጥሮላቸዋል፤ በኋላም ብዙ ታዓምራቶችን ካደረገ በኃላ ወደ ናዝሬት ሲመለስ "እነርሱ ድንቅ ከሆኑት ቃሎቹ የተነሳ ተደነቁ፡፡" (ሉቃስ 4፡22) ነገር ግን ለእርሱ ግሳጼ ያሳዩት ምላሽ እንደሚገልጸው መንፈስ ቅዱስ በእውነት ህይወት ሰጥቶአቸው እንደነበር ነው፡፡

*ሉቃስ 7፡17-22 ያንብቡ፡፡ ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ የጠየቀው ምንድን ነበር? ይህንን ለምን ጠየቀ?*

________________________________________________

________________________________________________

ከክርስቶስ በፊት መንገድ ጠራጊ የነበረው መጥምቁ ዩሐንስ እርሱ "የእግዚአብሔር በግ ነው"" ብሎ ያወጀው እንኳን ሳይቀር በነፍሱ ውስጥ በጥልቀት ጥያቄዎች ይመላለሱበት ነበር፡፡ "ልትመጣ ያለኸው አንተ ነህን ወይስ ሌላ እንጠብቅ? በማለት ለማወቅ ፈለገ (ሉቃስ 7፡19)፡፡

ኢየሱስ የዮሐንስን ጥያቄ በቀጥታ አለመመለሱንም በደንብ ያስተውሉ ፤ በዚህ ፋንታ ምሥክርነታቸውን የሚገልጹ ተግባራትን ጠቀመ፡፡ " ሽባዎች ይዘላሉ ፤ ለምጻሞች ይነፃሉ ፤ ደንቆሮዎች ይሰማሉ ፤ ሙታን ይነሳሉ ፤ ለድሆች ወንጌል ይሰበካል " (ሉቃስ 7፡22) የሱስ ለዩሐንስ ጥያቄ በቀጥታ መልስ መስጠት አያስፈልገውም ፤ የእርሱ ሥራዎችና ድርጊቶቹ ተገቢ የሆነ ምላሽ ይሰጣሉ ብሎ መሚገት ይቻላል፡፡

*ኢየሱስ የመለሰው ምላሽ ዮሐንስን ምናልባትም የበለጠ እንዲሸበር ሊያደርጎት ይሆናል፡፡ ታዲያ ኢየሱስ ይህንን ሁሉ ታላቅ ሥራ እየፈጸመ ከሆነ እኔ ከዚህ እሥር ቤት እንዴት እጨነቃለሁ? በግል የህይወት ሥቃይ ውስጥ እንኳን ያልሆኑ ተመሳሳይ ጥያቄ ይጠይቃሉ ፤ እግዚአብሔር ይህ ሁሉ ኃይል ካለው ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ለምን ይሆናል? መስቀሉና እርሱ የሚወክላቸው ተስፋዎች ብቻ መልሳችን የሚሆኑት ለምንድነው?*

________________________________________________

________________________________________________

## ሰኞ    ሚያዚያ 5 2007 ዓ. ም

# የእግዚአብሔር ልጅ

"የእግዚአብሔር ልጅና የሰው ልጅ" የሚሉ ሁለት ስሞች ክርስቶስ ማን እንደሆነ ለመግለጽ በወንጌላት ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የመጀመሪያው ከሦስቱ ሥላሴዎች ሁለተኛ





የመሆኑንና መለኮታዊነቱን የሚገልፅ ነው፡፡ ሁለተኛው እግዚአብሔር የሰውን ሥጋ መልበሱን የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለቱ ሀረጎች አንድ ላይ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተዓምራቶች እንድናስብ ይጋብዙናል፡፡ ለማስተዋል ከባድ የሆነ ሀሳብ ቢሆንም እንኳን ክብደቱ አስደናቂ ከሆነ እውነት እና ታላቅ ተስፋ እንድንርቅ አያደርገንም፡፡

*ሉቃስ 1፡3 ፤ 32 ፤ 35 ፤ 2፡11 ን ያንብቡ፡፡ ስለ ክርስቶስ ማንነት እውነታ እነዚህ ጥቅሶች ምን ይነግሩናል?*

________________________________________________

________________________________________________

በሉቃስ 1፡31፤ 32 መልአኩ "ኢየሱስ" የሚለውን ሥም "የልዑል ልጅም ይባላል" "ጌታ አምላክም የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል" በማለት ያገናኘዋል፡፡

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ እርሱ ደግሞ እንደ ምድራዊ ነፃ አውጪ ሆኖ ሳይሆን በመጨረሻው ዘመን ስለሚሆነው ነገር በሚያስተምረው ትምህርት መሰረት ሰይጣንን ሙሉ በሙሉ ድል በመንሳት ከጥንት የእግዚአብሔርን ዙፋን ለመፈንቀል የነበረውን የእርሱን ሀሳብ ወዲያ ጥሎ ክርስቶስ መሲህ ይሆናል፡፡ መልአኩም ለእረኞች ሲናገር በበረት ያለው ህፃን " አዳኝ እርሱም ጌታ ክርስቶስ ነው" (ሉቃስ 2፡21) በማለት አውጇል፡፡

"የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው ስም ፤ በሥላሴዎች ያለውን ሥፍራ የሚመሰክር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ከአባቱ ጋር የነበረውን ጥብቅ ግንኙነት ጭምር የሚያሳይ ነበር፡፡

ሆኖም በአባትና በልጅ መካከል የነበረው ግንኙነት እኛና እግዚአብሔር ካለን ግንኙነት ጋር ተመሳሳይ አይደለም፡፡ እኛ ያለን ግንኙነት ከኢየሱስ ፈጣሪነትና አዳኝነት የመነጨ ሲሆን የእርሱ ግንኙነት ግን የሦስቱ ዘለዓለማዊ አብረው የነበሩ አካላት ግንኙነት ነው፡፡ ኢየሱስ በመለኮታዊነቱ እጅግ ቅርብ የሆነውን ከአባቱ ጋር ያለውን ግንኙነት አፅንቶ ያዘው፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በሰብዓዊነቱ በምድር ከእርሱ ደቀ-መዛሙርት ጋር አብሮ በነበረ ጊዜ የመከራቸው ተካፋይ ፤ እና በስቃያቸው ለእነርሱ የሚሰማው ሁሉ እንደ ራሱ በሚሰማው ጊዜ ኢየሱስ በሰማይ ካለው አባቱ ጋር በመለኮታዊነቱ ከሰማይ ዙፋን ጋር ፍፁም የተገናኘ

መሆኑን ተናግሯል፡፡ *Ellen G. White, The desire of Ages P.442*

ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ አምላክ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? ምንም እንኳን ይህ እውነት በብዙ ትርጓሜዎች የተሞላ ቢሆንም ከሁሉ የሚያስደንቀው ኢየሱስ አምላክ ቢሆንም ሰብዓዊነታችንን ለመውሰድ (ለመልበስ) ራሱን ማዋረድ ብቻ ሳይሆን በሰብዓዊነቱ ራሱን ስለ እኛ መስዋዕት ማድረጉ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ እየተነጋገርን ያለው ስለ እግዚአብሔር ነው፡፡ *እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የሚያሳየን በዚህ እውነት ውስጥ ምን አሰደናቂ ተስፋ እናገኛለን?*

__________________________________________________________

__________________________________________________________

## ማክሰኞ ሚያዝያ 6 2007 ዓ ም

# የሰው ልጅ

ምንም እንኳን ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔርም የሰውም ልጅ መሆኑን በትክክል የሚያውቅ ቢሆንም (ሉቃስ 22፡ 67-70) እርሱ ራሱን የሰየመው "የሰው ልጅ" በማለት ነበር፡፡ በዚህ ስም ሌላ ማንም ጠርቶት አያውቅም በሌላ ሥፍራ ይህ ስም የሚገኘው በእስጢፋኖስ ንግግር ውስጥ (ሐዋ. 7፡56) እና (ራዕይ 1፡3 ፤ 14፡14) ብቻ ነው፡፡ ይህም ቃል 80 ጊዜ በወንጌላት ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን በሉቃስ 25 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ የመጽሐፉ ፀሐፊ ሉቃስ በዚህ ቃል አጠቃቀሙ በኢየሱስ ሰብዓዊነት ፤ መልካም የድነት የምሥራች ዜና ለዓለም እንዲያውጅ የተላከ ታዋቂ ሰው በመሆኑ ላይ ትልቅ ትኩረት መስጠቱን ያስታውቃል፡፡

"የእግዚአብሔር ልጅ ሰብዓዊነት ለእኛ ሁለመናችን ነው፡፡ ይህ እኛን ከኢየሱስና በኢየሱስ በኩል ከአብ ጋር የሚያስተሳስረን ወርቃማ ሰንሰለት ነው፡፡ ይህ ጥናታችን ሊሆን ይገባል፡፡ ክርስቶስ እውነተኛ ሰው መሆኑን ሰብአዊ ፍጡር በመሆን አረጋግጧል፡፡ ሆኖም እርሱ በሥጋ የነበረ አምላክ ነበር፡፡" *Ellen G. White, Selected Message, Book 1, p.244.*





በሉቃስ መጽሐፉ "የሰው ልጅ" የሚለው አጠራሩ በክርስቶስ ተፈጥሮ ፤ በተልዕኮው እና በፍጻሜው ላይ ብዙ ተጨማሪ ነገር እንድንረዳ ያደርገናል፡፡

**የመጀመሪያው** ይህ መጠሪያ እርሱ ሰብዓዊ ሰው መሆኑንና በዓለም ላይ የተለየ አድራሻና ልዩ ጥበቃ የሌለው መሆኑን ይገልጻል፡፡ (ሉቃስ 7፡34 ፤ ሉቃ 9፡58)

**ሁለተኛ** ሉቃስ ይህንን መጠሪያ የክርስቶስን መለኮታዊ ባህሪይ ለመግለጽ "የሰው ልጅ ደግሞ የሰንበት ጌታ ነው፡፡" በማለት ጽፏል፡፡ (ሉቃስ 6፡5)፡፡ ስለዚህ እርሱ ኃጢአትን ይቅር ለማለት የሚችል ኃይል ያለው ፈጣሪም ነው፡፡(ሉቃስ 5፡24)

**ሦስተኛ** ይህን የድነት ተልዕኮ ለማከናወን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በመለኮት በስላሴዎች የተቀባ ነው (ኤፌ. 1፡ 3-5) የሰው ልጅ የጠፉትን ለማዳን መጥቷል (ሉቃስ 9፡56፤ 19፡10)፡፡ "ነገር ግን የሰው ልጅ መከራ ሳይቀበል ፤ በሰዎች ሳይጠላ፤ ሳይገደል ፤ በሶስተኛ ቀንም ከሞት ሳይነሳ ድነት አልተፈጸመም ነበር፡፡ (ሉቃስ 9፡22) የሰው ልጅ በመከራ ስለሚያልፍበት መንገድ ስለ ለሰብዓዊ ዘር ኃጢአት መክፈል ስላለበት ዋጋ ማወቁ የድነት እቅድን መለኮታዊ መሠረት ያለው መሆኑን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በዚያ እቅድ ውስጥ የክርስቶስን በፈቃድ ራሱን በሰብዓዊነቱ መስጠቱን ጭምር ነው፡፡

**አራተኛ** ሉቃስ መከራ ስለተቀበለው መሲህ ያስቀመጠውን ሙሉ የሆነ መግለጫ እንዴት እንደሆነ በሚቀጥሉት ንባቦች ውስጥ አጢኑ ፤ ስለ መስቀሉ ቀድሞውኑ የነበረው ዕውቀት (ሉቃስ 18፡31-33) አሳልፈው እንደሚሠጡት (ሉቃስ 9፡44) ሞቱ የትንቢት ፍጻሜ መሆኑን (ሉቃስ 18፡22፤23) መስቀሉና ትንሳኤው (ሉቃስ 24፡7) ከሉቃስ 11፡30 ጋር ያነፃፅሩት እና እንደ አማላጅነቱ በአባት ፊት ያለው ሚና (ሉቃስ 12፡8)

**አምስተኛ** ሉቃስ የሰውን ልጅ እንደ መጨረሻው ዘመን ቋንቋ ፤ ታላቁን ተጋድሎ ለማጠቃለልና ለቅዱሳን ሽልማታቸው ሊሠጥ ወደ ምድር ተመልሶ የሚመጣ እንደሆነ ያየዋል (ሉቃስ 9፡26 ፤ 12፡4 ፤ 17፡24.26.30 ፤ 21፡36 ፤ 22፡69)

በአጭሩ "የሰው ልጅ " የሚለው መጠሪያ የሚገጥመው ክርስቶስ ማን ነበር፡፡ የሚለውን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ምን ለመሥራት እንደመጣ ፤ ምን እንደነበረው እና በድነት ዕቅድ ውስጥ ለእኛ ምን እንደሚያከናውን ጭምር የሚገልፅ ዘርፈ ብዙ ትርጓሜ ያለው ነው፡፡

**ረቡዕ** ሚያዝያ 7 2007 ዓ. ም

# የእግዚአብሔር ክርስቶስ

*ሉቃስ 9፡18-27 ን ያንብቡ፡፡ ኢየሱስ ራሱ መልሱን የሚያውቀውን ጥያቄ ለምን ጠየቀ? ስለ ራሱ ብቻ ሳይሆን እርሱን መከተል ማለት ምን ማለት እንደሆነ አስመልክቶ ማስተማር የፈለገው ትምህርት ምንድንነው?*

________________________________________________

________________________________________________

"እኔን ማን ነህ ትሉኛላችሁ" (ሉቃስ 9፡20) ኢየሱስ ከ2000 ዓመታት በፊት የጠየቀው ጥያቄ ዛሬም ድረስ በታሪክ ይዘወተራል፡፡ ሰዎችም ለዚህ ጥያቄ የተለያዩ መልሶችን ሰጥተዋል፡፡ ታላቅ መምህር፣ ፍጹም ጥልቅ የሆነ የሥነ ምግባር ሰው፤ የመስዋዕት ተምሳሌት ፤ ፍርሃት የለሽ ነቢይ ፤ የማህበረሰቡ ለውጥ አራማጅ ፤ የሰው ዘር እንዲሆን ለሚፈልገው ነገር ሁሉ ጥሩ ምሳሌ ፤ ነገር ግን ይህ መሠረታዊ ጥያቄ ከጴጥሮስ አፍ እንዳገኘው ዓይነት መልስ የትኛውም ምላሽ የተሟላ አይደለም፡፡

በተፈጥሮ ላይ ያለውን ሥልጣን (ሉቃስ 8፡22 - 25) ፤ በክፉ መናፍስት ላይ ያለውን ኃይል (ሉቃስ 26-35) በበሽታዎች ላይ ያለውን የበላይነት (ሉቃስ 5፡ 12-15) ከምንም 5000 ሰዎችን መመገብ መቻሉ (ሉቃስ 9፡ 13-17) በሞት ላይ ያለውን ኃይል (ሉቃስ 8፡51-56) ከገለጸ በኋላ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ፤ በሁለት ጥያቄዎች ይገዳደራቸዋል ፤ አንደኛ ሌሎች ስለ እርሱ ምን እንደሚያስቡ ቀጥሎም ደቀ-መዛሙርቱ ራሳቸው ስለ እርሱ ምን እንደሚያስቡ ነበር፡፡ጥያቄውን የጠየቀው አንድ የማያውቀውን ነገር ለመማር አልነበረም፡፡ ይልቅ የእርሱን ሁለንተናዊ መሰጠትን የሚጠይቀውን የእርሱን ማንነት እንዲያስተውሉ ለማገዝ ነበር፡፡

"ክርስቶስን ማወቃችን ከሌሎች የሰማነው ብቻ ሊሆን አይገባም፡፡ በክርስቶስ ላይ የተላለፈውን እያንዳንዱን ፍርድ የሰው አእምሮ የተረዳውን ማንኛውንም ስለ ክርስቶስ የተጻፈውን ትምህርት ሁሉ ምናልባትም የትኛውም የሥነ-መለኮት አዋቂ ሊናገር ከሚችለው ጋር የሚወዳደር የክርስቶስ ትምህርት ማጠቃለያ ለመስጠት የሚያካትተው ስለ ክርስቶስ





ማወቅን ሳይሆን ክርስቶስን ራሱን ማወቅን ነው፡፡ ክርስቶስ ግላዊ የሆነ ሀሳባችንን ይፈልጋል፡፡ እርሱ ጴጥሮስን ብቻ ሳይሆን እያንዳንዳችንን ይጠይቃል፡፡ አንተ/ቺ ስለ እኔ ምን ታስባለህ/ሽ/ ?

ኢየሱስ ለጠየቀው ጥያቄ የእኛም ምላሽ ጴጥሮስ ከሰጠው የእምነት ቃል ውጪ አይሆንም፤ ኢየሱስ " በእግዚአብሔር የተቀባህ" ነህ (ሉቃስ 9፡20)፡፡ ክርስቶስ ማለት " የተቀባ መሲህ ማለት ሲሆን ተልዕኮውም የፖለቲካ ነፃ አውጪ ሳይሆን የሰውን ዘር አጥብቆ ከያዘው ሰይጣንና ኃጢአት ነፃ አውጥቶ የእግዚአብሔርን የፅድቅን መንግሥት መክፈት ነው፡፡

*እንዲሁ ዝም ብሎ ክርስቶስ ማን እንደሆነ ማወቅ በቂ አይደለም፡፡ ይልቅ እርሱን ለራሳችን ማወቅ ያስፈልገናል፡፡ እንግዲህ ክርስቶስን አውቃለሁ የሚሉ ከሆነ ስለ ክርስቶስ የሚያውቁት ምንድን ነው? ታዲያ ይህ የእርስዎ ግላዊ ስለ ክርስቶስ ያለዎት ዕውቀት ነው ወይ እርሱ ምን እንደሚመስል ያስተማረዎት?*

________________________________________________

________________________________________________

**ሐሙስ** ሚያዚያ 8 2007 ዓ.ም

# የኢየሱስ መልክ መለወጥ

በሦስቱም ወንጌል ውስጥ ስለሚገኘው የመለወጥ ታሪክ ያንብቡ፡፡ (ሉቃስ 9፡27-36 ፤ ማቴ. 17፡1-9 ፤ ማር. 9 ፡ 2-8)

*በተጨማሪ ሐዋሪያው ጴጥሮስ በጊዜው የነበረውን ሁኔታ የዓይን ምሥክር በመሆን የሚያስቀምጠውን እውነት (ከ2ጴጥ. 1፡ 16-18) ያለውን ያንብቡ፡፡ ሉቃስ የሚሠጠን ተጨማሪ ሀሳብ ምንድን ነው? እናም አስፈላጊነቱ ምንድነው?*

________________________________________________

________________________________________________

ሉቃስ የታሪኩን ዝርዝር የሚጀምረው ማቴዎስና ማርቆስ ባልጠቀሱት ዝርዝር ሐሳብ ነው፡፡ ኢየሱስ ጴጥሮስን ፤ ዮሐንስንና ያዕቆብን ወደ ተራራ ለፀሎት ወሰዳቸው፡፡ ኢየሱስ እይታውንና አስተሳሰቡን ወደ ኢየሩሳሌም በማድረግ ከፊቱ ማለፍ የሚጠበቅበትን መከራ ያስብ ነበር፡፡ ኢየሱስ ፤ እርሱ የሚያደርገው ነገር እግዚአብሔር እንዲፈጽመው የሚፈልገው ተግባር መሆኑን እርግጠኛ መሆን ፈለገ፡፡ በእንዲህ ዓይነት ዋስትናና እርግጠኝነት በሚያስፈልግ ጊዜ ብቸኛው መንገድ ፀሎት ነው፡፡ የክርስቶስ ፀሎት በዚያው ቅጽበት በራሱ ላይ መለኮታዊ ክብር እንዲፈስ አድርጎታል፡፡ "ሲፀልይም የፊቱ መልክ ተለወጠ፤ ልብሱም የሚያንፀባርቅ ነጭ ሆነ፡፡" (ሉቃስ 9፡29)፡፡

የተለወጠው ኢየሱስ ከሙሴና ኤልያስ ጋር ይነጋገር ነበር፡፡ " በኢየሩሳሌም ሊፈፀም ስላለው ስለ መውጣቱ ይነጋገሩ ነበር" (ቁ. 31) በዚህ ሥፍራ መውጣት የሚለው ቃል በሁለት መልኩ ይስተዋላል ፤ አንደኛው በኢየሩሳሌም ስለሚጠብቀው ሞት ነው፡፡ ምንም እንኳን *(Exodus)* መውጣት የሚለው ቃል ሞትን የሚገልጽ ባይሆንም መውጣት የሚለው በተጨማሪ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ያለውን ታላቅ ከኃጢአት ነፃ ማውጣቱንና ተግባሩን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

የሦስቱ ስብሰባ የተጠናቀቀው  ከሰማይ ማረጋገጫ በሚሠጥ ቃል ነበር፡፡" ይህ ነው የምወደው ልጄ እርሱን ስሙት ! "(ቁ. 35) መለወጡ ኢየሱስን በክብር ቀባው ፤ የእግዚአብሔር ልጅነቱን ዳግም አረጋገጠ ፤ እናም ደህንነት የልጁን  ህይወት ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን  አወጀ፡፡ ስለዚህም ለደቀ-መዛሙርት የተሠጠው ትዕዛዝ "እርሱን ስሙት" ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ሳይገዙና ሳይታዘዙ ደቀ-መዝሙርነት የለም፡፡

ኤሌን ጂ. ኋይት ስለ ሙሴና ኤልያስ ፅፋለች፡፡ " በዙፋኑ ዙሪያ ካሉት መላዕክት ሁሉ በላይ ተመርጠው ስለሚጠብቀው መከራ ኢየሱስን ሊያበረታቱትና ሰማያዊ ዋስትና ኃዘኔታ/ ርህራሄ  ለማሳየት ከእርሱ ጋር አብረውት ሊሆኑ መጡ፡፡" የዓለም ተስፋ የሰብዓዊ ዘር ሁሉ መዳን የንግግራቸው ዋና ነገር ነበር፡፡ *The Desire of Ages P. 425.*

*ስለዚህ  ብዙዎችን ያፅናናው ኢየሱስ ለራሱ መጽናናትንና መበረታታትን ከሌሎች ፈልጓል፡፡ ይህ ጠንካራ መንፈሳዊያን የሆኑ በመካከላችን የሚገኙ መምህራን ፤ መሪዎች ፤ አንዳንዴ ማበረታቻና መጽናኛ ከሌሎች እንደሚያስፈልጋቸው ምን ትምህርት ይሠጠናል? በእውነቱ በዚህ ጊዜ መጽናናትን መበረታታትን የሚፈልግ የምታውቁት ሰው አለን?*

---





## ዓርብ *ሚያዝያ 9 2007 ዓ.ም*

**ለተጨማሪ ጥናት፡-** "የክርስቶስን ሰብዓዊነት እንዳያስተውሉ እንደ ምክንያት የሚሆነውን ማንኛውንም ጥያቄ ያስወግዱ፡፡ እውነት ከምናምነው ነገር ጋር እጅግ ይቀራረባል፡፡ የክርስቶስን ሰብዓዊነት ወደ ውስጥ ስንጋብዝ አድካሚ የሆኑ ማናቸውም ስምምነት መከላከል ቃሎችህ ከሚሠጡት ትርጓሜ የበለጠ መናገር ከቻሉ በቀር፤ የእርሱን ሰብዓዊነት ከመለኮት ጋር የተቀላቀለ የመሆኑን ግልጽ እውነታ ልታጣው ትችላለህ፡፡ አወላለዱ የእግዚአብሔር ተዓምር ሲሆን ይህም ጥቂት እንኳ ሊያጠራጥር የሚችል ወይም ወደዚህ አስተሳሰብ የሚያደላ ክርስቶስ ላይ እምነትን  የሚያጎድል ወይም እርሱ በምንም ሁኔታ እምነትን በሚያጎድል መልኩ አልተመላለሰም፡፡ እርሱ በሁሉም ነገር እንደ ሰው የተፈተነ ቢሆንም "ቅዱስ" ተብሎ ተጠርቷል፡፡ የኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው በሁሉም የተፈተነ ሆኖ ኃጢአትን ግን ያላደረገ መሆኑ ለሰብዓዊ ዘር ያልተገለጠ ሚሥጢር ነው፡፡ የክርስቶስ *ሥጋ* መልበስ እስከ አሁንም ወደፊትም ሚሥጢር ሆኖ ይኖራል፡፡" *Ellen. G White Comments, The SDA Bible Commentary, Vol.5 , pp. 1128 , 1129.*

## የውይይት ጥያቄዎች፡-

❶ *ስለ ክርስቶስ ተፈጥሮ / ባህሪይ ከላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ ያንብቡ ፡፡ በዚህ የክርስቶስን ሰብዓዊ ተፈጥሮ  ከመለኮታዊ ባህሪዩ ጋር በአንድ የመሆኑን እውነት እናገኛለን ፤ ይህም ሙሉ በሙሉ በጥልቀት ለመለካት የምንችለው አይደለም፡፡ አሌን ጂ ዋይት እንደ ጻፈችው "የክርስቶስ ሥጋ መልበስ ቀድሞም ወደፊትም ምሥጢር ነው፡፡" ብላ ከፃፈችው እኛ ይህን ምሥጢር በትክክል ለማስተዋል በሚቸገሩ ሌሎች ሰዎች ላይ ፍርድ ከመናገር ልንቆጠብ የሚገባን ለምንድን ነው?*

❷ *በመለወጥ ተራራ ስለሆነው ያስቡ ይህ አስደናቂ ክስተት በመዳን ታሪክ ውስጥ ሊፈጸም በነበረ ጊዜ ከእርሱ ጋር ወደዚህ ተራራ እንዲሄዱ የተመረጡት ምን እያደረጉ ነበር? እየተኙ ነበር (አንቀላፍተዋል)፡፡ በክርስቶስ ዳግም ምፃት በዚህ ታላቅ የክርስትና ታሪክ ሌላኛው ክስተት ዘመን ለምንኖር ክርስቲያኖች እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቤተክርስቲያን አባላት ይህ ምን አይነት ምሳሌ ሊሆነን ይችላል?*

❸ *ኢየሱስ ስለ ራሱ ያላቸውን (የተናገራቸውን ) ነገሮች ያንብቡ፡፡ ታዲያ ኢየሱስ ዝም ብሎ እንዲያው ታላቅ ሰው ፤ ታላቅ ነቢይ ፤ ወይም ታላቅ የሃይማኖት መሪ ነበር የሚለው አስተሳሰብ እንከን ያለበት የሚሆነው ለምንድንነው? እርሱ ስለራሱ የተናገረውን በእምነት መቀበል ወይም ስለራሱ አሳች ነገርን የተናገረ ነው ከሚሉት አንዱን የግድ መቀበል የሚገባን ለምንድንነው? የክርስቶስን ማንነት የምንቀበልበት ሌላ ምንም አማራጭ የሌለን ለምንድንነው?*





# 4ኛ ትምህርት

ሚያዝያ 10-16 2007 ዓ.ም

# የደቀ-መዝሙርነት ጥሪ

## ሰንበት ከሰዓት

**ለዚህ ሳምንት፡-** ሉቃስ 5፡1-11 ፤ 6፡12-16 ፤ 9፡ 1-6 ፤ ማቴ. 10፡5-15፤ ሉቃስ 10፡1-24 ፤ ሉቃስ 9፡23-25 እና ማቴ. 16፡ 24-28ን ያንብቡ፡፤

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "እንዲህም አላቸው በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ተዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡" *(ሉቃስ 9፡23)፡፡*

"ደቀ-መዝሙር" ተከታይ ወይም፤ ተማሪ ማለት ነው፡፡ በወንጌላትና የሐዋሪያት ሥራ በብዛት ሲኖር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ250 ጊዜ በላይ ደቀ-መዝሙር የሚለው ቃል ይገኛል፡፡

ደቀ-መዝሙር መሆን መንፈስን ያጠነክራል፣ የአእምሮን ትክክለኛነት ይፈትናል፣ እኛንም በአምላካችንና ከሰው ልጆች ጋር ባለን ግንኙነት ከፍተኛውን ደረጃ እንድንደርስ ይፈልግብናል፡፡ ራስን በሙላት የክርስቶስ ህይወትና መልዕክቱ የሚፈልገውን ያህል መስዋዕትነት ሳይከፍሉ ደቀ-መዛሙር መሆን አይቻልም፡፡ ወደ ውስጣችን የገባው የእግዚአብሔር መንፈስ ተገቢው ነገሮች ሁሉ እንዲኖሩ ያመቻቻል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት፤ ራሱን ያለ ምንም መከልከል ለእግዚአብሔር የሠጠ አዕምሮ ለማስተዋልና እግዚአብሄር የሚፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ አሟልቶ ለመገኘት የተጠናከረ ይሆናል፡፡ የሚዋዥቅ ባህሪይ የነበረው ደካማ ብርቱና ፅኑ ወደ መሆን ይቀየራል፡፡ ክርስቲያን ያለ ማቋረጥ ከክርስቶስ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በባህሪይና በአእምሮ

ክርስቶስን እንዲመስል ያደርገዋል፡፡ *Ellen G.White, The Desire of Ages p. 251.*

ይህ ሳምንት ክርስቶስ ደቀ-መዛሙርትን እንዴት እንደጠራቸው እናም ይህ ትምህርት እርሱ በምድር የጀመረውን ሥራ እኛ ስንቀጥል እንዴት እንደሚረዳን እንማራለን፡፡

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለሚያዚያ 17 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

## እሁድ ሚያዝያ 11 2007 ዓ.ም

# የሰው አጥማጆች

ሰምዖንና እንድሪያስ ሌሊቱን በሙሉ ለፍተዋል፡፡ የዓሣ ማጥመጃ ወቅትን በትክክል የሚያውቁ የማጥመድንም ዘዴ ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው መቼ ማጥመድ ማቆም እንዳለባቸው ያውቁ ነበር፡፡ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ እያሉ አንድ ያልተጠበቀ ትዕዛዝ መጣ " ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል መረቦቻችሁንም ለማጥመድ ጣሉ" (ሉቃስ 5፡4) የስምዖን ምላሽም ተስፋ የመቁረጥና ኃዘንን የሚያመለክት ነበር፤ "አቤቱ ሌሊቱን በሙሉ አድረን ስንደክም ምንም አልያዝንም ፤ ነገር ግን እንደ ቃልህ መረቦቼን እጥላለሁ "(ቁ. 5)

አሣ አጥማጆችን ስለ አሣ ማጥመድ የሚመክራቸው ይህ አናፂ ማን ነው? ስምዖን ትቶ ሊሄድ ነበር፤ ነገር ግን እየተናገረው ያለው አፅናኙና በሥልጣን ሲሰብክ የሚያውቀው ጌታ ኢየሱስ በመሆኑ ተፅዕኖ አሳደረበት እርሱም በቃሎችህ መረቡን እጥላለሁ በማለት መለሰለት፡፡

ከዚህ የተነሳ የደቀ-መዝሙርትነት የመጀመሪያው ትምህርት፤ ለክርስቶስ ቃላት መታዘዝ ነው፡፡ እንድሪያስ ዩሐንስና ያዕቆብም ረዥም እና ፍሬ አልባ ሌሊት፤ ብሩህና አስደናቂ በሆነ ማለዳ ሲተካና ፤ ቁጥር የሌለው አሣ ሲያዝ በቶሎ ትምህርት አገኙ፡፡ ጴጥሮስም በጉልበቱ ተንበርክኮ በመጮህ " አንተ ከእኔ ተለይ፤ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ" (ቁ. 8) የራስን ኃጢአተኝነትና የአምላክን ቅድስና መረዳት የደቀ-መዝሙርትነት ሌላኛው አስፈላጊ የሆነ ጥሩ ደረጃ ነው፡፡ ኢሳያስ እንዳደረገው ሁሉ ጴጥሮስም ይህንን ደረጃ አልፏል፡፡





*ሉቃስ 5፡1-11 ፤ ማቴ. 4፡18-22 እና ማር. 1፡ 16-20 ያንብቡ፡፡ ተዓምራቱን ፤ የአሣ አጥማጆች መደነቅ፤ የጴጥሮስን ግራ መጋባት እና የኢየሱስን ስልጣን ያስተውሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ታሪኮች ስለ ደቀ-መዝሙርትነት ምን ይነግሩናል?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

"አትፍራ ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ አለው (ሉቃስ 5፡10) ከዓሣ አጥማጅነት ሰውን ወደ ማጥመድ መሸጋገር ከተራ ሁኔታ እጅግ ከፍ ያለ ነው፤ ይህም ለጌታ ራስን ፈጽሞ ማስረከብን፣ ምንም የማድረግ አቅመ-ቢስነትንና ኃጢአተኝነትን መቀበልን፤ የደቀ-መዝሙርትን የማይታወቅ መንገድ ለመጓዝ እንዲያስችል ወደ ክርስቶስ በእምነት መቅረብን ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ ብቻ መጽናትን ይፈልጋል፡፡ የዓሣ አጥማጅ ህይወት ምን እንደሚገጥመው የማይታወቅ ከማዕበል ጋር ትግል እንዲሁም ስለ ገቢውም እርግጠኝነት የሌለው ነው፡፡ የሰው ማጥመድ ሥራም ከዚህ የሚያንስ አይደለም፡፡ ነገር ግን ጌታ "አትፍራ" በማለት ተስፋ ይሠጠናል፡፡ ደቀ-መዝሙርትነት ቀላል (ተራ) መንገድ አይደለም፤ የራሱ የሆነ ውጣ ውረድ የራሱ ደስታና ግድድሮሾች ያሉት ቢሆንም ደቀ-መዝሙር ግን ለብቻው እንዲሄድ የተጠራ አይደለም፡፡ እርሱ "አትፍራ" ያለው ጌታ ከታማኙ ደቀ-መዝሙር ጎን ይሆናል፡፡

*አሁን እንደገና ወደ ኋላ ይመለሱና የጴጥሮስን ንሰሐ ይመልከቱ፡፡ ኃጢአተኝነቱ ከክርስቶስ መለየት እንዳለበት ምን ያህል ንቁ እንዳደረገው ይመልከቱ፡፡ ኃጢአት እኛን ከእርሱ እንድንለይ የሚገፋን እንዴት ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## ሰኞ ሚያዚያ 12 2007 ዓ.ም

# የአሥራ ሁለቱ መመረጥ

ደቀ-መዝሙርነት በራስ የሚፈጸም አይደለም፡፡ ለኢየሱስ ጥሪ ምላሽ የመስጠት ውጤት ነው፡፡ ሉቃስ ኢየሱስ ጴጥሮስን ፤ እንድሪያስን እና ያዕቆብን (ሉቃስ 5፡11) እና ሌዊ ማቴዎስ

የቀረጥ ሰብሳቢውን (ቁ. 27-32) ቀደም ብሎ መጥራቱን ይጠቅሳል፡፤ አሁን ደግሞ ፀሐፊው የአሥራሁለቱን  መጠራት የድርጊት አፈጻፀምንና ሥፍራውን ለማሳየት በሚችል መልኩ በትረካው እጁ የሰለለችበትን ሰው በሰንበት ከፈወሰውና (ሉቃስ 6፡ 6-11) ይህም ፈሪሳውያን ኢየሱስን ለመግደል ሤራ እንዲጀምሩ የመራቸውን ሁኔታ ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ጌታም ሥራውን ለማጠናከርና ከመስቀሉ ባሻገር ላለው ሥራ እርሱ ሊያሠለጥናቸውና ሊያዘጋጃቸው የሚችልን የሠራተኞችን ቡድን ለማቋቋም ጊዜው እንደሆነ አወቀ፡፡

ሉቃስ 6፡12-16 ፤ 9፡ 1-6ን ያንብቡ፡፡ እነዚህ ጥቅሶች ስለ አሥራ ሁለቱ ደቀ-መዛሙርት መጠራት ምን ይነግሩናል?

ይከተሉት ከነበሩ ብዙ ህዝቦች መካከል ተማሪዎቹ  መምህራቸውን እንደሚከተሉ እርሱን የተከተሉ ብዙዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን የክርስቶስ ተግባር ከዚህ (ከማስተማር) የሚበልጥ ነበር፡፤ የእርሱ ዓላማ የደህንነት መልዕክት እስከ ምድር ዳርቻ የሚያደርሱ ፤ የዳኑ ህዝቦችን ማህበረሰብ መገንባት ነበር፡፡ ለዚህም ተግባሩ ከደቀ-መዛሙርቶች የሚበዙትን ይፈልጋል፡፡ "ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋሪያት ብሎ ሰየማቸው( ሉቃስ 6፡13) ሐዋሪያ ማለት የተለየ መልዕክት ይዞ ለተለየ ዓላማ የተላከ ማለት ነው፡፡ ሉቃስ ይህንን ቃል በወንጌሉ 5 ጊዜ ሲጠቅሰውና በሐዋሪያት ሥራ ከ25 ጊዜ በላይ ሲጠቀመው ማቴዎስና ማርቆስ  እያንዳዳቸው አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ጠቅሰውታል፡፡

አሥራ ሁለቱ የተመረጡት በዕውቀታቸው፤ በሐብታቸው በማህበረሰባዊ ታዋቂነታቸው የተሻለ የግብረገብ ባለቤት ስለሆኑ ወይም ለምርጫ ቅድሚያ የሚያደርጋቸው ምንም ነገር ተገኝቶባቸው አይደለም፡፡ እነርሱም ተራ ሰዎች እንዲሁም የኋላ ታሪካቸውም ተራ ነበር፡፡ አሣ አጥማጆች ቀረጥ ሰብሳቢዎች ፤ ቀናተኛ ፤ ተጠራጣሪ እናም በኋላ ከሀዲ የሆነውም ይጨመር ነበር፡፡ እነርሱም ለአንድ ዓላማ ብቻ ነበር የተጠሩት ፤ የንጉሥና የመንግስቱ አምባሳደሮች ለመሆን ነበር፡፡

"ሰዎች ሊገሩና ከእርሱ ሊማሩ ፈቃደኞች ከሆኑ እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ ሊያሰለጥናቸው እስከ ሰብዓዊ ባህሪያቸውና ማንነታቸው ይቀበላቸዋል፡፡ እነርሱ የተመረጡት ፍፁም ስለሆኑ ሳይሆን ፍጹም አለመሆናቸውን በመቀበል፤ እውነትን በማወቅና በመለማመድ በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ አማካይነት እርሱን ወደ መምሰል ስለሚለወጡ ነው" *Ellen G.White, The Desire of Ages, p. 294.*





*እኛም ሆንን ሌሎች የቤተክርስቲያን አባላት ፍጹም አለመሆናችንን ማወቅ አለብን፡፡ እኛ ሁላችንም በዕድገት ሂደት ውስጥ ነን (ምንም እንኳን ሌሎች እንዲያድጉ በሚፈለገው ፍጥነት ባያድጉም)፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለን አብረናቸው ለመስራት ሌሎችን ባሉበትሁኔታ መቀበል እንዳለብን የምንማረው እንዴት ነው?*

________________________________________________

________________________________________________

**ማክሰኞ** ሚያዝያ 13 2007 ዓ.ም

# *ለሐዋሪያት የሥራ ኃላፊነት መሥጠት*

*ሉቃስ 9፡1-6 እና ማቴ. 10፡5-15ን ያንብቡ፡፡ ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች እንዴት እንደጠራቸው ስናውቅ ምን መንፈሳዊ እውነት እንማራለን?*

ሉቃስ የሐዋሪያትን የሥራ ኃላፊነት በ3 ደረጃ ይገልፃቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ኢየሱስ በአንድ ላይ ጠራቸው (ሉቃስ 9፡1) ጥሪ የሚለው ቃል በክርስትና መዝገበ ቃላት የክርስቲያንን ተልዕኮ በተመለከተ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ የሥነ-መለኮት ትምህርት ቃል ከመሆኑ ቀድሞ የሕይወት ልምምድ ሊሆን ይገባል፡፡ ሐዋሪያት የጠራቸውን ሊያከብሩ፤ ወደ እርሱ ሊመጡ እና ከእርሱ ጋር አብረው ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ የጠራቸውን መታዘዝና ሁሉንም ነገር ለእርሱ ማስረከብ ተልዕኮውን ለመፈጸም የሚያስፈልገውን ህብረት ለመለማመድ የሚያስፈልጉ ሁለት ነገሮች ናቸው፡፡

ሁለተኛ፤ "ኢየሱስም ኃይልና ሥልጣን ሠጣቸው፡፡ (ሉቃስ 9፡1)"፡፡ ኢየሱስ የመንግሥቱን መልዕክተኞች ባዶ እጃቸውን አይሰዳቸውም፡፡ ወይም በራሳቸው ጥንካሬ የእርሱ ተወካዩች እንዲሆኑ አይፈልግም፡፡ የእርሱን ተልዕኮ ለማከናወን የእኛ ትምህርት ፤ ባህል ፤ የኑሮ ደረጃ፤ ሀብት ወይም የማስተዋል ችሎታችን ምንም ኃይል የላቸውም፡፡ የሚያስችል የሚያስታጥቅ፤ ኃይል የሚሠጥ ኢየሱስ ነው፡፡ ሃይልን የሚወክል የግሪክ ቃል *'dynamite'* የሚለው ሲሆን ከዚህም ቃል *'dynamo'* የብርሃን ምንጭ የሚለው እና *'dynamite'* የሚለው ተራሮችን የሚያፈርሰው የኃይል ምንጭ የተመሠረተበት ቃል ነው፡፡ ኢየሱስ የሚሠጠው ኃይልና ሥልጣን ክፉውን ለመስበርና የእርሱን ዓላማ ለመፈጸም በቂ ነው፡፡

የሰው ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ሲስማማ ሁሉን የሚችል ኃይል ይኖረዋል፡፡ በእርሱ ትዕዛዝ የሚሠራ ማንኛውም ነገር የሚከናወነው በእርሱ ኃይል ነው፡፡ የእርሱ ትዕዛዛት ሁሉን ለመተግበር የሚያስችሉ ጥሪዎች ናቸው፡፡ *Ellen G White, Christ Object Lesson , P. 33*

*ሦስተኛ፤* ‹‹ኢየሱስ የእግዚአብሔርን *መንግሥት* እንዲሰብኩና ድውያንንና ህመምተኞችን እንዲፈውሱ ላካቸው (ሉቃስ 9፡2) መስበክና መፈወስ አንድ ላይ የሚሄዱ በመሆናቸው የደቀ-መዛሙርቱ ተልዕኮ ለመላው ሰውነት ፤ አዕምሮና ነፍስ ጥንቃቄ ማድረግ ነበር፡፡ ኃጢአትና ሰይጣን መላውን ሰውነት ስለማረኩ መላው ሰውነት ወደሚቀድሰው የክርስቶስ ኃይል መምጣት አለበት፡፡

የደቀ-መዛሙርት ህይወት ሊፀና የሚችለው ይህ ህይወት ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ያለ ምንም ጣልቃ ገብነት ሲሰጥ ነው፡፡ ወርቅም ሆነ ብር፤ እናትም ሆነ አባት፤ ሞትም ሆነ ህይወት፤ ዛሬ ሊሆን የሚችል ነገር ሆነ የነገው ድንገተኛ ሁኔታ በደቀ-መዝሙርና በክርስቶስ መካከል ሊገባ አይገባም፡፡

*"ለጉዞ የሚሆን ምንም ነገር አትያዙ" (ሉቃስ 9፡3) በዚህ ሥፍራ እኛ ልናስተውል የሚገባን ምን አስፈላጊ መመሪያ እናገኛለን?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## *ረቡዕ* ሚያዝያ 14 2007 ዓ ም

# *ሰባዎቹን መላክ*

ሉቃ 10፡1-24 ን ያንብቡ፡፡ በዚህ ታላቅ ተጋድሎ መካከል የሰባዎቹ መላክ ታሪክ፤ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ በመማረክ ሥራ ውስጥ ምን ትምህርት ይሠጠናል፡፡

በአገልግሎቱ ጊዜ ክርስቶስን ከ12 ደቀ-መዛሙርት በላይ ተከትለውታል፡፡ ጴጥሮስ በይሁዳ ፈንታ ሰው እንዲተካ ጥሪ ባደረገ ጊዜ የደቀ-መዛሙርቱ ቁጥር ወደ 120 ይደርስ ነበር (ሐዋ.





1፡15)፡፡ ጳውሎስ እንደሚነግረን ክርስቶስ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ ደቀ-መዛሙርቱ ከ500 የማያንሱ ነበሩ (1ቆሮ. 15፡6) ስለዚህ የ70ዎቹ መላክ የሚያሳየው የክርስቶስን ደቀ-መዛሙርት ቁጥር ውስንነት ሳይሆን ለጉብኝት ወደ ገሊላ በሚሄድበት ጊዜ መንገድ እንዲያዘጋጁለት የላካቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የ70ዎቹን ታሪክ የዘገበው ልዩ የተልዕኮ አስተሳሰብ ያለው ሉቃስ ብቻ ነው፡፡ ቁጥር 70 በአይሁዶች ታሪክም ሆነ በቅዱሳት መጽሀፍት ተምሳሌታዊ ነው፡፡ ዘፍጥረት 10 70ዎቹ የምድር ነገዶች የኖህ ልጆች እንደሆኑ ሲገልፅ የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ ሉቃስ የዓለም አቀፍ አመለካከት ያለው ነው፡፡ ሙሴ እንዲረዱት ሰባ ሽማግሌዎችን መረጠ (ዘሌ. 11፡16 ፤ 24፤25) የአይሁድ መሪዎች ጉባኤ 70 ሰዎች ያሉበት ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከክርስቶስ የ70ዎቹ ጥሪ ጋር ግንኙነት ይኑራቸው አይኑራቸው የሚያስጨንቀን ነገር አይደለም፡፡ ነገር ግን በዚህ ስፍራ አስፈላጊው ነገር ኢየሱስ የቤተክርስቲያን መሪዎች አሠልጣኝ እንደመሆኑ አስቀምጦልን የሄደው አሠራር ኃይልን በአንድ አካባቢ ብቻ መሰብሰብ ሳይሆን ለደቀ-መዛሙርቱ ሁሉ ማድረስን ነው፡፡

ሰባዎቹ ተግባራቸውን ፈጽመው በደስታ ተመለሱ እንዲህም አሉ "አጋንንት እንኳ በስምህ ተገዝተውልናል፡፡" (ሉቃስ 10፡17) ነፍሳትን በመማረክ ሥራ ስኬት የወንጌላዊው ተግባር አይደለም፡፡ ወንጌላዊው መሣሪያ ብቻ ነው፡፡ ስኬቱ የሚመጣው "በስምህ" ብቻ ነው፡፡ ስኬታማ በሆነ የወንጌል ተልዕኮ ሁሉ የክርስቶስ ስም ዋና ነገሩ ነው፡፡

ነገር ግን በ70ዎቹ የወንጌል ተልዕኮ ስኬት ላይ ኢየሱስ የሠጠውን ሶስት ዋነኛ ምላሾችን ልብ በሉ፡፡ በመጀመሪያ፤ ክርስቶስ በወንጌል ስኬት ውስጥ የሰይጣንን መሸነፍ ያያል፡፡ (ቁ. 18) ሁለተኛ የደቀመዝሙር ደስታ ሊሆን የሚገባው የምድር ክንውን ሳይሆን ስሙ/ስሟ በሰማይ መዝገብ መጻፉ እንደሆነ ተናግሯል (ቁ. 20) ሦስተኛ ከሰይጣን እስራት የሚላቀቅን ማንኛውንም ሰው ሰማይ የደስታ ጉዳዩ አድርጎ ይመለከተዋል፡፡ እያንዳንዱ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚማረክ ነፍስ በሠይጣን ንድፍ ላይ የሚያርፍ ኃይለኛ ቡጢ ነው፡፡

*ሉቃስ 10፡24 እንደገና ያንብቡ፡፡ ነብያትና ነገሥታት ለማየት ፈልገው ያላዩትና እኛ ያየነው ምንድንነው? ይህ ለእኛ ምን ማለት ነው?*

____________________________________________________________

**ሐሙስ** ሚያዝያ 15 2007 ዓ ም

# ደቀ-መዝሙርነት የሚያስከፍለው ዋጋ

ሶቅራጠስ ፕላቶ ነበረው፡፡ የተለያዩ የኃይማኖት መሪዎች ፍጹም ራሳቸውን የሠጡ ተከታዮች ነበሩዋቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ ደቀ-መዝሙር በመሆንና የክርስቶስ ተከታይ/ደቀ-መዝሙር በመሆን መካከል ያለው ልዩነት የሰው ተከታዮች መሠረት የሚያደርጉት የሰብዓዊ ፍልስፍናን ሲሆን ክርስቶስን መከተል ሥሩን የሰደደው በክርስቶስ ማንነትና በእርሱ ገድል ላይ ነው፡፡ ስለዚህ የክርስቲያን ደቀ-መዝሙርትነት መሠረት የሚያደርገው በክርስቶስ ትምህርቶች ላይ ብቻ ሳይሆን እርሱ ለሰብዓዊ ዘር ደህንነት በፈጸመው ነገር ላይ ጭምር ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ኢየሱስ ተከታዮቹን በሙላት ራሳቸውን ለእርሱ የለዩ እንዲሆኑ መስቀላቸውን እንዲሸከሙ እና እርሱ በሚመራቸው መንገድ እንዲከተሉ ይጠራቸዋል፡፡ በጎልጎታ መንገድ ላይ የክርስቶስን ዱካ የሚከተሉ ህዝቦች ከሌሉ የክርስቲያን ደቀ-መዝሙርነት የለም፡፡

ሉቃስ 9፡23 -25 ፤ ማቴ. 16 16፡ 24-28 ፤ ማር. 8 ፡34 – 36 ን ያንብቡ፡፡ እዚህ ላይ ክርስቲያን ነኝ ለሚል ሁሉ ያለው ወሳኝ የሆነ መልዕክት ምንድን ነው?

የክርስቲያን ደቀ-መዝሙርነት በአዳኙና በዳነው መካከል የሚሠራ ግንኙነት ነው፤ እንደ ዳኑ ሰዎች አዳኙን ልንከተለው ይገባናል፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ እኔም አሁን ህያው ሆኜ አልኖርም ግን ክርስቶስ በእኔ ይኖራል" (ገላ. 2፡20)

ክርስትና የሚያስከፍለው ዋጋ በሉቃስ 9፡23 ተገልጿል፡፡ "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡" የሚከተሉትን የሚሠሩ ቃላትን ልብ ይበሉ፤ መካድ ፤ መሸከም፤ እና መከተል፡፡ ጴጥሮስ ኢየሱስን ስለ መካዱ ስናነብ "መካድ" ለሚለው ጥሩ የሆነ መግለጫ አናገኝም፡፡ ጴጥሮስ ኢየሱስን አላውቀውም አለ፡፡ ስለዚህ ደቀ-መዝሙርነት ራስን መካድ የሚጠይቅ ከሆነ ራሴን አላውቅም ማለት መቻል አለብኝ፡፡ ምክንያቱም ራስ ሞቷልና በእርሱም ፈንታ ክርስቶስ በህይወት ሊኖር ይገባል (ገላ. 2፡20) ሁለተኛ መስቀሉን ዕለት ተዕለት መሸከም ሳያቋርጥ ራስን ለመሰዋት ልምምድ ማድረግ ነው፡፡ ሦስተኛ የህይወት አቅጣጫን ክርስቶስና እርሱን ብቻ ማድረግን ይጠይቃል፡፡





በሉቃ 9፡57-62 በተገለፀው መሠረት ኢየሱስ የደቀ-መዝሙርነትን ዋጋ ከዚህ የበለጠ አድርጎታል ፤ ከክርስቶስ ቅድሚያ የሚወስድ አንዳች ነገር ሊኖር አይገባም፡፡ በወዳጅነት እና በህብረት በተግባርና በአምልኮ እርሱና እርሱ ብቻ ከሁሉም ከፍ ማለት ይገባዋል፡፡ በክርስቲያን ደቀ-መዝሙርነት ለራስ መሞት ምርጫ ሳይሆን ፤ የግድ የሚያስፈልግ ነው፡፡ "ክርስቶስ ሰውን ሲጠራ ሳለ መጥቶ ለራሱ እንዲሞት ይፈልጋል፡፡ ይህም ሁሌ ተመሳሳይ ሞት ነው፡፡ በኢየሱስ ለአሮጌው ማንነት የመሞት ጥሪ. . . ክርስቶስን ሊከተል የሚችል የሞተ ሰው ብቻ ነው፡፡" *Dietrich Bonhoeffer, The cost of discipleship (New York ; The Macmillan Co. 1965), p.99*

ክርስቶስን መከተል እርስዎን ምን ዋጋ አስከፈለ? ስለ መልስዎትና ስለሚያስከትለው ነገር ሁሉ አጥብቀው ያስቡ፡፡

**ዓርብ** ሚያዝያ 16 2007 ዓ.ም

**ለተጨማሪ ጥናት፡-** "መስቀልን ከፍ ማድረግ ራስን ከነፍስ ለይቶ ሰውን የክርስቶስን ጭንቀት ሸክም መሸከም እንዴት እንደሆነ መማር በሚያስችል ሥፍራ ያስቀምጣል፡፡ መስቀሉን ተሸክሞ ከኋላው ሳይከተሉና ቀንበሩን ሳይሸከሙ የክርስቶስ ተከታይ መሆን አይቻልም፡፡ ፈቃዳችን ከሰማይ ፈቃድ ጋር ስምምነት ከሌለው ዝንባሌዎቻችንን ልንክድ ይገባል፤ ውድ ፍላጎታችንን መተው እና የክርስቶስን ዱካ ልንከተል ይገባናል፡፡" *Ellen G.White , Sonsand Daughters of God, p 69.*

## የውይይት ጥያቄዎች፡-

❶ *ወደ ኋላ ሄደው በረቡዕ ቀን ትምህርት መጨረሻ ላይ ያለውን ጥያቄ በሉቃ 10፡24 መሠረት ይመልከቱት ፡፡ "ብዙ ነብያትና ነገሥታት ለማየት ተመኝተውት የነበረ ነገር ግን ያልሆነላቸው እኛ በዚህ ዘመን የምንኖር ሰዎች ውስጡን የምናውቀውና መመስከር የምንችለው ምንድን ነው? ለምሳሌ የትንቢት መፈጸምን እንዴት እናየዋለን ? ስለ ዳን. 2፤7 እና 8 ስናስብ ምን ያህሎች ተፈጽመው የእኛ ታሪክ እውነታ ሲሆን ለነቢያትና ለነገሥታት ግን ትንቢት ነበር? ሌላስ ምን ያስባሉ ?*

❷ *ክርስቶስ ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል ያለውን በጥልቀት ተወያዩበት ይህ ምን ማለቱ ነው? ወይም ህይወትን ለማትረፍ ህይወትን ማጣት ማለት ምን ማለት ነው ? አማኝ ያልሆነ ሰው የዚህ ዓለም  የሆነ ነገር መጠበቁ አንድ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም አለን ብለው የሚያምኑት ይህንኑ ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ ታዲያ በሌላ በምን ይጠበቁ ? ነገር ግን እንደ  አማኝ ይህ ዓለም እንደሚያበቃና ሌላ ዓለም እንደሚጀምር የምናውቅ ከዚህ ዓለም የምናገኘውን ትርፍ ለመፈለግ ዝግጁዎች ሆነን እንገኛለን፡፡ ከዚህ አደገኛና ለመንፈሳዊነት ወጥመድ ከሚሆን ነገር ራሳችንን መከላከል የምንችለው እንዴት ነው?*

❸ *ሉቃስ 10፡ 17-20 ያንብቡ፡፡ ኢጋንንት በክርስቶስ ስም ሲወጡ ሲያዩ ደቀ-መዛሙርቱ የነበራቸውን መደነቅ ማስተዋል ይቻላል፡፡ ክርስቶስ  ለእነርሱ የሰጠውን ምላሽ ይመልከቱ፡፡ ነፍሳትን በመፈለግ ሥራ ለተሠማራ ለማንኛውም ሰው የሚሆን ነገር እርሱ ያለው ምንድን ነው?*

❹ *መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዋናይ ከነበሩት ሰዎች ውጪ ክርስቶስን ለመከተል ምርጫቸውን ያደረጉ ምናልባትም ከብዙዎቻችን በተሻለ ሁኔታ ታላቅ የሆነ ዋጋ የከፈሉ እነማን ናቸው? በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ ራሳችሁን ጠይቁ " እነዚህ ሰዎች ክርስቶስን መከተላቸው ያስከፈላቸው ዋጋ ምንድን ነው? ምንስ ተው? ታዲያ እንደ እነርሱ ለመሆን ፈቃደኛ ነን ወይ?*





# 5ኛ ትምህርት

ከሚያዝያ 17-23 2007 ዓ.ም

# ክርስቶስ የሰንበት ጌታ

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት ጥናት፡-** ማር. 1፡21 ፤ 6፡2 ፤ ሉቃስ 4፡17-19 ፤ 31-37 ፤ 2ቆሮ. 5፡17 ፤ ሉቃስ 6፡ 1-11 ፤ 13፡ 10-16ን ያንብቡ፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥሮአል እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም ፤ እንዲሁም የሰው ልጅ የሰንበት እንኳ ጌታዋ ነው" *(ማር. 2፡27)* ፡፡

ምንም እንኳን ሉቃስ ወንጌሉን የፃፈው ለአህዛብ ቢሆንም "ስለ ሰንበት በተደጋጋሚ መጻፉ አስፈላጊ ነበር፡፡ ወንጌላትና የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ 54 ጊዜ ከተጠቀሰው ሰንበታት መካከል 17ቱ፤ በሉቃስ ወንጌል ፤ 9ኙ በሐዋሪያት ሥራ፤ 9ኙ በማቴዎስ ፤ 10ሩ በማርቆስ እና 9ኙ በዩሐንስ ወንጌል ይገኛሉ፡፡ ሉቃስ ከአህዛብ ወገን ወደ ክርስትና የመጣ እንደመሆኑ የሰባተኛው ቀን ሰንበት ለአይሁድም ሆነ ለአህዛብ የተሠጠ መሆኑን ያምናል፡፡ የክርስቶስ የመጀመሪያው ምፃት በሰንበት አጠባበቅ ላይ ያመጣው ምንም ለውጥ የለም፡፡

በእርግጥ "ክርስቶስ በምድራዊ የአገልግሎቱ ዘመን ፤ በሁሉም አስተምሮዎቹ እርሱ ራሱ ለመሠረተው ለዚህ ተቋም (ሰንበት) የሚገባውን አክብሮት በመስጠት አሣልፏል፡፡ በእርሱ ዘመን ሰንበት የተጣመመ ሲሆን አጠባበቁም የራስ ወዳዶችንና በዘፈቀደ የሰዎችን ባህሪይ እንጂ የእግዚአብሔርን ባህሪይ የሚያሳይ አልነበረም፡፡ ክርስቶስ እግዚአብሔርን እናውቃለን

የሚሉ ሰዎች ስለ እርሱ በስህተት ያስተማሯቸውን ትምህርቶች በሙሉ ለይቷቸዋል፡፡

የዚህ ሳምንት ትምህርት ኢየሱስ የሰንበት ጌታ ስለመሆኑ ያስቃኘናል፡፡ በዚህም እርሱ ሰንበትን እንዴት ጠብቆ ለእኛ ምሳሌ እንደተወልን እንማራለን፡፡ የሳምንቱን መጀመሪያ ቀን እንደ ሰንበት ማክበርን ክርስቶስም ሆነ አዲስ ኪዳን የሚደግፉት አልነበረም፡፡

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለሚያዚያ 24 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

**እሁድ** ሚያዝያ 18 2007 ዓ.ም

## "እንደ ልማዱ" (ሉቃስ 4፡16 -30 ፤ ኢሳ. 61 ፡ 1.2 ) በተጨማሪ ያንብቡ፡፡

"እንደ ልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገባ" (ሉቃስ 4፡16) ይህ ጥሩ የሆነ የአድቬንቲስት ጥቅስ ነው፡፡ ብዙዎቻችን በትልልቅ የወንጌል ጥረት ፕሮግራሞችና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ሰንበትን መጠበቅ የክርስቶስ ልምድ እንደነበር ለማሳየት እንጠቀምበታለን፡፡

በአይሁዳውያን ኃይማኖት ምኩራቦች ወሳኝ የሆነ ሚና ይጫወቱ ነበር፡፡ በምርኮ ዘመን መቅደስ ባልነበረባቸው ዘመናት ለአምልኮና ወጣቶችን ለማስተማር ምኩራቦች ተገንብተው ነበር፡፡ በየትኛውም አሥር የሚሆኑ የአይሁድ ቤተሰቦች በሚገኙበት ሥፍራ ሁሉ ምኩራብ ይገነባ ነበር፡፡ በናዝሬት ከተማ ያደገ በመሆኑ ክርስቶስ በእያንዳንዱ ሰንበት ወደ ምኩራብ የመሄድን ልምድ ይከተል የነበረ ሲሆን ወዳደገበት በሄደበት የመጀመሪያ ጉዞው በምኩራብ ውስጥ ተገኘ፡፡

ማር. 1፡21 ፤ 6፡2 ፤ ሉቃስ 4፡16-30 ፤ 6፡6-11 ፤ 13 ፡10-16 እና 14፡ 1-5 ን ያንብቡ፡፡ እነዚህ ጥቅሶች ስለ ሰንበትና ስለ ክርስቶስ ምን ያስተምሩናል? እነዚህን ጥቅሶች እያነበቡ ሳለ ክርስቶስ ሰንበትን የመሻርን ወይም ሰንበትን የመጠበቅ ትዕዛዝን የተናገረበት ማንኛውም ሥፍራ ካለ ወይም ሰንበትን በሌላ ቀን የተካበት ሁኔታ ራስዎን ይጠይቁ፡፡





"እንደ ልማዱ" (ሉቃስ 4፡16) ይህንን ሀረግ የተጠቀመው ሉቃስ ብቻ ነው፡፡ በሉቃ 4፡16 የሱስ በናዝሬት ምኩራብ እንደተገኘ እና በሉቃስ 22፡39 የመስቀሉ ጊዜ እየቀረበ ሲሄድ ክርስቶስ እንደ ልማዱ ወደ ደብረ-ዘይት ተራራ ሄደ በሁለቱም ጊዜ "ልማድ" ከአምልኮና ፀሎት ጋር የተያያዘ ነበር፡፡

*ኢየሱስ በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ እንደ ሄደ ሁሉ እኛም ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ልምዳችን ሊሆን የሚገባው ለምንድን ነው?*

________________________________________________________

________________________________________________________

በመጀመሪያ እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ ነው፡፡ በየትኛውም ሥፍራ ሊመለክ ይችላል፤ ነገር ግን በእርሱ ህግ የታዘዘን እንዲሁም በፍጥረቱ የተሠየመ ቀን ላይ በአንድነት መሆን የተለየ ትርጉም አለው፡፡

ሁለተኛ እግዚአብሔር ፈጣሪና አዳኝ መሆኑን ከህዝብ ጋር የመስማማትን ትልቅ ዕድል ይፈጥራል፡፡

በመጨረሻም አብሮ ለማምለክና አንዱ የሌላውን ደስታና ያለንን ውስጣዊ ስሜት ለመጋራት ይጠቅማል ፡፡

*እኛን ሰንበትን በመጠበቃችን ምክንያት ህግ ጠባቂዎች እና በእሥራት ያሉ ናቸው ብለው የሚያስቡ ሰዎች ሰንበት ይዞ የሚመጣውን ታላቅ በረከት አጥተዋል፡፡ ሰንበትን በነፃነት ማክበርን እንዴት ተለማመዱት?*

**ሰኞ** ሚያዝያ 19 2007 ዓ.ም

## የሰንበት መልዕክትና ትርጓሜው

"ሊያነብም ተነሳ" (ሉቃስ 4፡17) የሰንበት ዕለት ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርንም ቃል ለመስማትም ጭምር ነው፡፡ ያለ እግዚአብሔር ቃል የሆነ ህይወት ከኃጢአት ወጥመድ የራቀ አይደለም፤ " አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ

ሰወርሁ" (መዝ. 119፡11)፡፡

*ሉቃስ 4፡17-19 ያንብቡ፡፡ ዛሬ ስለ ክርስቶስ የምናውቀውን ሁሉ ማንነቱን ለእኛ ያደረገውን ሁሉ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናስብ የነዚህን ቃላት ትርጓሜ እንዴት እናስተውላለን? መሲህነቱ የሚጠይቃቸውን ነገሮች በህይወትዎ ከእርሱ ጋር ባለዎት ጉዞ የተለማመዱት እንዴት ነው?*

——————————————————————————————————

——————————————————————————————————

ኢየሱስ ክርስቶስ ከኢሳ 61፡1.2 ካነበበ በኃላ " ዛሬ ይህ መፅሐፍ በጆሮአችሁ ተፈፀመ" አለ (ሉቃስ 2፡21) ዛሬ የሚለው ቃል ትኩረት ያሻዋል፡፡ አይሁዳውያን የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠብቁ የነበረው አንድ ጊዜ ወደፊት ትዕይንታዊ በሆነ ሁኔታ ወታደሮችን በመጠቀም ገዢዎቻቸውን ነቅሎና አስወግዶ የዳዊትን ዙፋን ይይዛል ብለው ይጠብቁ ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የእግዚአብሔር መንግሥት በእርሱ መምጣት እንደተመሠረተና እርሱ ከኃጢአት ኃይል ነፃ ለማውጣት ዲያቢሎስን ለመስበርና በእርሱም ግዞት ቁጥጥር ሥር ያሉትን ነፃ ለማውጣት እርሱ በአካል የተገኘ መሆኑን ገለፀላቸው፡፡

መሲህነቱ የሚጠይቀው ነገር ከሰንበት ጋር ምን ያህል ቁርኝት እንዳለው ያሰቡ፡፡ ሰንበት የዕረፍት ቀን ሲሆን ዕረፍትም በክርስቶስ ነው (ዕብ 4፡1-4) ሰንበት የነፃነትና ነፃ የመውጣት ምልክት ነው (በክርስቶስ ያለን ነፃነት (ሮሜ 6፡ 6-7) ሰንበት የፍጥረት መታሰቢያ ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ እንደገና የመፈጠራችንም መታሰቢያ ጭምር ነው (2ቆሮ 5፡17 ፤ 1ቆሮ 15፡ 51-53) ኢየሱስ ብዙዎቹን በህመም የተጨቆኑትንና በእሥራት ያሉትን ነፃ ለማውጣት የፈውስ ተግባራትን በሰንበት ቀን ማድረጉ በአጋጣሚ የሆነ አልነበረም፡፡

ሰንበት በብረት ላይ እንደ ተቀረጸ እንደማይጠፋ ነገር በመሆን በክርስቶስ የተሠጠን የየሳምንቱ ማሳሰቢያ ነው፡፡

*ክርስቶስ ለእኛ ባደረገው ነገር ላይ ማረፍ እንድንችል መዳናችን በእምነት ላይ ብቻ የተመሠረተ መሆኑን ሰንበት የሚያሳስበን እንዲሁም የሰማይን መንገድ በራሳችን አካሄድ እንዳንፈልገው የሚረዳን እንዴት ነው?*





**ማክሰኞ** ሚያዚያ 20 2007ዓ.ም

# በቅፍርናሆም የተደረጉ የሰንበት ዕለት ፈውሶች

በናዝሬት በክርስቶስ ላይ የተነሳው ተቃውሞ መጀመሪያ ያገለግል ወደነበረበት ወደ ቅፍርናሆም እንዲመለስ አደረገው (ማቴ. 4፡13) ይህ በጣም አስፈላጊ የሆነ ከተማ ለክርስቶስ በገሊላ ለነበረው አገልግሎቱ መሠረት ሆኖለት ነበር፡፡ ክርስቶስ እንደ ልማዱ በሰንበት የሄደበት ምኩራብ የሚገኘውም በዚህ ከተማ ሲሆን የተገነባውም በሮማዊው ባለሥልጣን ነበር (ሉቃስ 7፡5)

በዚህች ሰንበት የክርስቶስ ብዙዎቹ ተግባራት ማስተማርን፣ መፈወስን፣ እንዲሁም መስበክን ጭምር የሚያጠቃልል ነበር፡፡ ክርስቶስ ስለምን እንደሰበከ ምንም የተባለ ባይኖርም የህዝቡ ምላሽ ግን የሚያሳየው መደነቅን ነበር፡፡

"የሚናገረው በሥልጣን ነበር" (ሉቃስ 4፡32) የእርሱ ትምህርት ከመምህራኑ ትምህርት ጋር የሚቃረን ነበር፡፤ ተራ የሆነ ማድበስበስ የለበትም፡፡ በዚህም ሥፍራ በሥልጣን መስበክ ፤ መሠረቱ በቅዱስ ቃሉ ላይ የሆነ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሠበከ ኃጢአትን በስሙ የሚጠራና ለንስሐ የሚጎተጉት ስብከት ነበር፡፡

ሉቃስ 4፡31-37 ን ያንብቡ፡፡

**1ኛ.** ስለ ታላቁ ተጋድሎ

**2ኛ.** ስለ ኢጋንንት

**3ኛ.** የሰንበት ዓላማን በሚመለከት

**4ኛ.** በክፉው ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ኃይል እንዲሁም ሌላ ምን ታላቅ እውነት ነው በዚህ ቁጥር የተገለፀው በሉቃስ 4፡31 -41 ሉቃስ በሰንበት ዕለት ከተደረጉት አምስቱ ታላላቅ ፈውሶች መካከል የመጀመሪያውን ዘግቦታል፡፡ ሉቃስ 4፡38.39 ፤ 6፡6-11 ፤ 13፡ 10-16፤ 14፤ 1-16ን ይመልከቱ፡፡ በናዝሬት ባደረገው ንግግሩ ኢየሱስ መፈወስ፣ የተጨቆኑትን ነፃ ማውጣትና ልባቸው የተሠበሩትን መፈወስ የእርሱ ተልዕኮ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ እዚህ በቅፍርናሆም ደግሞ ፤ በሰንበት ዕለት የሚያመልኩ ሰዎች በሞሉበት ኢጋንንት የተጠናወቱት

ሰው ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በመናገር ተገዳድሮታል፡፡ "ተው የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለን? ማን እንደሆንህ አውቄሃለሁ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ " ሉቃስ 4፡34 አጋንንቱ የሠይጣን ሰራዊት እና ከሰው በላይ የሆነ ፍጡር በመሆኑ ሥጋ የለበሰውን አዳኛችንን ለይቶ ለማወቅ እጅግ ፈጣን ነበር፡፡ በዚህ ታሪክ በሚታየው ዓለምና በማይታየው መካከል የነበረው ሽፋን ተወገደ፡፡

*በዚህ ሥፍራ ታላቁ ተጋድሎ እንዴት ግልፅ በሆነ ሁኔታ እንደታየ ያስቡ፡፡ ብዙውን ጊዜ እንደዚህ አልነበረም፡፡ በራስዎት ህይወት ይህ ተጋድሎ የሚከናወነው እንዴት እንደሆነ ተመልክተዋል? በዚህ ውጊያ የእርስዎ አሸናፊነት ብቸኛ ተስፋ ምንድን ነው? ነቆሮ. 15፡2ን ይመልከቱ፡፡*

__________________________________________________________

__________________________________________________________

**ረቡዕ** ሚያዝያ 21 20007 ዓ.ም

# የሰንበት ጌታ

ሉቃስ 6፡1-11 ክርስቶስ ስለ ሰንበት ከፈሪሳውያን ጋር ያደረገውን ሁለት ንግግሮች እናገኛለን፡፡

*የመጀመሪያውን ታሪክ በሉቃ 6፡1-5 ያንብቡ፡፡ እርሱና ደቀመዛሙርቱ ስለ ሰንበት ግድ የሌላቸው እንደሆነ የቀረበውን ክስ ክርስቶስ እንዴት ገጠመው?*

በእርሻ መካከል እየሄዱ ሳለ ፤ ደቀ-መዛሙርቱ እሸት ቀጥፈው በእጃቸው አሽተው በሉ፤ ነገር ግን ፈሪሳውያን እውነቱን በማጣመም ደቀ-መዛሙርቱን የሰንበትን ትዕዛዝ እንደሻሩ በማድረግ ክስ አቀረቡ፡፡ ክርስቶስም በቀጥታ የንጉሥ ዳዊትን ታሪክ በመጥቀስ በተራበ ጊዜ እርሱና ወታደሮቹ ወደ እግዚአብሔር ቤት በመግባት ካህናት ብቻ እንዲበሉት ከሚፈቀደው ህብስት መብላቱን ተናገረ፡፡

ይህንን በማድረግ ኢየሱስ ፈሪሳውያን በረዥም ዘመናት መካከል ህግን በህግ ላይ ባህልን በባህል ላይ በመከመር ሰንበት ከተፈጠረበት ደስታ ወደ ሸክምነት እንዲቀየር ማድረጋቸውን





ጠቆመ፡፡

*ሁለተኛው ታሪክ በሉቃስ 6፡6-11ን ያንብቡ፡፤ በዚህ ሥፍራ ደግሞ ስለ ሰንበት ምን ትምህርት እናገኛለን?*

ምንም እንኳን ሁሉም ወንጌላት የዚህን ታሪክ ነገር ያተቱ ቢሆንም የሰውየው የሰለለች እጅ ቀኝ መሆኑን የሚነግረን ሉቃስ ብቻ ነው፡፡ የዶ/ር ሉቃስ ተጨማሪ ዝርዝር ፤ ሰውዬው በእጁ መስለል ምክንያት በመደበኛው የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ያሳደረበትን የከፋ ተፅዕኖ እንድንረዳ ይጠቅመናል፡፡ ይህ ወቅት ሁለት ምላሾችን ቀስቅሷል ፤ የመጀመሪያው ፈሪሳውያን ኢየሱስን ሰንበትን ሽሯል ብለው ክስ እንዲያቀርቡ ሁለተኛ ኢየሱስ ልባቸውን በማንበብ እርሱ ራሱ የሰንበት ጌታዋ መሆኑንና እርሱ የሰንበት ፈጣሪ በመሆኑ ከዚህ በኃጢአት በሽታ ከተመታችው ዓለም ውስጥ እሥረኞችን ነፃ የማውጣት ተልዕኮውን ቻል እንደማይል አሳየ፡፡ ስለዚህም የሰንበትን አጠባበቅ በመለኮታዊ አመለካከት ሲያስቀምጠው በሰንበት ቀን መልካም ማድረግና ነፍስን ማዳን በህግ የተፈቀደ ነው (ሉቃስ 6፡ 9-11)

*እነዚህ መሪዎች እነርሱ ከእግዚአብሔር እንደ ተሠጠ በሚቆጥሩት ነገር ግን በራሳቸው ህጎችና ድንጋጌዎች ምክንያት ምን ያህል የታወሩ መሆናቸውን ያስቡ፡፡ እኛስ በተመሳሳይ ሁኔታ ባህልንና የሰውን ትምህርቶች በህይወታችን በመፍቀድ ወጥመድ ውስጥ ገብተን ጥልቅ የሆኑትን መለኮታዊ እውነቶች እንዳናይ አለመታወራችንን እርግጠኛ የምንሆነው እንዴት ነው?*

__________________________________________________________

__________________________________________________________

**ሐሙስ** ሚያዚያ 22 2007 ዓ.ም

# ሰንበት ከህመምተኛ፣ ከበሬና ከአህያ ጋር ሲነፃፀር

ከሦስቱ ዋና ወንጌሎች እነዚህን ሁለት የሰንበት ዕለት ፈውሶች የዘገበው ሉቃስ ብቻ ነው (ሉቃስ 13፡ 10-16 ፤ 14 1-5) የመጀመሪያው የምኩራቡ አለቆች በክርስቶስ ላይ እንዲቆጡ አድርጓቸዋል፤ ሁለተኛው ደግሞ ፈሪሳውያንን ፀጥ አሰኝቷቸዋል፡፡ በሁለቱም ጊዜ የኢየሱስ ጠላቶች የተሳሳተ ትርጉማቸውን እርሱ የሰንበት ህግ ጥሷል ለማለት ተጠቅመውበታል፡፡

*ሉቃስ 13፡10-16 እና 14 ፡ 1-6 ን ያንብቡ ፡፡ በዚህ ሥፍራ በጣም ወሳኝ የሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ለማጣመም ቀላል እንደሆነ ለማሳየት ምን አስፈላጊ የሆኑ እውነቶች ተገልፀዋል?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ጎባጣ የነበረችዋን ሴት አስተውሏት፡፡ እርሷ በፈሪሳውያን ዘንድ በጣም ዝቅ ተደርጋ የምትታይ ነበረች፣ ህይወት ትርጉም የለሽ መሆኑ ይሰማት ዘንድና የማንኛውንም ሰው ትዕግሥት ሊፈታተን በሚችል መጠን ለ18 ዓመታት ያህል ጎባጣ ሆና ኖራለች፡፡ በመጨረሻም ራሷን በፍጹም ነፃ ለማድረግ አቅቷታል፡፡

ለእርሷም ሰማያዊ ፀጋ በአካል መጣላት ኢየሱስ ተመለከታትና ወደ እርሱ እንድትቀርብ ጠራት ትፈወስም ዘንድ ተናገራት፤ እጁንም በላይዋ ጫነባት "ከዚያም በቶሎ ቀና አለች" (ሉቃስ 13፡13) የ18 ዓመቱ ስቃይ በአንዴውኑ በፍጹም ሊጠፋ በማይችል ደስታ ተተካ፤ እርሷም "እግዚአብሔርን አመሰገነች" (ቁ. 13) ሉቃስ የተጠቀመው እያንዳንዱ ቁጥር የሴትየዋን ግምትና ክብር ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሲሆን የእርሷን ብቻ ሳይሆን ማንኛውም የተናቀ ሰው ቢሆን እንኳን ሊሠጠው የሚገባውን ግምትና ክብር ሰውየው ያለበት ማንኛውም ሁኔታ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ሊሆን እንደሚገባ የሚያሳይ ነበር፡፡

በሁለተኛው ተዓምር (ሉቃስ 14 1-6) ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት ቀን ወደ ፈሪሳዊው ቤት ለምሳ እየሄደ ሳለ በሆድ ህመም ይሰቃይ የነበረውን ሰው ፈወሰው፡፡ በቅርብ እየተከታተሉት ከነበሩት መሪዎች ተቃውሞ እንደሚገጥመው በመጠባበቅ ኢየሱስ ሁለት ጥያቄዎችን አነሳ፤ የመጀመሪያው የህግን ዓላማ የሚመለከት ሲሆን "በሰንበት መፈወስ ተፈቅዷልን" (ቁ. 3) ሁለተኛው ስለ ሰው ልጅ ግምት "ከእናንተ ማናችሁ ናችሁ በሬአችሁ ወይም አህያችሁ በሰንበት ቀን ጉድጓድ ቢገባ የማታወጡት" (ቁ. 5) እርሱ ለማንሳት የፈለገው ነጥብ ግልፅ ነበር፤ እንደ ሉቃስ ገለፃ ግን እነርሱ ለጥያቄው ምንም ምላሽ አልሠጡም፡፡ እነርሱ የእግዚአብሔርን ህግ መተላለፍ መስሎ በሚታያቸው ነገር ምክንያት ራሳቸው ፃድቅና ቅዱስ አድርጎ በማየት የከፋ ግብዝነት ውስጥ መሆናቸውን ክርስቶስ ገለጸ ፡፡ ምን ያህል ልንጠነቀቅ ይገባል





## ዓርብ ሚያዝያ 23 2007 ዓ.ም

**ለተጨማሪ ጥናት፡-** "እግዚአብሔር ለቅፅበት ያህል እንኳን እጁን ቢሰበስብ ሰው በጠፋ ነበር፡፡ እና ሰው ዳግም በዚህ ሰንበት መሥራት የሚገባው ነገር አለ፡፡ ለህይወት አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ተሣትፎ ሊያደርግ ይገባል ፤ ህሙማን ጥንቃቄ ሊደረግላቸው ግድ ነው ፤ ለተቸገሩት የሚያስፈልጋቸው ሊሠጥ ይገባል፡፡ በሰንበት ዕለት ሌሎችን ከሥቃይ ወይም ከመከራ ነፃ ለማድረግ ሥራ የማይሠራ ሁሉ ከህሊና ወቀሳ ነፃ አይሆንም፡፡ በእግዚአብሔር ቅዱስ ቀን የተሠራው ለሠው ነው፤ የምህረት ተግባራት ቀኑ ከተፈጠረበት ዓላማ ጋር ፍጹም የሆነ አንድነት (ስምምነት ) አለው ፡፡ እግዚአብሔር ህዝቡን በሰንበትም ሆነ በሌላ ቀን ነፃ ከሚወጣበት ጭንቀት ውስጥ ለአንድ ሰዓት እንኳን እንዲቆይ አይፈልግም" *Ellen G.White , The Desire of Ages P.207.*

ለአይሁዳውያን ከተሠጡት ተቋማት እንደ ሰንበት በሙላት እነርሱን በዙሪያቸው ካሉ ህዝቦች የሚለያቸው ሌላ ምንም አልነበረም፡፡ እግዚአብሔርም ሰንበትን መጠበቃቸው እነርሱ እርሱን የሚያመልኩ እንደሆነ የሚያሳይ አድርጎ ቀርጾታል፡፡ ይህም እነርሱን ከጣኦት አምልኮ የሚለያቸውና ከእውነተኛው አምላክ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማስታወሻ ምልክት ነው፡፡ ነገር ግን ሰንበትን በቅድስና ለመጠበቅ ሰዎች ራሳቸው መቀደስ አለባቸው፡፡ በእምነት በኩል የክርስቶስ ጽድቅ ተካፋዮች *ይሆናሉ፡፡ Ellen G.White , The Desire of Ages p. 207*

## የመወያያ ጥያቄዎች፡-

❶ *መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስና ስለ ሰንበት ያለው ግልጽነት አስደናቂ አይደለም? ነገር ግን እጅግ ብዙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ በአለም ዙሪያ ያሉ የቤተክርስቲያን ሰዎች የሰባተኛ ቀን ሰንበት ጽኑ አይደለም ወይም ሰንበትን መጠበቅ የህጋዊነት ትዕዛዝ ነው፤ መጠበቁ አስፈላጊ አይደለም ይላሉ፡፡ የማይናወጥ እምነትና የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ አስፈላጊ ስለመሆኑ ይህ የሚያስተምረን እንዴት ነው? እንደ አንድ ቅዱስ መሠረታዊ መመሪያ ብዙዎች ከፉኛ ተታለዋል፡፤ በማር. 13፡22 ኢየሱስ ምን ወሳኝ የሆነ እውነት ነው የሠጠን?*

❷ *ሰይጣን ሰንበትን ለማጥፋት ምን ያህል እንደሠራ ይመልከቱ፡፡ ሰንበትን ሙሉ በሙሉ ሸክም እንዲሆን በማድረግ ወይም ሁለመናውን ባዶ አስቀርቶ ሊሥጥ የተፈጠረበትን ዓላማና ትርጉሙን ለማጥፋት በመሪዎች ተጠቅሟል፤ ወይም ዳግም አሁንም እየተጠቀመ እንዳለው የቤተክርስቲያን መሪዎች የጥንት አይሁዳውያን ህግና ወግ ነው ብለው ትርጉም እንዲያሳጡት አድርጓል፡፡ ሰንበት የሰይጣን ጠላትነት ኢላማ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?*

❸ *ኢየሱስ "የሰንበት ጌታ ነው" (ሉቃስ 6፡5) ይህ ዓ.ነገር ለክርስቲያኖች በሰንበት ላይ ባላቸው አመለካከት ምን እንድምታ አለው?*





# 6ኛ ትምህርት

ሚያዝያ 24-30 2007 ዓ.ም

# በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ የሴቶች ሥፍራ

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት፡-** ሉቃስ 1፡39 -55 ፤ 2፡36 -38 ፤ 7፡11-17 ፤ 36-50፤ ሮሜ 10፡17 ፤ ሉቃስ 8፡1-3 ፤ 18 ፡ 1-8 ን ለዚህ ሳምንት ያንብቡ፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "በእምነት በኩል ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ ሴት ወንድ የለም፣ ባሪያ ጨዋ የለም ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ " *(ገላ. 3፡26-28)*

የሉቃስ ወንጌል አንዳንዴ የሴቶች ወንጌል ይባላል፡፡ ምክንያቱም በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ሴቶች የነበራቸውን ተሳትፎ እና ኢየሱስ የሴቶችን ችግር ለመፍታት እንዴት በጥንቃቄ ይሰራ እንደነበር የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ስለሚገልጽ ነው፡፡

ልክ በአሁኑ ዘመን በአንዳንድ ባህሎች እንደሚታየው በኢየሱስም ዘመን ለሴቶች የሚሠጠው ሥፍራ በጣም አነስተኛ ነበር፡፡ በጊዜው አንዳንድ አይሁዶች ባሪያ ፤ አረማዊ ወይም ሴት ሆነው ባለመፈጠራቸው እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር፡፡ የግሪክና የሮማውያን ማህበረሰቦች ሴቶችን ከዚህም በከፋ ሁኔታ ይመለከቷቸው ነበር፡፡ የሮማውያን ባህሎች እንዲያውም ገደብ የለሽ ክብረ-ቢስ የሆነ የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ሁሉ ይፈቅድ ነበር፡፡ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ሚስት የሚኖራቸው የሚያወርሷቸው ህጋዊ ልጆች እንዲኖሯቸው

ሲሆን ለሥጋዊ ፍላጎታቸው ማርኪያ የሚሆኑ ቅምጦች ነበሯቸው፡፡

ሴቶች ተጥለውና በክፉ ሁኔታ በሚስተናገዱበት ዘመን ላይ ክርስቶስ ሴቶችም በእውነት የአብርሃም ልጆች ናቸው የሚለውን መልካም ዜና ይዞ መጣ (ሉቃስ 13፡16) በዚያ ዘመን የነበሩ ሴቶች እነርሱም ከወንዶች ጋር እኩል እና ወንዶችም ሴቶችም በእግዚአብሔር እይታ አንድ ናቸው የሚለውን መልዕክት ኢየሱስ ሲናገር መስማታቸው እንዴት ደስ ተሰኝተው ይሆን፤ ዛሬም መልዕክቱ በዓለም ሁሉ ላሉ ሴቶች ተመሳሳይ ነው፤ እኛ ሁላችንም ወንዶችና ሴቶች በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ነን፡፡

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለግንቦት 1 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

## እሁድ ሚያዚያ 25 2007 ዓ.ም

# የኢየሱስን ምፃት በደስታ የተቀበሉ ሴቶች

የማዳንን ተልዕኮ እና የህዝቡን የመሲህ ተስፋ ለመፈጸም የእግዚአብሔር ልጅ የሰውን ሥጋ መልበስ ፤ ይህን ዓለማት የሚያደንቁትን ታላቅ ታሪክ ሴቶች እየሆነ የነበረውን ነገር በሙላት ባያስተውሉም ለዚህ አስደናቂ ለሆነው ክስተት የሠጡት ምላሽ፤ የተናገሯቸው ቃላት እምነታቸውንና በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ያላቸውን አድናቆት የሚገልፅ ነበር፡፡

ሉቃ 1፡39 -45 ያንብቡ፡፡ ኤልሳቤጥ ምንም እንኳን ያላት ማስተዋል በጉዳዩ ላይ አነስተኛ ቢሆንም፤ እየተፈፀመ ስለነበረው ታላቅ ክስተት የተናገረችው የእርሷን ማስተዋል የሚገልፀው እንዴት ነው?

ኤልሳቤጥ ከተናገረች በኋላ ማሪያም ደግሞ በራሷ ቃላት ተከተለቻት (ሉቃስ 1፡46-55) በብሉይ ኪዳን እነዚህ ቃላት ሙሉ ዓ.ነገር ሆነው ባይፃፉም እንደ መዝሙር የሚታወቁ ሲሆን ማሪያም የቅዱሳት መጻህፍት ጥሩ ተማሪና ለኢየሱስ እናትነት ብቁ እንደነበረች ያስታውቃል፡፡ የማሪያም መዝሙር በቃሉ ላይ ያላትን ዕውቀት ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር የነበራትንም ግንኙነት ያሳያል፡፡ ይህም ጌታዋና በነፍሷ እንዲሁም በእምነቷና በአብርሃም ተስፋ ላይ የተመሠረተ መታወቂያ ወይም መለያዋ ነበር፡፡





*ሉቃስ 2፡36-38ን ያንብቡ፡፡ በሃና የቤተ-መቅደስ ታሪክ ምን በጣም አስፈላጊ የሆኑ እውነቶች ተገለጡ ?*

ይጠበቅ የነበረው ተስፋ በኢየሱስ ፍጻሜን አገኘ፡፡ ይህች መበለት ተዓምራቱን አስተዋለች ከዚያ ጊዜም በመጀመር አዳኙን ወደ ቤተ-መቅደሱ ለሚመጡ ሁሉ ለመናገር የተገባ ተልዕኮዋ አደረገች፡፡ በዚህም የመጀመሪያ ሴት ወንጌላዊት ለመሆን በቃች፡፡

*እስቲ በዙሪያቸው ስለ ተገለጠው ታላቅ ክስተት እነዚህ ሴቶች የነበራቸውን መደነቅ ያስተውሉ፡፡ ልናውጅ ስለተጠራንበት ታላቅ እውነቶች በልባችን ውስጥ ያለውን መደነቅ ህያው ሆኖ እንዲቆይ ምን ማድረግ እንችላለን?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## ሰኞ ሚያዚያ 26 2007 ዓ.ም

# ሴቶችና የኢየሱስ የፈውስ አገልግሎት

በሉቃ 7፡11-17 ፤ በናይን ስለ ተደረገው ተዓምር ያንብቡ፡፡ ይህች የተቸገረች ባልቴት አሁን ደግሞ በብቸኛ ልጇ ሞት ምክንያት ሌላ መከራ አገኛት፡፡ እጅግ ብዙ ለቀስተኞች የኃዘንና የርህራሄ ጩኀት እያሰሙ አብረዋት ነበሩ፡፡ የብቸኛ ልጇ ሞትና ወደፊት የሚሆነው ምን እንደሆነ አለማወቋ ይህችን ባልቴት ሁለመናዋ ተስፋ የቆረጠችና ኃዘንተኛ እንድትሆን አድርጓል፡፡

ነገር ግን ከከተማው ወደ ውጪ ይወጡ የነበሩ ተጓዦች ወደ ውስጥ ሊገቡ ከሚመጡ ተጓዦች ጋር ተገናኙ፡፡ ወደ ውጪ በሚወጡ ተጓዦች ራስ ላይ የሬሳ ሳጥን ነበር፡፡ ወደ ውስጥ ከሚገቡ ተጓዦች ጋር ግን ከታላቁ ፈጣሪ የተነሳ ህይወት ነበር፡፡ ተጓዦቹ ሲገናኙ ኢየሱስ በኃዘን የተሞላችውንና ተስፋ የቆረጠችውን ባልቴት ተመለከተ፡፡"አታልቅሺ" ከሚለው ትዕዛዝ በስተጀርባ ኃዘኗን ሊያስወግድ የሚችል ኃይል ነበር፡፡ ኢየሱስም ወደ ሬሳው ቀርቦ ነካውና ወጣቱን እንዲነሳ አዘዘው፡፡ ሬሳ መንካት (ዘሌ. 19፡11-13) በሜዳዊ ሥርዓት የሚያረክስ ቢሆንም ለኢየሱስ፣ ርህራሄ ከሥርዓቶች ይልቅ አስፈላጊው ነበር፡፡ የሰዎችን ፍላጎት ማሟላት ሥርዓቶች ከሚጠይቁ መስፈርቶች ይልቅ አንገብጋቢ ጉዳይ

ነው፡፡

የናይን መንደር ህዝቦች አስደናቂ ለሆነው ተዓምር ምሥክሮች ብቻ ሳይሆኑ በኢየሱስ ዘንድ ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች አስጨናቂ ስሜት ልዩነት ወይም የሚጋጭ ምንም ነገር እንደሌለው አስደናቂ መልዕክት ተቀብለዋል፡፡ ኢየሱስ በመገኘቱ የሞትን ኃይል ፊት ለፊት ገጠመው እንዲሁም ስህተት መሆኑን አረጋግጦ ረታው፡፡

ሉቃስ 8፡41 ፤ 42 ፤ 49-56ን ያንብቡ፡፡ ኢያኢሮስ፤ ታዋቂ የምኩራብ አለቃ እንዲሁም የቤተ-መቅደስ አገልግሎት ኃላፊ ነበር፡፡ እርሱ በእያንዳንዱ ሰንበት የሚመራ፣ ጥቅስ የሚያነብ፣ የሚፀልይና የሚሰብክ ሰውን ይመርጥ ነበር፡፡ እርሱ ታዋቂና ተፅዕኖ የሚያሳድር ብቻ ሳይሆን ሀብትም ኃይልም ያለው ሰው ነበር፡፡ ልጁንም በጣም ይወዳት ስለነበር እንዲፈውስለት ወደ ኢየሱስ ለመምጣት አልተጠራጠረም፡፡

*በእነዚህ ታሪኮች የምተውን ልጅ ወደ እናቱ እቅፍና የምትችውን ልጅ ወደ አባቷ እቅፍ የመለሰው የኢየሱስ ኃይል ነው፡፡ ይህ ድርጊት በጊዜው ለተመለከቱት በተለይም ለወላጆች ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ያስተውሉ፡፡ እነዚህ ታሪኮች ስለ እግዚአብሔር ኃይል ምን ይነግሩናል? ኃይሉን ለማስተዋል ምን ያህል ውስን እንደሆንን ምን ይነግሩናል? (እንዲያውም ሳይንስ እነዚህ ነገሮች እንዴት እንደሚፈጠር ፍንጭ ካሳየን በኃላ እንኳ)፡፡ እኛ አሁን ያለንበት ሁኔታ ከግንዛቤ ሳይገባ በእግዚአብሔር ኃይልና መልካምነት መተማመንን ለመማር ምን ማድረግ አለብን?*

________________________________________________________________

________________________________________________________________

## ማክሰኞ ሚያዚያ 27 2007 ዓ.ም

# የሴቶች እምነትና ውለታ

በሉቃ 7፡36-50፤ ኢየሱስ ግብዣውን ኃጢአተኛ ለነበረችው ሴት ክብርን ወዳጎናፀፈው መንፈሳዊ ክስተት ለወጠው፡፡ ስምዖን፤ የሀገሪቱ ዜጋ እና መሪ ፈሪሳዊ ኢየሱስን ለምሳ ጋበዘው፡፡ ለግብዣው የተጠሩት በጠረጴዛው ዙሪያ ተቀምጠው ሳለ ድንገት መራበሽ ተፈጠረ፤ "በከተማው የታወቀች ኃጢአተኛ ሴት" (ቁ. 37) ቀጥ ብላ በፍጥነት ወደ ኢየሱስ





በመቅረብ ውድ የሆነውን የአልበስጥሮስ ሽቶ ብልቃጥ በመስበር ራሱን ቀባችው ፤ በእግሩም ሥር በመስገድ እግሩን በእንባ አጠበችው፡፡

*ከሴትዮዋ ውለታ አመላለስና ኢየሱስም የእምነት ተግባሯን ከመቀበሉ ምን ትምህርት እናገኛለን?*

________________________________________________________________

________________________________________________________________

"ለሰብዓዊ ሰው አይን የማሪያም ጉዳይ ተስፋ የለሽ ቢሆንም ኢየሱስ ግን በእርሷ ለመልካም የሚሆን አቅም ተመለከተ፡፡ እርሱ መልካም ባህሪይን አየ የማዳን ዕቅዱ ለሰው ልጆች ብዙ አማራጮችና መንገዶች ያሉት በመሆኑ እነዚህ ሰፊ ዕድሎች በማሪያም ህይወት እውን ሆነዋል፡፡ በፀጋው አማካይነት እርሷ የሰማያዊው ባህሪይ ተካፋይ ሆነች... ከትንሣኤው በኋላም ማሪያም በኢየሱስ መቃብር ቦታ የተገኘች የመጀመሪያዋ ሴት ነበረች፡፡ የክርስቶስ የአዳኙን ትንሣኤ የተናገረች የመጀመሪያዋ ሴት ነበረች፡፡

በሉቃስ 8፡43-48፤ በጣም ከፉኛ ጨቋኝ የነበረው ሁኔታ ለአዳኙ ታላቅ ክብር የሚያመጣ ሆነለት፡፡ ለብዙ ጊዜ ይህች ሴት ነፍሷንና አካሏን ያወደመው አደገኛ በሽታ ነበረባት፡፡ የዚህ የ12ቱ ዓመት መከራ መጨረሻ ገደማ በድንገት የተስፋ ጭላንጭል በልቧ ፈነጠቀ፤ "ስለ ኢየሱስ ሰማች" (ማር. 5፡ 27)

የሰማችው ምንድን ነው ? የሰማችው ጥቂት ይሁን ብዙ አናውቅም፡፡ ነገር ግን የሰማችው ኢየሱስ ለድሆች መጠንቀቁን ማህበረሰቡ የናቃቸውን ማቀፉን ፤ ለምጻሞችን መንካቱን ፤ ውኃን ወደ ወይጠጅ መለወጡን፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ተስፋ የቆረጡትን የሚንከባከብ መሆኑን ሰማች፡፡ ነገር ግን መስማት በቂ አይደለም ወደ እምነት ሊመራ ይገባዋል፡፡(ሮሜ 19፡17) እናም ያ እምነት የቀሚሱን ጫፍ ወደ መንካት ቀላል ድርጊት መራት፡፡ቀሚሱን የመንካቱ ድርጊት በእምነት የተመራ ዓላማ ያለው ፍቱን መድኃኒት እና በክርስቶስ ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር፡፡ ይህን የመሰለ እምነት ብቻ ነው የአዳኙን ቡራኬ ሊቀበል የሚችለው "እምነትሽ አድኖሻል" (ሉቃስ 8፡48)

*ወደ ሰዎች ማየትና እነርሱ ላይ መፍረድ ቀላል አይደል? ምንም እንኳን ከአፋችን ባናወጣውም በልባችን እንፈርድባቸዋለን ያም ቢሆን ትክክል አይደለም፡፡ በሀሳባችን*

*እንኳን ቢሆን በሌሎች ላይ መፍረድን ልናቆም የምንችለው እንዴት ነው? እኛ በእነርሱ ሥፍራ ብንሆን ምን እናደርግ እንደሆነ ማን ያውቃል?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ረቡዕ** ሚያዚያ 28 2007 ዓ.ም

# ኢየሱስን የተከተሉ ጥቂት ሴቶች

*ሉቃስ 10፡38-42 ያንብቡን፡፡ ከዚህ ታሪክ ምን አስፈላጊ መንፈሳዊ እውነት እናገኛለን? (ሉቃስ 8፡14ን ለራሳችን እናንብበው)*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

እንደ አገልጋይ ማርታ በብዙ ትታወካለች (ሉቃስ 10፡40) እናም ለእንግዶች የተሻለውን ለማድረግ በጣም ትሮጣለች፡፡ ነገር ግን "ማሪያም በኢየሱስ እግር ሥር ተቀምጣ ቃሎቹን ትሰማለች፡፡ " (ቁ. 39) ስለዚህም ማርታ ትመጣና ከባድ ሥራ ሁሉ ለእሷ ብቻ የተተወ መሆኑን ለኢየሱስ ነገረችው፡፡ ኢየሱስም ማርታ ለመስተንግዶ ቅድሚያ በመስጠትዋ ሳይወቅሳት ነገር ግን በህይወታችን ቅድሚያ መስጠት ለሚገባን ነገር ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባን ጠቁሟል፡፡ ከኢየሱስ ጋር ህብረት የመጀመሪያው ሲሆን አብሮ መብላት ተከትሎ ሊመጣ ይገባል፡፡

"የክርስቶስ ሥራ ጠንቃቃና ጉልበት ያላቸው ሠራተኞችን ይፈልጋል፡፡ ለእነማርታ የሚሆን በቅንነት ንቁ የሆነ ሃይማኖታዊ ተግባር ሊፈጽሙ የሚችሉበት ሠፊ መስክ አለ፡፡ ነገር ግን መጀመሪያ ከእነ ማሪያም ጋር በኢየሱስ እግር ሥር ይቀመጡ፡፡ ትጋት ንቃትና ኃይል በክርስቶስ ፀጋ ይቀደሱ፤ ከዚያም ህይወት መልካም ነገርን በማድረግ የማትሸነፍ ትሆናለች፡፡ *"Ellen G.White , The Desire of Ages, p. 525.*





*ሉቃስ 8፡1-3፣ 55፣ 56፤ 24፡1-12 ን ያንብቡ፡፡ እነዚህ ቁጥሮች በክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ ሴቶች ስለነበራቸው ሚና ምን ይነግሩናል?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ክርስቶስ አገልግሎቱ እየሠፋ በሄደ ጊዜ "እየሰበከና እያስተማረ በየከተማውና በየመንደሩ ይሄድ ነበር" (ሉቃስ 8፡1) 12ቱ ደቀመዛሙርትም አብረውት ይሄዱ ነበር፡፡ ሉቃስ የሱስ የፈወሳቸው በስብከቱ ልባቸው የተነካ እናም ሀብታም የነበሩ አንዳንድ ሴቶች በታላቁ የአገልግሎት ጊዜ ተከትለውት እንደነበር ታላቅ ምስክርነትን ዘግቧል፡፡ ሉቃስ ከሚጠቅሳቸው አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ከክፉ መናፍስነት ነፃ የወጡ መግደላዊት ማርያምን ጨምሮ
2. የሄሮድስ የገንዘብ አስተዳዳሪ የሆነችው የኩዛ ሚስት ዩሐና
3. ሶስናና ሌሎችም እርሱን ያገለገሉ ይገኙበታል፡፡ (ቁ. 3)

*ኢየሱስ ለሰብዓዊ ዘር ሁሉ መሞቱን ስናስተውል ፤ በእግዚአብሔር ፊት ሰው ሁሉ እኩል መሆኑን በተሻለ ሁኔታ እንረዳለን፡፡ ይህንን እውነት ለሌሎች በምናሳየው ባህሪያችን በጥሩ ሁኔታ ልናሳይ የምንችለው እንዴት ነው? ይህም ማለት አስፈላጊ ከሆነ ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማየትንና ራሳችን ከሌሎች የምንሻል አድርገን ማየት የምናስወግደው እንዴት ነው?*

**ሐሙስ** ሚያዚያ 29 2007 ዓ.ም

# በፀሎት መፅናት በመስዋዕትነት መሰጠት

ሉቃስ፣ ኢየሱስ አስፈላጊ የሆኑ መንፈሳዊ እውነቶችን ለማስተማር ወደ ሁለት መበለቶች መለስ ማለቱን ያሳየናል፡፡

በመጀመሪያ ጉዳይ (ሉቃስ 18፡1-8) ኃይለኛ በሆነ ፈራጅ ፊት ፍትህ ፍለጋ ስለተመላለሰችው ደሃና ደካማ መበለት ራራላት፡፡ እርሷም የፍትህ መጓደልና የማጭበርበር ሰለባ ነበረች፤ ሆኖም ግን በህግ የበላይነትና በፍትህ ታምን ነበር፡፡ ነገር ግን ዳኛው ሰውንም እግዚአብሔርንም የማይፈራ በመሆኑ ሊረዳት ግድ አልሠጠውም፡፡ ባልቴቶችን መርዳት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መጠይቅ ነው:: (ዘፀ. 22፡22-24 ፤ መዝ. 68፡5 ፤ ኢሳ. 1፡17 ) ነገር ግን ዳኛው ህግን ቸል በማለት ተደሰተ:: ይህች ሴትም አንድ መሣሪያ ነበራት በእርሱም ዳኛውን በማዳከም ፍትኋን አገኘች እርሱም ትዕግሥት እና ፅናት ነው::

ይህ ምሳሌ ሦስት አስፈላጊ የሆኑ ትምህርቶችን ያስተምረናል:: **1.** ተስፋ ሳይቆርጡ መፀለይ (ሉቃስ 18፡1) **2.** ፀሎት ነገሮችን እንደሚለውጥ ከፉውን ዳኛ ሳይቀር **3.** ፅኑ እምነት አሸናፊ እምነት ነው :: እውነተኛ እምነት ለእያንዳንዱ አማኝ ዘላለማዊ ምክር አለው፤ ምናልባትም የመጨረሻው ነፃ መውጣት በእግዚአብሔር ልጅ መገለጥ ጊዜ የሚሆን እንኳ ቢሆን ተስፋ አትቁረጡ (ቁ. 8)

በሁለተኛው ጉዳይ (ሉቃስ 21፡1-4 ፤ ማር. 12፡41-44)፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የፀሐፊዎችን ጉራ እና አለሁ አለሁ ባይነት በቤተ-መቅደስ ዙሪያ ያሉትን መሪዎች የሃይማኖት ግብዝነት ማውገዝ እንዲቀር አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ ትህትና ከተሞላበት የደሃዋ መበለት ኃይማኖት ጋር አወዳደረ::

ኢየሱስ አንዳንዶቹን የሃይማኖት መሪዎች "የመበለቶችን ቤት የሚቀሙ (ሉቃስ 20፡47) እና በመጽሐፍ ቅዱስ ለመበለቶች እንዲጠነቀቁላቸው የተሠጣቸውን ኃላፊነት የሚተላለፉ እንደሆኑ ገልጿል:: ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ ብዙዎች ጥሩ ለመምሰል ፤ እና ይህ ደግሞ የከፋ የሚሆነው የሰጡት ከተረፋቸው ሀብት ላይ ነው:: ሥጦታቸው እውነተኛ የግል መስዋዕትነትን የሚያሳይ አልነበረም:: ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ-መዛሙርቱ መበለቷን የእውነተኛ ሃይማኖት ምሳሌ አድርገው እንዲወስዱ ጠየቃቸው ፤ ምክንያቱም እርሷ ያላትን ሁሉ ሰጥታለችና::

የመጀመሪያው ግሩፕ የሥጦታው መነሻ ታይታ ሲሆን የመበለቷ ሥጦታ መነሻ የእግዚአብሔር ክብርና መስዋዕትነት ነበር:: መበለቷን ያላትን ሁለት ዲናር እንድትሰጥ ያስገደዳት እግዚአብሔር ያላት ነገር ሁሉ ባለቤት መሆኑን መቀበሏና ባላት ሁሉ እርሱን ማገልገል እንዳለባት ማስተዋሏ ነበር:: ሁሉን በሚችል ፈጣሪ ዓይኖች ዋጋ ያለው የምንሠጠው ነገር ሳይሆን ለምን እንደምንሰጥ የመነሻ ሀሳባችን ነው፤ የምንሠጠው መጠን ሳይሆን ለመስጠት ያለን መስዋዕትነት ነው::





*ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ሰዎች ሲሉ ምን ያህል መስዋዕትነት ይከፍላሉ?*

__________________________________________________

__________________________________________________

## ዓርብ ሚያዚያ 30 2007 ዓ.ም

**ለተጨማሪ ጥናት:-** እርሱ " በመስቀል ላይ በጭንቀት ተሰቅሎ እያለ እናቱን ያስታወሰው ፤ ሲያለቅሱ ለነበሩ ሴቶች በመገለጥ የመጀመሪያውን የአዳኙን ከሞት የመነሳት አስደሳች ዜና እንዲያውጁ መልዕክተኞች ያደረጋቸው ፤ ዛሬም ሴትን ለመርዳት የሚችል በህይወት ጉዳዮቿ ሁሉ ሊረዳት ፈቃደኛና መልካም ወዳጅ ነው::"

"ጌታ ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች ሥራ አለው:: እርሱ በእነርሱ ሥራውን እንዲሰራ በዚህ ችግር ውስጥ ሥፍራቸውን መያዝ አለባቸው:: መሥራት በሚገባቸው ነገር ላይ ቢመሰጡና በመንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ ሥር ተግባራቸውን ቢያከናውኑ በዚህ ዘመን የሚፈለጉ ራሳቸውን የሚቆጣጠሩ መሆን ይችላሉ:: በእነዚህ ራሳቸውን መስዋዕት በሚያደርጉ ሴቶች ላይ የእርሱን ፊት ብርሃን ያበራላቸዋል:: እናም ከወንዶች የሚበልጥ ኃይል ይሰጣቸዋል:: እነርሱ በቤተሰብ ውስጥ ወንዶች የማይሠሩትን ወደ ውስጣዊ ህይወት የሚገባ ሥራ መሥራት ይችላሉ:: ወንዶች ሊደርሷቸው ወደማይችሏቸው ልቦች ተጠግተው መሥራት ይችላሉ:: የእነርሱ ሥራ ተፈላጊ ነው:: *Ellen G. White , Evangelism p. 464 : 465*

# የመወያያ ጥያቄዎች

1. *ሉቃስን ጨምሮ የወንጌላት ሁሉ አስደሳች ነገር የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በሚመለከት የሴቶችን ሚና ይናገራሉ:: በሁሉም የወንጌል ታሪኮች የተነሳውን አዳኝ በማየትም ዜናውን በመናገርም የመጀመሪያዎቹ ሴቶች መሆናቸውን ይናገራሉ:: የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች ይህንን እውነታ ለክርስቶስ በሥጋ ትንሣኤ መነሳት ጥያቄ ለሚያቀርቡና ለሚጠራጠሩ መተማመኛ እንዲሆናቸው ሲጠቀሙ ኖረዋል:: በዚህ ሥፍራ የሴቶቹ ሚና አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን*

*ነው?አንዳንዶች እንደሚናገሩት የክርስቶስ ትንሣኤ በጸሐፊዎች የተፈጠረ ከሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ብዙም ሥፍራ የሌላቸውን ሴቶች የታሪኩ አካል ማድረግ ለምን አስፈለገ? እነርሱ ይህንን ታሪክ በዚያን ዘመን ሰውን ለማግኘት ፈልገው የፈጠሩት ከሆነ ለምን ሴቶችን ከወንዶቹ በተለየ መልኩ ተጠቀሚቸው ተወያዩበት፡፡*

❷ *በማንኛውም ሁኔታ ለሴቶች ትኩረት በማይሰጥ ማህበረሰብ ውስጥ ኢየሱስ በፍጥረቱ ጊዜ የሠጣቸውን ደረጃ ሰጣቸው፤ እነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች የአብርሃም ሴቶች ልጆች እንዲሁም በአዲሱ የወንጌል ዘመን ከወንዶቹ ጋር እኩል ናቸው፡፡ የሴቶችንና የወንዶችን እኩልነት በእግዚአብሔር ፊት የምናረጋግጠው እንዴት ነው? ነገር ግን ያሉትን ልዩነቶች ተቀብለናቸው ሥፍራ ሰጥተን በቤተክርስቲያን ህይወት ውስጥ ሚና እንዲኖራቸው የምናደርገው እንዴት ነው?*





# 7ኛ ትምህርት

ግንቦት 1-7 2007 ዓ.ም

# ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስና ፀሎት

**ሰንበት ከሰዓት**

ለዚህ ሳምንት ጥናት፡- ሉቃስ 2፡25 -32 ፤ ዮሐ. 16፡5-7 ፤ ሉቃስ 23፡46 ፤ ሉቃስ 11፡ 1-4 ፤ ማቴ. 7፡21 – 23 ፤ ሉቃስ 11፡9-13 ያንብቡ፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "እኔም እላችኋለሁ ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያውን እንኳኩ ይከፈትላችኋል፤ የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልግም ያገኛል መዝጊያውንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል፡፡" *(ሉቃስ 11፡9-10)፡፡*

ኢየሱስ ክርስቶስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስላለው ህብረት ከሦስቱ ዋና ዋና ወንጌላት የበለጠ የሚናገረው ሉቃስ ነው፡፡ ማቴዎስ ስለ መንፈስ ቅዱስ 12 ጊዜ ፤ ማርቆስ 6 ጊዜ ፤ እና ሉቃስ በወንጌሉ 17 ጊዜ ሲጠቀስ በሐዋሪያት ሥራ ደግሞ 57 ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ የኢየሱስን ሰብዓዊነት ከተፀነሰበት (ሉቃስ 1፡35) ዓለምአቀፍ ተልዕኮውን እስከመሠረተበት ትዕዛዝ (ሉቃስ 24፡ 44-49)ድረስ ሉቃስ በኢየሱስና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ተልዕኮውን ለመፈጸም የሚያስችል ግንኙነት እንደሚታይ አድርጎ ይገልፃል፡፡ የእነርሱ ህብረትም የአዳኙን አገልግሎት ለማስተዋል መሠረታዊ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እኩል ሙሉ በሙሉ መለኮታዊ የሆነ

ኢየሱስ፤ ፀሎትን በሚመለከት በሰብዓዊነቱ ለእኛ ምሳሌ ትቶልናል፡፡

*ኢየሱስ የፀሎትን አስፈላጊነት በዚህ ሁኔታ ካየው እኛ ምን ያህል ያስፈልገን ይሆን?*

"ነቅተን የማንጠብቅ እና ሳናቋርጥ የማንፀልይ ከሆነ ከእውነተኛው መንገድ ላይ ዞር ወደ ማለት አደጋ እንገባለን፡፡ ጠላት ሳያቋርጥ እኛ ፈተናን ለመቋቋም እንድንችል፤ በነቃ ፀሎትና ልመና ኃይልንና ፀጋን እንዳናገኝ ሳናቋርጥ ወደ ምህረት መቀመጫ እንዳንቀርብ ያደናቅፈናል፡፡"

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለግንቦት 8 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

## እሁድ ግንቦት 2 2007 ዓ.ም

# ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ

ከአህዛብ ወደ ክርስትና የመጣ እና የጳውሎስ የወንጌል ተልዕኮ ባልደረባ እንደመሆኑ ሉቃስ የክርስቶስን ትምህርት ከመፀነሱ እስከ መወለዱ እስከ ቤተክርስቲያን መስፋፋት ድረስ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የመጣ መለኮታዊ ድንቅ መሆኑን አስቀምጧል፡፡ በኢየሱስ ህይወት ውስጥ ለመዳናችን ሦስቱም ሥላሴዎች በሥራ ላይ መሆናቸውን እናያለን፡፡ (ሉቃስ 3፡21.22)፤ እናም ሉቃስ ይህንን ነጥብ ሳያቋርጥ ትኩረት ሰጥቶ ይጠቅሰዋል፡፡

*የሚከተሉት ጥቅሶች ክርስቶስ በሥጋ ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምን እንደነበር የሚገልጹልን እንዴት ነው? ሉቃስ 1፡35 . 41 ፤ 2፡ 25 -32፡፡*

________________________________________________________

________________________________________________________

የኢየሱስ ክርስቶስ ተልዕኮ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተወሰኑ መግለጫዎችን በመስጠት ነው፡፡ እንደ ሉቃስ አቀራረብ መጥምቁ ዮሐንስ ምንም እንኳን እርሱ ያጠምቅ የነበረው በውኃ ቢሆንም ከእርሱ በኋላ የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ ተናግሮ ነበር፡፡ (ሉቃስ 3፡16) በኢየሱስ ጥምቀት ጊዜ ሁለቱም አባትና መንፈስ ቅዱስ የእርሱን የደህንነት





ተልዕኮ ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡ እግዚአብሔር አባት ከላይ ኢየሱስ የምወደው ልጄ መሆኑን እና የሰውን ዘር ለማዳን የተላከ መሆኑን አውጇል፡፡ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል በላዩ አርፏል፡፡ (ሉቃስ 3፡21.22) ከዚያ ጊዜ ጀምሮ "ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ" (ሉቃስ 4፡1) እናም ጠላትን በምድረበዳ ሊገጥመውና አገልግሎቱንም ልጀምር በመንፈስ ቅዱስ ተቀባ (ሉቃስ 4፡14)፡፡

በናዝሬት ምኩራብ የነበረው የአገልግሎቱ መክፈቻ መልዕክት ኢሳያስ ስለ መሲሁ የተናገረው በራሱ ላይ መፈጸሙን የሚያሳይ ነበር፡፡ "የእግዚአብሔር መንፈስ በላዬ ነው" (ቁ. 18) መንፈስ ቅዱስ የማያቋርጥ ወዳጁ የጥንካሬው ማረጋገጫ እንድሁም እርሱ ከደቀመዛሙርቱ ጋር አብሮ በማይሆንበት ጊዜም አብሮአቸው የሚቆይ ነበር፡፡ (ሉቃስ 16 5 -7) ይህም ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር ለሚጠይቁት የመንፈስ ሥጦታ እንደሚሠጥ ተስፋ ሰጥቷል፡፡ (ሉቃስ 11፡13) ኢየሱስ በማዳን ተልዕኮው ሁሌም ከአባቱ ጋር ያስተሳሰረው ያው መንፈስ ቅዱስ በእምነት ጉዞአቸው ወቅት ደቀ-መዛሙርቱን ያጠነክራቸዋል፡፡ ስለዚህ በክርስቲያን ህይወት መንፈስ ቅዱስ ወሳኝ ነው፡፡ በእርግጥ መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ከሁሉ የከፋ ኃጢአት ነው (ሉቃስ 12፡10)

*እኛ ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ክፍት የምናደርግባቸው ተግባራዊ መንገዶች ምንድን ናቸው? እኛ በምርጫዎቻችን ልባችንን ለእርሱ ጥሪ እንዳናደነድን የምንጠነቀቀው እንዴት ነው?*

________________________________________________________

________________________________________________________

## ሰኞ ግንቦት 3 2007 ዓ.ም

# የኢየሱስ የፀሎት ህይወት

ኢየሱስ ከፀለየባቸው ብዙ ጊዜያት መካከል ጥቂቶቹ የተፃፉት በሉቃስ ወንጌል ብቻ ነው፡፡ ኢየሱስ በህይወቱ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ጊዜያት መካከል የሚከተሉትን አጢኗቸው፡፡

1. በጥምቀቱ ጊዜ ኢየሱስ ፀልየዋል (ሉቃስ 3፡2) "አዲስና እጅግ አስፈላጊ የሆነ ዘመን ከፊቱ እየተጀመረ ነበር፡፡ የዚያን ጊዜ ጌታችን በህይወቱ ወደ ተጋድሎ

የሚገባበት ሰፊ መድረክ ላይ ነበር፡፡" *Ellen G. White , The Desire of Ages , P.111* ይህ ሰፊ የሆነው ህዝብን የሚያገልገልበት መድረክ ያም ወደ ጎልጎታ መስቀል የሚያመራውን ያለ ፀሎት ለመጀመር አልደፈረም፡፡

2. ኢየሱስ 12ቱን ደቀ-መዛሙርት ከመምረጡ በፊት ፀልየዋል (ሉቃስ 6፡ 12-13) ማንኛውም መሪ ተከታዮቹን ያለምንም ዕቅድ ተነስቶ አይመርጥም፡፡ ኢየሱስ ይመርጥ የነበረው ዝም ብሎ ተከታዮቹን ሳይሆን በግልፅና ሙሉ በሙሉ የእርሱን ማንነትና ተልዕኮውን በትክክል የሚያስተውሉትን ነው፡፡ " እነርሱ የተጠሩበት ቢሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሰብዓዊ ዘር ከተጠራበት የተለየ ሲሆን ይህም ከኢየሱስ ክርስቶስ ከራሱ ጥሪ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የሚገኝ ነው"፡፡ *Ellen G. White , The Desire of Ages, p. 291*

3. *ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ፀልየዋል (ሉቃስ 9፡18) ደቀ-መዛሙርነት ፈጽሞ ራስን ለኢየሱስ ማስረከብንና የእርሱን ማንነት ማስተዋልን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ 12ቱ እርሱን እንዲያውቁ "ብቻውን ከፀለየ በኋላ እርሱ በጣም ወሳኝ የሆነ ጥያቄ ጠየቃቸው፡፡"እናንተ እኔን ማነው ትሉኛላችሁ?" (ሉቃስ 9፡20)*

4. ኢየሱስ ከመለወጡ በፊት ፀልዮል (ሉቃስ 9፡28-36) በዚህም ለራሱ የእግዚአብሔር የተወደደ ልጅ የመሆኑን ሁለተኛ ድጋፍ አግኝቷል፡፡ ስለዚህ በሩቅ ያለ መከራ እንዲሁም ሊመጣ ያለ ነገር በአባትና በልጅ መካከል ያለውን የጠበቀ ዝምድና አልለወጠውም፡፡ ፀሎቱ ዳግም ደቀመዛሙርት "ለታላቅነቱ የዓይን ምሥክር" እንዲሆኑ አድርጓቸዋል (2ጴጥ. 1፡16)

5. ኢየሱስ በጌተ-ሰማኔ ፀልየዋል (ሉቃስ 22፡39-46) ይህ ምናልባትም በማዳን ታሪክ ውስጥ እጅግ አስፈላጊው ነው፡፡ በዚህም አዳኛችን ሰማይንና ምድርን እያገናኘ ሲሆን ይህንንም ሲያደርግ ሦስት ወሳኝ የሆኑ መመሪያዎችን መሥርቷል፤ የእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ ቅድሚያ እንደሚገባው ይህን ቅድሚያ ለመተግበር የሚደረግ መሰጠት እስከ ደም መፍሰስና ሞት ድረስ እንደሆነ እና ፈተናን ለመቋቋምና የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማከናወን ብርታት ለማግኘት እንደሆነ ነው፡፡

6. ኢየሱስ ክርስቶስ ህይወቱን ለእግዚአብሔር አሣልፎ ለመስጠት ፀልየዋል (ሉቃስ 23፡46) በመስቀሉ ላይ ለመጨረሻ በተናገራቸው ቃላት "አባት ሆይ ህይወቴን አንተ ተረከብ" በማለት የመፀለይን ዋነኛ ዓላማ አሳይቷል፡፡ በውልደት ሆነ በሞት





በወዳጆቹም ሆነ በጠላቶች ፊት አንቀላፍተን ሆነ ነቅተን ፀሎት ከእግዚአብሔር ጋር ፅኑና ቀጣይ በሆነ ግንኙነት ሊያቆየን ይገባል፡፡

*እነዚህ ምሳሌዎች ስለ ራስዎ ፀሎት ምን ይነግርዎታል?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## ማክሰኞ ግንቦት 4 2007 ዓ.ም

# የፀሎት ተምሳሌት ክፍል 1

*ሉቃስ 11፡1- 4ን ያንብቡ፡፡ እነዚህ ጥቅሶች ፀሎት እንዴት እንደሚሠራ ለመረዳት እንዴት ይጠቅሙናል?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

"አባት" የሚለው መጠሪያ ክርስቶስ እግዚአብሔርን የሚገልፅበት መንገድ ሲሆን በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ለ170 ጊዜ ተዘግቧል፡፡ እግዚብሔርን አባት ብለን ስንጠራው እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ልዩ የሆነ የጠበቀ ግንኙነት መፍጠር የሚችል አካል መሆኑን እውቅና እየሠጠነው ነው፡፡ እግዚአብሔር እንደ አካላዊው የስጋ አባት እውነተኛ አፍቃሪና የሚጠነቀቅ ነው፡፡ እርሱ ሁሉን አዋቂ ለሁሉ የሚጠነቀቅ ነው፡፡ ነገር ግን እርሱ ሰማያዊ አባት ነው፡፡ እርሱ ሁሉን አዋቂ ሁሉን ቻይ በሁሉም ሥፍራ የሚገኝ እና በፍፁም ቅዱስ በመሆኑ ከምድራዊ አባት ይለያል፡፡

"ሰማያዊ አባት" የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር ቅዱስና ግላዊ እንደሆነ ለዘላለም ያሳስበናል፤ እናም ክርስትናም ሆነ ፍልስፍና ሁሉም ነገር አምላክ ነው፣ አምላክም ሁሉም ነገር ነው የሚል ተራ ነገር አይደለም፡፡

"ስምህ ይቀደስ" (ሉቃስ 11፡2) እዚህ ደግሞ የእግዚአብሔር ቅድስናና የተለየ መሆኑን የሚያሳይ ሌላ ማሳሰቢያ አለ፡፡ አምላክን እንከተላለን የሚሉ ሁሉ የእርሱን ስም በቃልም

ሆነ በተግባር ሊቀድሱት ይገባል፡፡ እንከተለዋለን እያሉ እርሱ ላይ ኃጢአት ማድረግ ስሙን ማርከስ ነው፡፡ በማቴ. 7፡21-13 ያሉት የኢየሱስ ቃላት ስሙን መቀደስ ማለት ምን እንደሆነ የበለጠ እንድናስተውል ይረዱናል፡፡

"*መንግሥትህ ትምጣ*"(ሉቃስ 11፡2) ወንጌሎች የእግዚአብሔር *መንግሥት* የሚለውን 100 ጊዜ ሲጠቅሱ 40 ጊዜ በሉቃስ ፤ 50 ጊዜ በማቴዎስ፤ 16 ጊዜ በማርቆስ እና 3 ጊዜ በዩሐንስ ወንጌል ተጠቅሷል ፡፡ ይህም የእግዚአብሔር *መንግሥት*፤ ኢየሱስ አሁን የፀጋውን *መንግሥት* እና በሚመጣው ጊዜ ደግሞ የክብር *መንግሥቱን* ለመግለጥና ለመመሥረት ሲል ነው ወደ ምድር የመጣው፡፡ ወደ መጀመሪያው *መንግሥት* ሳይገቡ ወደ ሁለተኛው መግባት የማይቻል ሲሆን የኢየሱስ ፍላጎት ደቀ-መዛሙርቱ ሁለተኛውን *መንግሥት* ወደፊት ተስፋ እያደረጉ ወደ መጀመሪያ *መንግሥት* እንዲገቡ ነው፡፡

"*ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን*" (ሉቃስ 11፡2) የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ ተቀባይነት ያለው እንዲሁም በሰማይ ያሉት የሚታዘዙለት ነው፡፡ ኢየሱስ ይህን ሰማያዊ እውነት ወደ ምድር በማምጣት ተመሳሳዩ ነገር በምድር እንዲሆን ተስፋ በማድረግ ነው፡፡ "በምድር" አጠቃላይ ቢመስልም በውስጡ ግላዊነትም አለበት፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር ትሁን ነገር ግን መጀመር ያለበት በእኛ በእያንዳንዳችን የግል ህይወት ነው፡፡

*አምላክን ታውቁታላችሁ? ወይስ ስለ እርሱ ሰምታችኋል? የግል የፀሎት ህይወታችሁ ወደ እርሱ ሊያስጠጋችሁ የሚችለው እንዴት ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

### ረቡዕ ግንቦት 5 2007 ዓ.ም

# የፀሎት ምሳሌ ክፍል ሁለት

"የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ" (ሉቃስ 11፡3)፡፡ ልመናው የሚጀምረው ስጠን በሚል ቃል ነው፡፡ ይህ ቃል ሚሊዮኖች ካሉት ሰው ይሁን ከወላጅ አልባ ልጅ አንደበት ቢወጣ፤ ፀሎቱ የሚያሳየው በእርሱ መደገፍንና በእምነትም እውቅና መስጠትን ነው፡፡ እኛ ሁላችን





በእግዚአብሔር የተደገፍን ነን፤ ይህ ስጠን የሚለው ልመናም እግዚአብሔር የሁሉም ነገር ወይም የሥጦታ ሁሉ ምንጭ መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡ እርሱ ፈጣሪ ነው፡፡ በእርሱ እንኖራለን፤ እንመላለሳለን ማንነታችንም በእርሱ ነው "እርሱ ሠርቶናል እናም በራሳችን አይደለንም" (መዝ. 100፡3)

እግዚአብሔር የምንፈልገውን ነገር ሁሉ የሚሠጠን አባት ነው በዚህ ተስፋ፤ በሉቃ 11፡ 9-13 ምን ዋስትና እናገኛለን?

"ኃጢአታችንን ይቅር በለን"(ሉቃ 11፡4) ይቅርታ የወንጌል ልብ ነው፡፡ ያለ እግዚአብሔር ይቅርታ እኛ መዳን አንችልም፡፡ "እናንተም በበደላችሁ. . . ሙታን በሆናችሁ ጊዜ ከእርሱ ጋር ህይወትን ሰጣችሁ በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ" (ቆላ. 2፡13) የእግዚአብሔርን ይቅርታ የተለማመዱ ሁሉ እጃቸውን በመዘርጋት የበደሏቸውን ሁሉ ሊያቅፉ ይገባል፡፡ ይቅር እንድንባል የምንጸልየው ፀሎት "የበደሉንን ይቅር እንደምንል"(ሉቃስ 11፡4) የእግዚአብሔር ይቅር ባይነት እኛ ሌሎችን ይቅር በማለታችን ላይ የተመሠረተ ነው ማለት አይደለም፡፡ ይልቅ እንደ ደቀ-መዝሙር ይቅር የማለታችን ደረጃ ክልሉ በፀጋ የሠፋ እንዲሆን እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቸርነት በአንድ በኩል ተቀብሎ በሌላው በኩል ደግሞ ፍቅሩንና ይቅርታውን እኛን ለበደሉን አሳልፎ መስጠት ማለት ነው፡፡

"ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ "(ሉቃስ 11፡4) ሁለት እውነቶች ትኩረት ያሻቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ፈተና ኃጢአት አይደለም፡፡ "ፈተና "ለሚለው የግሪኩ ቃል "ፓይራአስሞስ" *(Peirasmos)* ነው፡፡ አስሞስ *(Asmos)* በሚል የሚያበቁ የግሪክ ቃላት የሚገልጹት ሂደትን እንጂ ውጤትን አይደለም፡፡ ቅዱሳት መጻህፍት ፈተናን የመጨረሻ ውጤት አድርገው አያዩም፤ ነገር ግን ይህ ፈተና አንድ የተወሰነ ውጤት ለማግኘት ለሚደረግ ሂደትና አሠራር የሚጠቅም ነገር ነው፡፡ ምንም እንኳን ፈተና በራሱ ኃጢአት ባይሆንም ለእርሱ መረታት ግን ኃጢአት ነው፡፡ ሁለተኛ እግዚአብሔር የፈተና ጠንሳሽ አይደለም፡፡ (ያዕ. 1፡13) እግዚአብሔር ፈተና ይመጣ ዘንድ ይፈቅድ ይሆናል ይህንንም የሚያደርገው ወደ ኃጢአት እንድንሳብ ለማድረግ አይደለም፡፡ ፀሎቱ ታዲያ ፈተናን ለመቋቋም እግዚአብሔር ትክክለኛው የኃይል ምንጭ መሆኑን እውቅና መስጠትን ያመለክታል፡፡

*ሉቃስ 11፡ 1-4 ያለውን ይከልሱ፡፡ ጥቅሱ ስለሚሸፍናቸው ጉዳዮች በሙሉ ያስቡ፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች በሙሉ በፀሎት አማካይነት የተደላደሉና ሥር የሰደዱ መሆን የሚችሉት እንዴት*

*ነው?*

____________________________________________________________

_______________________________________________________

## ሐሙስ ግንቦት 6 2007 ዓዓም

# በፀሎት ተጨማሪ ትምህርት

ጌታችን ኢየሱስ ለደቀ-መዛሙርቱ የፀሎትን ምሳሌ ከሰጣቸው በኋላ የእኩለ ሌሊቱ ወዳጅ በሚለው ምሳሌ (ሉቃስ 11፡ 5-13) ተግቶ የመጸለይን አስፈላጊነት አስተምሯቸው ነበር፡፡

ከዚያም ወደ አገልግሎቱ መጨረሻ እየተቃረበ ሲሄድ ዮሐንስ ራሱን አዋርዶ የመጸለይን አስፈላጊነት አሳሰባቸው (ሉቃስ 18፡9-14) እነዚህ ሁለቱ ምሳሌዎች ፀሎት ዝም ብሎ ሃይማኖታዊ ድግግሞሽ ሳይሆን ከአባት ጋር የማያቋርጥ ጉዞ ንግግርና ህይወት ማለት መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

ሉቃስ 11፡5-8 ያንብቡ፡፡ ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ የተናገረው ያለ መሰልቸት መጸለይን ለማበረታታት ነው፡፡ ፀሎት ልማዳዊ ድግግሞሽ መሆን የለበትም፤ በምትኩ ፀሎት በእርሱ የመጽናት፣ የፍጹም ግንኙነት፣ እና በእርሱ የመደገፋችን መሠረት ሊሆን ይገባል፡፡ ፀሎት ያለ እርሱ በመንፈሳዊ ህይወት ልንኖር የማንችልበት የነፍሳችን እስትንፋስ ነው፡፡ ኢየሱስ ጎረቤትነቱን ስላልተቀበለ አንድ ጎረቤት ምሳሌ ተናገረ፡፡ ወዳጁ በእኩለ ሌሊት ባጋጠመው ሁኔታ ዳቦ እንዲሰጠው የለመነውን ልመና አቃለለው፡፡ ነገር ግን በመጨረሻ ይህ ጎረቤት እንኳን ያለማቋረጥ በሩ በእኩለ ሌሊት ይንኳኳ ስለነበር ተረትቷል፡፡ እግዚአብሔር ታዲያ ሳያቋርጥ ለሚፀልየው እንዴት ከዚህ የበለጠ አያደርግም? እንደዚህ ፀንቶ መፀለይ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማስቀየር ሳይሆን እኛ በእርሱ ላይ ያለንን መታመን ለማጠናከር ነው፡፡

*ሉቃስ 18፡ 9-14 ን ያንብቡ፡፡ በዚህ የሚገኝ ስለ ፀሎት ወሳኝ የሆነ ትምህርት ምንድን ነው?*

__________________________________________________________





ፈሪሳዊው እርሱ ራሱ በሠራቸው የፅድቅ ስራዎች እግዚአብሔር እንዲያፀድቀው ጠብቋል፡፡ ቀራጩ ግን ራሱን በእግዚአብሔር ምህረት ላይ በመጣል፤ በእግዚአብሔር ፀጋ ተቀባይነትን ለማግኘት ፀለየ፡፡ እግዚአብሔር እኛን የሚቀበለን በማንነታችንና በምንነታችን ሳይሆን በፀጋው ብቻ ነው፡፡ የሚጸፀቱ ራሳቸውን ያዋረዱ፤ እና በመንፈስ የተሠበሩ ብቻ ፀጋን ያገኛሉ፡፡ ለውጤታማነትና ለአሸናፊነት የሚያደርሱ ቅድመ ሁኔታዎች የዋህነትና ራስን ዝቅ ማድረግ ናቸው፡፡ በመስቀሉ ሥር ለሚሠግዱ የክብር አክሊል ይጠብቃቸዋል፡፡ *Ellen G. White , Prophets and Kings , p.590.*

*እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች ራሳቸውን ከእነርሱ የከፉ ኃጢአተኞች ናቸው ብለው ከሚገምቱ ሌሎች ሰዎች ጋር ያነፃፅራሉ ፤ ይህንንም የሚያደርጉት እራሳቸው ብዙም የከፉ አለመሆናቸውን ለማሳመን ነው፡፡ ይህንን የመሰለ መንፈሳዊ ራስን ማታለል ለምን ይሆን? ሌሎች ከእኛ የከፉ ቢሆኑ ምንድን ነው የሚያደርግልን?*

____________________________________________________________

_______________________________________________________

## ዓርብ ግንቦት 7 2007 ዓ.ም

**ለተጨማሪ ጥናት፡**- "ለእርዳታ፤ ለድጋፍ፤ ኃይልን ለማግኘትና በእያንዳንዱ

ዕለት ትጉህ ፀሎት ወደ እግዚአብሔር ፊቷን የምትመልስ ነፍስ የፀና ከፍተኛ ተስፋ ንፁህ የሆነ የእውነት ማስተዋልና ተግባር ፤ ከፍተኛ የሆነ የሥራ ዓላማ እና የማያቋርጥ የፅድቅ ጥማትና ረሃብ ይኖራታል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት በማጥበቅ በልባችን ውስጥ ያለውን ገዢ ስርዓት ከሌሎች ጋር ባለን ህብረት አማካይነት ብርሃናችንን ሰላማችንንና የመንፈስን እርጋታ ወደ ሌሎች ለማስረፅ እንችላለን፡፡ "

ወደ እግዚአብሔር አምላክ በመጸለይ የተገኘ ጥንካሬ ያለመሰልቸትን ለእውነትና ለጥንቃቄ አእምሮን ለመልካም ነገር ከማሰልጠን ጋር ተጨምሮ መንፈስን በማንኛውም ሁኔታ በሰላም ለመጠበቅና አንድን ሰው ለዕለታዊ ተግባሮች ዝግጁ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ Ellen G. White thoughts from the mount of blessing , p.85.

"እግዚአብሔርን አባታችን ብለን ስንጠራው የእርሱ ልጆች በሙሉ የእኛ ወንድሞችና

እህቶቻችን መሆናቸውን እንቀበላለን፡፡ እኛ ሁሉም የሰው ዘር የተያያዘበት ታላቅ የሆነ ቤተሰብ አካል ነን፡፡ በልመናችን ራሳችንንና ባልንጀሮቻችን ልናጠቃልል ይገባናል፡፡ ለራሱ ብቻ በረከትን የሚለምን ማንም ሰው የሚፀልየው ፀሎት ትክክል አይደለም "

## የመወያያ ጥያቄዎች፡-

❶ *ሉቃስ ኢየሱስንና መንፈስ ቅዱስን ማገናኘቱ በወንጌል ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ የሐዋሪያት ሥራን መጽሐፍ የሚያነብ ማንም ሰው በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የክርስቲያን ማህበረሰብን ህይወት ዓላማና አገልጋዮቹን የሚያስገድድ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያለበት የሉቃስ ሁለተኛው መጽሐፍ መሆኑን ሳይረዳ አይቀርም፡፡ በእርግጥ ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ ለደቀ-መዛሙርቱ ከኢየሩሳሌም መንፈስ ቅዱስን ሳይቀበሉ እንዳይወጡ የሠጠውን ማስጠንቀቂያ የዘገበው ሉቃስ ብቻ ነው፡፡ "እናንተ ግን ከላይ ኃይልን እስክትቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" (ሉቃስ 24፡ 49)የተሰቀለውንና ከሙታን የተነሳውን መድህን መልዕክት ይዘው ወደ ምድር ዳርቻ ከመሄዳቸው በፊት የተሠጣቸው መመሪያ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ሉቃስ የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍን የሚጀምረው ኢየሱስ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ደግሞ በሚሠጠው ሀሳብ (ሐዋ. 1፡ 7.8) ሲሆን ተስፋውም የተፈጸመው በጴንጤቆስጤ ቀን ነበር (ሐዋ. 2) ይህ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በቤተክርስቲያን ህይወት ውስጥ ማዕከላዊ ነገር ስለመሆኑ ምን ይነግረናል ?*

❷ *ፀሎት ራሱ እኛ በእግዚአብሔር ላይ የምንደገፍ እናም እርሱ የሚያስፈልገን መሆኑን ዕውቅና መስጠታችን የሚሆነው በምን መንገዶች ነው ? ሉቃስ 18፡9ን ያንብቡ፡፡ ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ በሰጠው ምሳሌ መጥቀስ የፈለገው ጥልቅ መንፈሳዊ ችግር ምንድን ነው?*





# 8ኛ ትምህርት

ከግንቦት 8-14 2007 ዓ.ም

# የኢየሱስ ተልዕኮ

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት ጥናት** ፡ ሉቃ 15፡ 4-7 ፤ 11-32 ፤ ሉቃ 16፡ 19-31 ፤ 18፡ 35-43 ፤ እና 19፡ 1-10ን ያንብቡ፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "የሰው ልጅ የጠፋውን ለመፈለግና ለማዳን መጥቶአልና" *(ሉቃስ 19፡10)*

የክርስቶስን ተልዕኮ ዓ.ነገር የምንፅፍ ብንሆን የተፃፈውን ከመድገም የተሻለ መጻፍ አንችልም ፡፡ "**የጠፋውን ለመፈለግና ለማዳን**" የጠፋው ምንድን ነው? ከእግዚአብሔር የተለየው፣ ለሞት የተገዛው፣ በፍርሃት የተዋጠውና ተስፋ የቆረጠው ራሱ የሰው ዘር ነው፡፤ በእኛ ፈንታ ምንም ያልተደረገ ቢሆን ኖሮ ጠፊዎች ነበርን፡፡

ቢሆንም ቅሉ ለኢየሱስ ምሥጋና ይግባውና እኛ ሁላችንም ተስፋን የተሞላን እንድንሆን ብዙ ምክንያቶች አሉን ፡፡

"በክህደቱ ሰው ራሱን ከእግዚአብሔር ለየው፤ ምድርም ከሰማይ ተቋረጠች በመካከላቸው በተፈጠረው የባህረ ሰላጤ ምክንያት ምንም ዓይነት ግንኙነት አልነበረም፡፡ ነገር ግን በኢየሱስ አማካይነት ምድር እንደገና ከሰማይ ጋር ተያያዘች፡፡ ክርስቶስ በራሱ በሆነ መልካም ሥራ ኃጢአት ለፈጠረው ጥልቅ ሸለቆ ድልድይ ሆነ . . . ክርስቶስ የወደቁትን ሰዎች ከድካማቸውና ከረዳተ ቢስነታቸው ጋር መጨረሻ ከሌለው የኃይል ምንጭ ጋር

ያያይዛቸዋል፡፡" *Ellen G. White , Steps to Christ, P. 20*

ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ፤ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የጠፋውን የሰው ዘር የፈለገበት ታሪክ ነው፡፡ ሉቃስ ይህንን እውነት ሦስት ጠቃሚ ምሳሌዎችን በመጠቀም ይገልፃል፡፡ የጠፋው በግ (ሉቃስ 15፡ 4-7) የጠፋው ሳንቲም ( ቁ. 8-10) እና የጠፋው ልጅ (ቁ. 11-32)

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለግንቦት 15 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

## እሁድ ግንቦት 9 2007 ዓ.ም

# የጠፋው በግና የጠፋው ሳንቲም

*ሉቃስ 15፡4-7 ያንብቡ፡፡ ይህ እግዚአብሔር ለእኛ ሰላለው ፍቅር ምን ይነግረናል? የጠፋውን በግ ፍለጋ የሔደው እረኛው መሆኑን ማስተዋል የሚጠቅመው ለምንድን ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ለእኛ ጥንቃቄ በማያደርግና ግድየለሽ በሆነ ዓለም ውስጥ ይህ ምሳሌ አስገራሚ እውነትን ይገልጽልናል፡፡ እግዚአብሔር እጅግ ስለ ወደደን እኛን ወደ ራሱ ለመውሰድ እርሱ ራሱ ተከተለን፡፡ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን ስለፈለጉ ሰዎች ብንናገርም በእውነት ግን ሰውን የሚፈልገው እግዚአብሔር ነው፡፡

"ራሷን ለእግዚአብሔር የሰጠች ውድ ነፍስ በእግዚብሔር እይታ ከዓለም ሁሉ ትበልጣለች ይህችን ብቸኛ ነፍስ ድና በመንግስቱ እንድትገኝ ሲል ኢየሱስ የጎልጎታን ስቃይ ይወስድ ነበር፡፡ እርሱ የሞተላትን አንድንም ነፍስ አይጥልም፡፡ ተከታዮቹ ለመለየት ካልወደዱ በቀር እርሱ አጥብቆ ይይዛቸዋል፡፡ *Ellen G. White , The Desire of Ages , p 483*

ሉቃስ 15፡8-9 ን ያንብቡ፡፡ ይህ ምሳሌ የሚገኘው በሉቃስ ወንጌል ብቻ ነው፡፡ የጠፋው ሳንቲም ከሁለት አንድ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ **1ኛ.** በኢየሱስ ዘመን አይሁዶች ታላቅ በሆነ ድህነት በመውደቃቸው አንዲት ዲናር (ሳንቲም) ለብዙዎቹ ቤተሰቦች ከአንድ ቀን ሥራ





ክፍያ በላይ ስትሆን አንድን ቤተሰብ በጥቂቱ ከመራብ ታድን ነበር፡፡ **2ኛ.** በደሃው ቤተሰብ ሁኔታ ሲታይ በጣም ትልቅ የሆነና ለረዥም ጊዜ የተጠራቀመ አስር ዲናር (ሳንቲም) አንዳንድ ሴቶች የጋብቻቸው ምልክት እንዲሆንላቸው በሻሻቸው ላይ ይሰፉ ነበር፡፡

ከሁለት አንዱም ሁኔታ መጥፋቱ እጅግ አሳሳቢ ነገር ነው፡፡ ስለዚህ ሴትዮዋ እጅግ በጣም በማዘን ምናልባትም መስኮት የሌላት ወይም በጣም ትንሽ መስኮት ያላትን ቤት መብራት አብርታ መጥረጊያዋን በመውሰድ የጠፋችውን ሳንቲሟን ለማግኘት ቤቱን አመሰቃቀለችው፡፡ የእርሷ ሣንቲሟን ማግኘት ልቧን ሞልቶ በሚፈስ ደስታ ሞላው የጓደኞቿንም እንዲሁ፡፡

"ምንም እንኳን ሣንቲሟ በአቧራና በቆሻሻ መካከል የወደቀች ብትሆንም አሁንም ወርቅ ወይም ብር ናት፡፡ ባለቤቷም የሚፈልጋት አሁንም ዋጋ ያላት በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ነፍስ ምንም እንኳን በኃጢአት የተዋረደ ቢሆንም በእግዚአብሔር እይታ ውድ ነው፡፡ ሳንቲሟ የገዢውን ምስልና ምልክት እንደምታሳይ ሁሉ ሰው በፍጥረቱ የእግዚአብሔርን ምስልና ምልክት ይዟል፡፡ እናም አሁን በኃጢአት ተፅዕኖ የጎደፈና የወየበ ቢሆንም የዚህ የተቀረጸ ፅሁፍ ምልክት ሁሌም በእያንዳዱ ነፍስ ውስጥ አይጠፋም፡፡ *Ellen G. White, Christ Object Lesson , p. 194.*

ዘመናዊ ሳይንስና ፍልስፍና እንደሚነግረን እኛ ትርጉም በሌለው ሁኔታ ስለ እኛ ማንነትና የወደፊት ሁኔታ ግድ በማይሠጠው ዩኒቨርስ በአጋጣሚ የመጣን ስለመሆናችን ብዙ ይናገራሉ፡፡ በእነዚህ ሁለቱ ምሳሌዎች የተሠን በፍጹም የተለየ ዓለም አመለካከት ምንድን ነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## ሰኞ ግንቦት 10 2007 ዓ.ም

# የጠፋው ልጅ ምሳሌ ክፍል አንድ

ስለ ይቅር ባይነት በጣም ቆንጆና አጭር ተደርጎ የተነገረ በታሪክ የተመሰገነ ምሳሌ፤ የጠፋው ልጅ ምሳሌ ነው (ሉቃስ 15፡11-32) በሉቃስ የተተረከ ምናልባትም የአፍቃሪ

አባትና የሁለት የጠፉ ልጆች ምሣሌ ተብሎ ሊጠራ የሚችል ምሳሌ ነው፡፡ አንዱ ልጅ ህግ በሌለበት ሩቅ አገር መኖርን ከአባቱ ፍቅር ይልቅ መረጠ፡፡ ሌላኛው ልጅ ከአባቱ ጋር ቤቱ መኖርን መረጠ ነገር ግን የአባቱን ፍቅርና የወንድምን ትርጓሜ አልተረዳም፡፡

1. "ስጠኝ" (ሉቃስ 15፡12) የታናሹ ልጅ አባቱን ከንብረቱ የእርሱ የሚሆነውን ድርሻ እንዲሠጠው የመጠየቁ ውሳኔ እንጂ በአእምሮው ብልጭ ያለበት ነገር አይደለም፡፡ ኃጢአት ብዙውን ጊዜ የሚመነጨው ለብዙ ጊዜ ትክክለኛ ባልሆነ ቦታ ከተሠጣቸው ቅድሚያዎች ነው፡፡ ታናሹ ልጅ ስለ ሩቅ ሀገር ውበትና አንፀባራቂነት ከወዳጆቹ ሰምቶ ይሆናል፡፡ ህይወት በቤት ውስጥ ወዲህም ወዲያም የማያላውስ ነበር፡፡ በዚያ ፍቅር ነበር ነገር ግን የራሱ የሆነ ድንበር ነበረው፡፡ ያ ሩቅ ሀገር ገደብ የሌለውን ኑሮ ሰጠው፡፡ አባትየው ለልጁ በጣም የሚጠነቀቅ ነበር፣ ፍቅሩም እጅግ በእቅፉ ውስጥ ነበር፡፡ ልጁም ነፃነት ፈለገ የእርሱም አመጽ ዘሩ የመጣው ምንም ክልከላ የሌለውን ነፃነት በመፈለጉ ነበር፡፡

2. "እኔ ለምን "( ሉቃስ 15፡ 13-16) ልጁም ያለውን ድርሻ በገንዘብ ተተምኖ ይዞ "ወደ ሩቅ ሀገር ሄደ፡፡" እርሱ የሄደበት ሩቅ ሀገር ከአባቱ ቤት በጣም ሩቅ ነበር፡፡ የሚጠነቀቁ የፍቅር ዓይኖች፣ ተከላካዩ የህግ አጥር፣ ሁሌ ያለው የፀጋ እቅፍ ለዚያ ሩቅ ሀገር የማይታወቅ ውጫዊ ነገር ነበር፡፡ ያም ሩቅ ሀገር የረብሻና ሁካታ ነበር (ሉቃስ 15፡13) ሁካታ ለሚለው የግሪኩ ቃል *(asotos)* እንደ ስም በመሆን ለሌሎች ሦስት ሥፍራዎች ስካርን ለመግለጽ በአዲስ ኪዳን ጥቅም ላይ ውሏል (ኤር. 5፡18) አመጸኝነት (በቲቶ 1፡6) "መዳራት የሥጋ ምኞት ስካር ዘፈን ያለልክ መጠጣት ጣኦትን ማምለክ " (1ጴጥ. 4፡3-4) ይህን የመሰለ አምላክ የሌለበት ደስታ ጤናውንና ሀብቱን አባክኖበት በአጭር ጊዜ ገንዘብ ጓደኛና የሚበላው የሌለው ሆነ፡፡ አንፀባራቂ የነበረው ህይወቱ በጣም ዝቅተኛ ወደ ሆነው የኑሮ ደረጃ ወረደ፡፡ በአይሁዳውያን ዘንድ እጅግ የተዋረደውን የአሣማ ጥበቃ ሥራ እስኪመኝ ድረስ በጣም ረሃብተኛ ሆነ፡፡

3. "ከሞያተኞቹ እንደ አንዱ አድርገኝ" (ሉቃስ 15፡ 17-19) ነገር ግን የጠፋው ልጅ አሁንም ልጅ ነው፡፡ ወደ ቤቱ የመመለስ ምርጫ የማድረግ ኃይል አለው፡፡ ስለዚህም ልጁ ወደ "ልቡ ተመልሶ" ቤቱን አሰበ አባት የሚባል ሰው እንዳለውም አሰበ፡፡ እንዲሁም ፍቅር የሚባል ግንኙነት እንዳለም አስታወሰ፡፡ አባቱን ለመለመን የሚሆኑ ቃላትን ወይም ንግግር ይዞ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ "አድርገኝ" ያ ማለት





የፈለከውን አድርገኝ ነገር ግን በእይታህ ውስጥና በአንተ ፍቅርና ጥንቃቄ ውስጥ ብቻ ይሁን፡፡ ከአባት ልብ የሚበልጥ ምን የተሻለ ሥፍራ አለ፡፡ ዓለም በጣም ማራኪ ሆና ትታያለች፡፡ *በዓለም ካሉ ነገሮች በተለየ መልኩ ፈታኝ የሆነብዎት ነገር ምን ይሆን? ያም እርስዎ ሲያስቡት ምንም ችግር የሌለው የሚመስል ነገር ግን ከፋቱን ውስጡ ከጠለቁ በኋላ ብቻ የሚያውቁት ምንድን ነው?*

## ማክሰኞ ግንቦት 11 2007 ዓ.ም

## የጠፋው ልጅ ምሳሌ ክፍል ሁለት

4. ወደ ቤት መመለስ (ሉቃስ 15፡17-20) የንስሐ ጉዞ ነበር፡፡ ጉዞውም የጀመረው ወጣቱ "ወደ ራሱ ሲመለስ ነበር"፡፡ የነበረበትን ሥፍራ ማስተዋልና የአባቱ ቤት ምን ይመስል እንደነበር ማወዳደሩ "ተነስቶ" ወደ አባቱ እንዲሄድ ገፋፋው፡፡ የጠፋውም ልጅ ወደ ቤቱ ሲመለስ እውነተኛ ንስሐን የሚያሳይ አራት ንግግሮችን ይዞ መጣ፡፡

**የመጀመሪያው፡-** አባትን "አባቴ" ብሎ መቀበሉ (ቁ. 18) የጠፋው ልጅ ልክ እኛ በሰማያዊው አባታችን ፍቅርና ይቅርታ መታመን እንደሚገባን ሁሉ እርሱም የአባቱን ፍቅርና ይቅርታ ታምኖ መደገፍ ነበረበት፡፡

**ሁለተኛ፡-** ንስሐ መግባት የጠፋው ልጅ ያደረገው የፍርድ ሥህተት ሳይሆን በእግዚአብሔርና በአባቱ ላይ ኃጢአት አደረገ፡፡

**ሦስተኛ፡-** መጸጸት "ከእንግዲህ ልጅህ ልባል አይገባኝም" (ቁ. 19)፡፡ እውነተኛ ንሰሐ ይሆነን ዘንድ የእግዚአብሔርን ታላቅነት በማስተዋል የራስን ዋጋቢስነት መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

**አራተኛ፡-** የአቤቱታ፤ "ከእንግዲህ ከባሮችህ እንደ አንዱ አድርገኝ" (ቁ. 19) እግዚአብሔር የወደደውን እንዲያደርግ መፍቀድ የንሰሐ ዓላማ ነው፡፤ ልጁም ወደ ቤት ተመለሰ፡፡

5. ይጠባበቅ የነበረው አባት (ሉቃስ 15፡20-21) ነቅቶ መጠበቅ መጨነቅና ተስፋ ማድረግ የጀመረው ገና የጠፋው ልጅ እግሩ ከቤት እንደወጣ ነበር፡፤ እርሱም መጠበቅ ያበቃው"ከሩቅ በተመለከተው ጊዜ" ነበር፡፡ "እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፤ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው፡፡"(ቁ. 20) በዚህ ዓይነት

ከሚጠባበቀው አባት የበለጠ የእግዚአብሔርን ምስል ሊያሳይ የሚችል ሌላ ምንም ነገር የለም፡፡

6. ተቀባይ ቤተሰብ (ሉቃስ 15፡22-25) አባት ልጁን አቀፈው አዲስ ልብስ አለበሰው ለጣቱም ቀለበት አደረገለት፤ ለእግሩም ጫማ ከዚያም ግብዣ እንዲደረግ አዘዘ፡፡ ቤተሰቡ በሙሉ በደስታ ላይ ነበር፡፡ ቤት ጥሎ መሄዱ ሞት ከነበረ፣ ወደ ቤት መመለስ ትንሣኤ በመሆኑ መደሰት ያስፈልግ ነበር፡፡ እውነትም ልጁ የጠፋ ነው፤ ነገር ግን ምንም እንኳን ልጅ ባይሆንም በእያንዳንዱ ንስሐ በሚገባ ሰው ምክንያት በሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆናል፡፡ (ቁ. 7)

7. (ሉቃስ 15፡25-32) ታናሹ ልጅ የጠፋው ወደ ሩቅ ሀገር ለመሄድ ከቤቱ ወጥቶ እርምጃ በጀመረ ጊዜ ነበር፡፤ ታላቁ ልጅ በአካል በቤት ውስጥ ቢኖርም ልቡ ግን ሩቅ ነበር፡፡ እንዲህ አይነት ልበ ቁጡ ነበር፡፡ (ቁ. 28) ተጨቃጫቂ እና በራሱ ጻድቅ እንደሆነ የሚሰማው (ቁ. 29) እና ወንድሙን ለመቀበል እምቢ ያለ ነበር፡፡ የተቀበለው ነገር "ልጁ"አባካኝ መልካም ባህሪይ የሌለው መሆኑን ነበር፡፡ ታላቁ ልጅ የነበረው ባህሪይ ፈሪሳዊያን በኢየሱስ ላይ ከነበራቸው ጋር ይመሳሰል ነበር፤ ይህ ሰው ኃጢአተኞችን ይቀበላል ከእነርሱም ጋር ይበላል፡፡ (ቁ. 2) አባትየው ለታላቁ ልጅ የተናገረው የመጨረሻው ቃል ንስሐ ለሚገቡ ኃጢአተኞች ሰማይ የሚያሳየው ባህሪይ ነፀብራቅ ነው፡፡ "ዳሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበር ህያው ስለሆነ ጠፍቶም ነበር ስለተገኘ ደስ እንዲለን ፍስሐም እንድናደርግ ይገባናል አለው"(ቁ. 32)

*ራስዎ በታላቁ ልጅ ጫማ ውስጥ ይቁሙ፡፡ አስተሳሰቡ ስህተት እንኳን ቢሆን እንደዚያ ማሰቡ ትርጉም የሚኖረው ለምንድነው? ይህ ታሪክ ወንጌል ከአስተሳሰብና ከስሜት የበለጠ ርቆ የሚሄድ መሆኑን የሚያስተምረን እንዴት ነው?*

__________________________________________________________

__________________________________________________________





**ረቡዕ** ግንቦት 12 2007 ዓ.ም

# የባከኑ ዕድሎች

ምንም እንኳን ኢየሱስ የመጣው በኃጢአት የጠፋትን ፍለጋ ቢሆንም እርሱ የሚሠጠውን ደህንነት የማይቀበለውን ማንንም አያስገድድም፡፡ መዳን በነፃ የተሠጠ እና ለሁሉም የሚበቃ ነው፤ ነገር ግን አንድ ሰው ይህንን ነፃ ሥጦታ ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር በሚስማማ ህይወት አማካይነት በፈቃዱ ሊቀበለው ይገባል፡፡ ይህን ልናደርግ ያለን ጊዜ ደግሞ በምድር በህይወት ሳለን እንጂ ሌላ ዕድል የለንም፡፡

*ሉቃስ 16፡19-31 የዚህ ምሳሌ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?*

__________________________________________________________

__________________________________________________________

ይህ ታሪክ የተዘገበው በሉቃስ መጽሐፍ ብቻ ሲሆን፤ ደህንነትን በሚመለከት ሁለት ታላላቅ እውነቶችን ያስተምረናል፤ በደህንነት ሂደት ውስጥ የዛሬን አስፈላጊነትና ከሞት በኋላ ለድነት የሚሆን የቀረ ምንም ዕድል አለመኖሩን ይነግረናል፡፡

የመዳን ቀን ዛሬ ነው፡፡ ምሳሌው ከሀብት ጋር አብሮ የሚወረስ ክፉ ወይም ደሀ በመሆን እንዳናመልጠው ሊይዘን የሚችል አንዳችም ነገር እንደሌለ ያስተምረናል፡፡ የሚያስተምረን ትምህርት ግን የዳኑ የመሆን ዕድልንና በምድር ድኖ መኖር ልናጤነው የሚገባን እንደሆነ ነው፡፡ ሁለቱም ወይም ደሃ የተማረ ያልተማረ ሃይል ያለው ወይም የሌለው ማናችንም ብንሆን ሁለተኛ ዕድል የለንም፡፡ ሁሉም ሰው የሚድነው ሆነ የሚፈረድበት ዛሬ ለክርስቶስ ባለው ባህሪይ ነው፡፡ "እነሆ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው" (2ቆሮ. 6፡2)

ታሪኩ በተጨማሪ ዘለዓለማዊ ሽልማት ከቁሳዊ ሀብት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ያስተምረናል፡፡ "ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ፀጋ ሰው ነበር ዕለት ዕለት እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር፤ ነገር ግን ለህይወት እጅግ አስፈላጊ የሆነው እግዚአብሔር የሌለበት ነበር፡፡ እግዚአብሔር በሌለበት የሰው ልጆች ፋይዳ የላቸውም፡፡ የሀብታሙ ሰው ኃጢአት በሀብቱ ላይ ሳይሆን እርሱ ሊቀበለው ከተዘጋጀው የበለጠ እጅግ

ሥፊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቤተሰብ ለማስተናገድ ዝግጁ አለመሆኑ ነበር፡፡

ከሞት በኋላ የሚሆን ሌላ የደህንነት ዕድል የለም፡፡ ኢየሱስ እያስተማረን ያለው የማይታለፍ እውነታ ከሞት በኋላ የሚሆን ሌላ ደህንነት ዕድል የሌለ መሆኑን ነው፡፡ "ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱም በኋላ ፍርድ እንደተመደበላቸው" (ዕብ. 9፡27) ፡፡ የዚህ ታሪክ ሌላኛው ነጥብ ዛሬ በዚህ ህይወት ሳለን ምርጫችንን ለእግዚአብሔር ወይም በተቃራኒው ለማድረግ የሚሆን በቂ ማስረጃ የተሠጠን መሆኑን ለህዝቦች ማሳየት ነው፡፡ ከሞት በኋላ ሌላ ዕድል መኖሩን የሚያስተምር ማንኛውም የስነ-መለኮት ትምህርት ታላቅ ማሳሳቻ ነው፡፡

*እግዚአብሔር እንደሚወደንና ያደረገው በሙሉና እያደረገ ያለው እኛን ሊያድነን መሆኑን እንናገራለን፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅርና እርሱ የሚሠጠንን ደህንነት ችላ ማለት ምን አደጋ እንዳለበት ይህ ምሳሌ ምን ያስተምረናል፡፡?*

________________________________________________

________________________________________________

## ሐሙስ ግንቦት 13 2007 ዓ.ም

# እውር ነበርሁ አሁን ግን አየሁ

የሰው ልጅ የጠፉትን ለመፈለግ መጥቷል የሚለው የክርስቶስ ተልዕኮ ዋና ዓ.ነገር የእርሱ አጠቃላይ አገልግሎት ማረጋገጫ ነበር፡፡ እርሱ የመጣው የሰውን ልጆች ወንዶችነንና ሴቶችን ሙሉ ሊያደርግ በአካል፣ በአእምሮ፣ በመንፈሳዊ እና በማህበራዊ ነገሮች ሊለውጣቸው ነው፡፡ የሉቃስ ወንጌል ኢየሱስ ሁለት የተሠበሩ ሰዎችን እንዴት ሙሉ አድርጎ እንደጠገናቸው ይተርክልናል፡፡ አንዱ በአካል እውር የነበረ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በመንፈስ እውር ነበር፤ ሁለቱም ከማህበረሰቡ የተገለሉ ሲሆኑ አንደኛው ለማኝና ሌላኛው ደግሞ ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር፡፡ ነገር ግን ሁለቱም የኢየሱስ አዳኝ አገልግሎት እጨዎችና ሊደርስበትም በሚችለው ርቀት በልቡ የነበሩ ናቸው፡፡

**ሉቃስ 18፡ 35-43 ን ያንብቡ፡፡ ይህ እኛ በእግዚአብሔር ላይ ሙሉ በሙሉ የተደገፍን ስለመሆኑ ምን ያስተምረናል?**

________________________________________________

________________________________________________





ማርቆስ ይህን ሰው ባርጤሜዎስ ይለዋል፡፡ (ማር 10፡46) ከኢያሪኮ ከተማ ውጭ የሚቀመጥ ለማኝ ነበር፡፡ በአካል የተለወጠ ማህበራዊ ኑሮ የሌለው እናም በረሃብ የተመታ፤ በድንገት ራሱን በሰማያዊ መደነቅ ውስጥ አገኘ፤ "የናዝሬቱ ኢየሱስ እያለፈ ነው፡፡ (ሉቃ 18፡37) እና በውስጡ ያለው እምነት "የዳዊት ልጅ ማረኝ" ብሎ እንዲጮህ አስገደደው፡፡ (ቁ. 39) እምነት እጅን፤ እግርን፤ ጆሮን፤ ዓይንን ሳይሆን የሚፈልገው ከፈጣሪው ጋር የሚያገናኝን ልብ ብቻ ነው፡፡

ሉቃ 19፡ 1-10 ያንብቡ፡፡ በዚህ ታሪክ እውሩ ሰውዬ ማን ነበር? ከማህበረሰቡ ከተገለሉ ኢየሱስ ካገኛቸውና ካቀረባቸው ብዙ ሰዎች መካከል የዘኬዎስን ታሪክ የዘገበው ሉቃስ ብቻ ነው፡፡ የጠፉትን መፈለግና ማዳን የሚለው የክርስቶስ ተልዕኮ ከዘኬዎስ ጋር ባደረገው ግንኙነት በተሟላ ሁኔታ ተገልጿል፡፡ ዘኬዎስ የኢያሪኮ ቀረጥ ሰብሳቢዎች አለቃ ነበር፤ በከተማው በሚገኙ ፈረንሳዊያን ዘንድ ዋና ኃጢአተኛ ነገር ግን በክርስቶስ የታሰበና የዳነ ኃጢአተኛ ነበር፡፡ ክርስቶስ ተልዕኮውን ለመፈጸም የተጠቀመባቸው መንገዶችና ቦታዎች እንዴት እንግዳ ነበሩ፡፡ የሾላ ዛፍ፣ ኢየሱስን ማን እንደሆነ ለማየት ጉጉት የነበረው ሰው፣ ሰውዬውን ከዛፉ ወርዶ ወደ እርሱ እንዲመጣ የሚያዝ የፍቅር ጌታ በራሱ ምሳውን ከዚያ ሰው ጋር ለመብላት ጋብዞ ነበር፡፡ ነገር ግን ከሁሉ የሚበልጠው ክርስቶስ ለዚያ ቤት የሚሠጠው ነበረው፡፡ "ዛሬ መዳን ወደዚህ ቤት መጥቷል " (ሉቃ 19፡9) ነገር ግን ዘኬዎስ ነገሮችን ከማስተካከሉ ቀድሞ አልነበረም፡፡ (ቁ.8)

*የሰዎችን ስህተትና ውድቀት ማየት ቀላል ነው አይደል? ነገር ግን ስለ ራሳችን እውራን ልንሆን እንችላለን፡፡ በህይወትዎ ፊት ለፊት ገጥመው ንስሐ በመግባት ድልን መጎናፀፍ የሚገባዎት የትኞቹ የህይወትዎ ክፍሎች ናቸው?*

## ዓርብ ግንቦት 14 2007 ዓ.ም

**<u>ለተጨማሪ ጥናት</u>፡-** "የጠፋው በግ ምሳሌ የሚያመለክተው ኃጢአተኛ የሆነውን ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በኃጢአት የተበላሸችውንና ከሃዲ የሆነችውንም አንዷን ዓለም ጭምር ነው፡፡"

የአንዲትን ነፍስ ትልቅ ዋጋን በተመለከተ "የአንዲትን ነፍስ ዋጋ ማን ይተምናል? ወደ ጌትሰማኔ ሂድ ከክርስቶስም ጋር በመሆን ስለ እነዚያ የጭንቅ ሰዓታት እርሱ ባሰበው ጊዜ እንደ ደም ጠብታ ተመልከት ያኔ ዋጋዋን ታውቃለህ፡፡ በመስቀል ላይ ከፍ ተደርጎ የተሰቀለውን ጌታ ተመልከት በመስቀሉ ሥርም በመሆን ክርስቶስ ለአንዲት ኃጢአተኛ ነፍስ

እንኳ ቢሆን ህይወቱን ይሠጥ እንደነበር በማስተዋልና በማሰብ የዚያኔ የአንዲትን ነፍስ ዋጋ ትገምታለህ"

## የመወያያ ጥያቄዎች:-

❶ *ሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ ሰው እግዚአብሔርን እንደሚፈልግ ሲናገሩ ክርስትና ብቻ ፈላጊ እግዚአብሔር እንደሆነ ይነግረናል፡፡ አዳም ወዴት ነህ (ዘፍ. 3፡9) ቃየል ወንድምህ ወዴት ነው? (ዘፍ. 49) ኤልያስ በዚህ ምን ታደርጋለህ? (1 ነገሥት 19፡9) ዘኬዎስ ና ውረድ (ሉቃስ 19፡5) እግዚአብሔር እርስዎን የሚፈልግ ስለመሆኑ ልምምድዎ ምን ነበር?*

❷ *በማክሰኞ ቀን መጨረሻ ያለውን ጥያቄ እንደገና ይመልከቱ፡፡ ታላቁ ልጅ የሠራው ትልቅ ስህተት ምንድን ነው? በእርሱ ባህሪይ ምን መንፈሳዊ ድክመት ተገለፀ? እኛ ከምናስበው በተለየ ሁኔታ ተመሳሳይ ባህሪይ ሊኖረን የሚችለው እንዴት ነው? ማቴ. 20፡16 ይመልከቱ፡፡*

❸ *ኢየሱስ በሀብታሙ ሰውና በአልዓዛር ታሪክ የሞቱ ሰዎች እንደገና በህይወት የሚመጡ እንኳ ቢሆን የማያምኑ ይኖራሉ ብሏል፡፡ ይህ ምሳሌ ወደፊት በክርስቶስ ትንሳኤ ጊዜ ሰዎች ስለሚኖራቸው አመለካከት የሚተነብየው እንዴት ነበር? ብዙዎችም የትንሳኤውን ብዙ መረጃ እየተመለከቱ ያላመኑትስ?*

❹ *የክርስቶስ አዳኝ አገልግሎት የሚመስጠው ክፍል ሁሉን ህዝቦች በእኩል ማስተናገዱ ነው ለምሳሌ እውሩን ለማኝ ፤ ዘኪዎስን፣ ኒቆዲሞስን፣ እናም የሰማሪያዋን ሴት መስቀሉ ከሁሉም በላይ ሁሉም ሰዎች በእግዚአብሔር እይታ እኩል መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ይህ በጣም ወሳኝ የሆነ እውነት በፖለቲካ በባህል በዘር ሆነ በሌላው በማንኛውም እኛ ቀደም ሲል ወድቀንበት የነበረ ሁኔታ ቢሆን እኛ ሌሎችን እንዴት መቅረብ እንዳለብን ምን ያስተምረናል? እንደዚህ ዓይነት አመለካከቶች የክርስቶስ ተቃራኒ የሚሆኑትስ እንዴት ነው?*

❺ *የጠፋውን ልጅ ታሪክና የሀብታሙንና የአላዛርን ታሪክ ያወዳድሩ፡፡ አንዱ የሌላውን ሚዛን የሚጠብቀው እንዴት ነው?*





# 9ኛ ትምህርት

ግንቦት 15-21 2007 ዓ.ም

# ኢየሱስ ዋናው መምህር

### ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት ጥናት:- ሉቃስ 8፡ 22-25 ፤ 4፡ 31-37 ፤ 6፡20-49 ፤ 8፡ 19-21 ፤ 10፡ 25-37 ዘዳ. 6፡5 ን ያንብቡ፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ:-** *"ቃሉ በሥልጣን ነበርና በትምህርቱ ተገረሙ" (ሉቃስ 4፡32)*

ክርስቶስ ወደ ምድር በመጣበት ዘመን ሰብዓዊ ዘር እጅግ ዝቅ ወዳለው ደረጃ በፍጥነት እየሄደ ነበር፡፡ ለህብረተሰቡ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ ችላ ተብለው ነበር፡፡ ህይወት ራሱ ውሸትና ከአንገት በላይ ሆኖ ነበር፡፡ የሰውን አስተሳሰብ ውጦ ለማስቀረት በማሰብ ተረትና ውሸት የሚያስጠላ ሆኗል፡፡ ሰዎችም ቃል ኪዳንን ወደ ማፍረስና ቁሳዊነት ዞር ብለዋል፡፡ ዘለዓለማዊነትን ከአእምሮአቸው በማስወጣት ለጊዜያዊው ብቻ ይኖሩ ነበር፡፡

"መለኮታዊውን ማስተዋል ሲያቅታቸው ሰብአዊውንም ማክበር ጠፋባቸው፡፡ እውነት፣ አክብሮት ጽናት፣ በራስ መተማመን፣ ለሌሎች ማዘን እነዚህ ሁሉ ከምድር እየጠፉ ነበር፡፡ ምህረት የለሽነት ፤ ስግብግብነት፤ እና ሁሉን ለራስ የሚል ምኞት በዓለም ሁሉ ላይ አለመተማመን እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ የግዴታ መንፈሰ ጠንካራው ለደካማው ማድረግ የተገባው የሰው ስብዕናና ሰብዓዊ መብቶች እነዚህ ሁሉ እንደ ተረትና ህልም ወዲያ ተጥለዋል፡፡ ተራዎቹ ህዝቦች እንደ ተሸካሚ እንስሳትና የራስን ምኞት ለማሳካት እንደ

*መርገጫ ደረጃዎች ይታዩ ነበር፡፡ ሀብትና ኃይል፣ የራስን ፍላጎት ማርካትና ቀላል ኑሮ እነዚህ እንደ ትልቅ ነገር ይታዩ ነበር፡፡ መንፈሰ ልል መሆን በመጠጥ አእምሮን መሣት መንፈሳዊ ሞት እነዚህ የዘመኑ አብይ ባህሪያት ነበሩ፡፡" Ellen. G. White Education PP. 74:75*

በእነዚህ ቅድመ ታሪኮች ክርስቶስ ያስተማራቸውን ነገሮች ለምን እንደነበር በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ይጠቅመናል፡፡

**ለግንቦት 21 ሰንበት ለመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ያጥኑ፡፡**

**እሁድ** ግንቦት 16 2007 ዓ.ም

# የኢየሱስ ሥልጣን

ሉቃስ ሐኪምና የተማረ እንደመሆኑ የሥልጣንን ሚና ጠንቅቆ ያውቅ ነበር፡፡ በግሪኮች ትምህርትና ዕውቀት መሠረት ከፍልስፍናና ሥልጣን ጋር የቀረበ ዝምድና ነበረው፡፡ የሮማውያንን የፍትሐ-ብሔር ህግ ሥልጣንን ያውቅ ነበር፡፡ ከጳውሎስ ጋር አብሮ ተጓዥ እንደ መሆኑ ደግሞ ሐዋሪያው ሲያዘው የነበረውን እርሱ በመሰረታቸው ቤተክርስቲያናት ላይ የሰባኪነት ሥልጣን ምን እንደሆነም ያውቅ ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳ ሉቃስ ሥልጣን የአንድ ሰውን ደረጃ፣ የአንድን ድርጅት ሚና፣ የመንግሥትን ምንነትና የአስተማሪን ከተከታዮቹ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገልፅ ነገር መሆኑን አስተውሏል፡፡

የትኞቹም ዓይነት በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የተኞቹም ኃይላትና ሥልጣናት፣ በአናፂ ቤት የተወለደው፣ አነስተኛ በሆነችው የናዝሬት ገሊላ ለ30 ዓመታት ያደገው፣ በዓለማዊ መስፈርት በምንም ታላቅ ነገር ያልታወቀው፣ እየሱስ እያንዳንዱን የሮም መሪ፣ የተማረን አይሁድ፣ መምህራንን፣ ተራዎቹን ሰዎች ዓለማዊውንና ሃይማኖታዊ ሥልጣናት በትምህርቱና አገልግሎቱ ተገዳድሯቸዋል፡፡ "ከአፉም ከሚወጣው የፀጋ ቃል የተነሳ ይደነቁ ነበር (ሉቃስ 4:22)፡፡ የሞተውን ልጇን በማንሳት ለነይኗ መበለት ተስፋን አመጣላት (ሉቃስ 7:11-17)፡፡ በከተማው ኢየሱስ በህይወት ላይ የነበረው ሥልጣን ናይንን ብቻ ሳይሆን ይሁዳንም በሙሉ አንቀሳቅሷል፡፡ (ቁ. 16:17)





ሉቃስ 8:22-25 ፤ 4:31-17 ፤ 5:24-26 ፤ 7:49 ፤ 12:8 ን ያንብቡ፡፡ እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ ተጎናጽፎት ስለነበረው ሥልጣን ምን ይነግሩናል?

ሉቃስ፤ ኢየሱስ በአገልግሎቱ አማካይነት የእርሱ ሥልጣን ከሁሉ የተለየ የመሆኑን መሠረት የጣለ እንደሆነ ለወዳጁ ቴዎፍሎስ ብቻ ሳይሆን ለሚመጣው ትውልድ ሁሉ ዘግቧል፡፡ አምላክ በሥጋ እንደመሆኑ በእርግጥ ማንም ያልነበረው አይነት ሥልጣን ነበረው፡፡

ብዙዎች በሚያገለግሏቸው ድርጅቶች፤ ሥልጣን እንዲያገኙ በእግዚአብሔር ስም ብዙ ነገር ያደርጋሉ፡፡ "እግዚአብሔር ይህንን እንዳደርግ መርቶኛል ስንል እርግጠኞች ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው? በሰንበት ትምህርት ክፍልዎ መልሱን ይወያዩ፡፡

**ሰኞ** ግንቦት 17 2007 ዓም

# የክርስቶስ ከሁሉ የሚበልጠው ስብከት

የተራራው ስብከት (ማቴ. 5-7) "የክርስትና ፍሬ ነገር" በመባል ይመሰገናል፡፡ ሉቃስ የዚህን መልዕክት በሉቃስ 6:20-49 እና በሌሎች ሥፍራዎችም እየመረጠ ያቀርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ሉቃስ ስብከቱን በቀጥታ የደቀመዛሙርትን ህጋዊ መመረጥ አስከትሎ አስቀምጦታል፡፡ (ሉቃስ 6:13) አንዳንድ አዋቂዎች "የ12ቱ የመቀባታቸው ኃላፊነት"ብለው ይጠሩታል፡፡

በሉቃስ 6:20-49ን ያጥኑና በዚህ የተገለጡ ደንቦችን የእርስዎ ህይወት ምን ያህል ያቀፈ እንደሆነ ራስዎን ይጠይቁ፡፡

1. የክርስቲያን በረከቶች (ሉቃስ 6: 20-22) ድህነት ፤ ረሃብ ፤ ለቅሶ ፤ እና የተጣሉ መሆን ወደ በረከት ሊመራ የሚችለው እንዴት ነው?
2. በተቃውሞ መካከል የክርስትያን ደስታ ምክንያት (ሉቃስ 6:22:23)
3. ጥንቃቄ የሚያሻቸው ዕይታዎች (ሉቃስ 6:24-26)፡፡ ክርስቲያን ከእነዚህ መጠንቀቅ የሚያሻው ለምንድን ነው?
4. ክርስቲያኖችን ሊያደርጓቸው የሚገቡ ነገሮች (ሉቃስ 6:27-31)፡፡ ከኢየሱስ

የፍቅር ወርቃማ ትዕዛዛት በላይ አከራካሪና ለመጠበቅ አስቸጋሪ የሆኑ ትዕዛዛት የሉም፡፡ በመሠረቱ የክርስቲያን ግብረገብ አዎንታዊ እንጂ አሉታዊ አይደለም፡፡ በውስጡም የያዘው መደረግ ያለበትን እንጂ መደረግ የሌለበትን አይደለም፡፡ "ጠላትህን አትጥላ በማለት ፋንታ ጠላትህን ውደድ "ጥርስን በጥርስ በሚለው አድርጎ የመመለስ ህግ ፋንታ ወርቃዊ ህግ "አንዱን ጉንጭህን ለመታህ ሌላውን ስጠው" በማለት ፍጹም ንፁህ የሆነ ግብረገባዊነትን ይፈልጋል፡፡ መሀተመ ጋንዲ ከወርቃማ ህግ ከፉውን በመልካም የማሸነፊያ ሌላ የፖለቲካ ፊሎዞፊ በማዘጋጀትና ይህንንም ደንብና ሥርዓት ህንድን ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነፃ ለማውጣት ተጠቅሞበታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ማርቲን ሉተር ኪንግ የወርቃማውን ህግ የተባበሩት የአሜሪካን ግዛቶች የነበረውን በህዝቦች መካከል የነበረውን ልዩነት በመስበር ላይ አውሏል፡፡ ፍቅር በነገሠበት ሥፍራ በረከት ዙፋን ላይ ይወጣል፡፡

5. የክርስቲያን ሁኔታ (ሉቃስ 6፡37-42) የክርስቶስን ስለ ይቅርታ አጥብቆ ማስተማር፣ በደስታ የመስጠት ምሳሌያዊ ህይወት ስለመኖር እና ስለ ትዕግሥት ያስተማረውን ያጢኑ፡፡
6. የክርስቲያንን ፍሬ ማፍራት ( ሉቃስ 6፡ 43-45 )፡፡
7. ክርስቲያን ግንበኛ (ሉቃስ 48፤49)፡፡

## ማክሰኞ          ግንቦት 18 2007 ዓ.ም

# አዲስ ቤተሰብ

ከክርስቶስ በፊትና እስከ ክርስቶስ የነበሩ ታላላቅ መምህራን ስለ አንድነትና ፍቅር አስተምረዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ፍቅር ከአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ ነበር፡፡ ይህም ቤተሰብ የተለየ ማህበረሰብ ቀለም ቋንቋ ነገድ ወይም ሃይማኖት ያለው ስለመሆኑ ይነገራል፡፡ ነገር ግን ክርስቶስ የሰብዓዊን ዘር የሚከፋፈለውን ነገር ሁሉ በማስወገድ በተራ ነገሮች መከፋፈልን ትቶ ልዩነት የሌለውን ቤተሰብ መሠረተ፡፡ አጋፔ በሆነው ፍቅሩ ሥር በችሎታ ላይ ያልተመሠረተ ሁሉን በሚያቅፍ ማንንም ወደ ውጪ በማይተውና መስዋዕትነት በሚያሳይ ሁኔታ አዲስ ቤተሰብን መሠረተ፡፡ ይህ ቤተሰብ ጥንታዊውን ዓለም አቀፋዊ እና





በጣም ጥሩ የሆነውን ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሯል የሚለውን የዘፍጥረትን የፍጥረት ሁኔታ የሚያንፀባርቅ እና የሚመሰክር ነው፡፡ (ዘፍ 1፡ 26.27) እናም ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር ፊት እኩል መሆኑን ያሳያል፡፡

ሉቃስ 8፡19-21 ን ያንብቡ፡፡ ልጆችንና ወላጆችን ወንድሞችንና እህቶችን እና የቤተሰብን የሚያስተሳስሩ ህጎችን በምንም መልኩ ሳያሳንስ ክርስቶስ ከሥጋና ከደም አርቆ በማሰብና በመሰውያዊ ላይ በማስቀመጥ ሁሉንም "በሰማይና በምድር ያሉትን አንድ ቤተሰብ አደረጋቸው"(ኤፌ 3፡15) የክርስቲያን ደቀመዛሙርነት ቤተሰብ መካከል ካለው ዝምድና በሥጋ ልጆች ካሏቸው የዝምድና ትስስር የሚያንስ አይደለም፡፡ ለኢየሱስ የአንድ ቤተሰብ አባል የመሆን መለኪያው ደም ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ መፈጸም ነው፡፡

*የሚከተሉት ጥቅሶች የሰውን ልጆች የሚለዩ የነበሩ ግድግዳዎች ግን ክርስቶስ ያስወገዳቸው ስለመሆኑ ምንድነው የሚያስተምሩ?*

ሉቃስ 5፡27-32 ------------------------------------------------

ሉቃስ 7፡1-10 ------------------------------------------------

ሉቃስ 14፡15-24------------------------------------------------

ሉቃስ 17፡11-19 ------------------------------------------------

የክርስቶስ ተልዕኮና አገልግሎት ፤ የእርሱ ይቅር ባይ ልብ፤ እና የሚያቅፈው ፀጋው ማንንም ወደ ውጪ የሚተው ሳይሆን ጥሪውን የሚቀበሉትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡

የእርሱ ዘላለማዊ ፍቅር ከመላው ማህበረሰብ ጋር ዝምድና እንዲኖረው አድርጎታል፡፡

*እንደ ቤተክርስቲያን ይህንን ወሳኝ የሆነ ደንብ በተሻለ መልኩ ልንከተል የምንችልባቸው መንገዶች ምንድንናቸው?*

------------------------------------------------

------------------------------------------------

## ረቡዕ ግንቦት 19 2007 ዓ.ም

# ፍቅር ሲተረጎም ፤ የመልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ፤ ክፍል 1

ከአራቱ ወንጌላት የጠፋውን ልጅና የመልካሙን ሳምራዊ ታሪክ የዘገበው ሉቃስ ብቻ ነው። (ሉቃስ 10፡25-37)። የመጀመሪያው አባት ለኃጢዓን ያሳየውን ከላይ ወደ ታች የሆነውን ያልተለመደውን የእግዚአብሔር ፍቅር የሚያሳይ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በሰዎች ህይወት መታየት የሚገባውን በሰዎች መካከል ላለው ለማንኛውም መሠናክል ሥፍራ የማይሠጠውን ነገር ግን እንደ ኢየሱስ "ባልንጀራ" በሚለው ትርጓሜ መሠረት በመኖር ሁሉም ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑ ፤ እናም መወደድ እንደሚገባቸው እንዲሁም ያለ አድልዎ ሊስተናገዱ እንደሚገባ የሚያሳይ ነው።

*ሉቃስ 10፡25-28ን ያንብቡና በተነሱት ሁለት ጥያቄዎች ውይይት ያካሂዱ። እያንዳንዱ ጥያቄ ከክርስቲያን ህይወትና እምነት ጉዳዮች ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዴት ነው?*

1. "መምህር ፤ የዘላለምን ህይወት ለመውረስ ምን ላድርግ?" (ቁ. 25)። የህግ አዋቂው የዘላለምን ህይወት መውረሻ መንገድ ለማወቅ መፈለጉን ልብ ይበሉ። ከኃጢአት አምልጦ የእግዚአብሔርን መንግስት መውረስ ለማንኛውም ሰው ሊኖር ከሚገባው ምኞቶች ሁሉ የሚበልጠው ቢሆንም ነገር ግን የህግ አዋቂው እንደ ሌሎቹም ብዙ ሰዎች የዘላለምን ህይወት መውረስ የሚቻለው በመልካም ሥራ ነው የሚለውን ትምህርት እየሰማ ያደገ ነበረ። "የኃጢአት ዋጋ ሞት ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሥጦታ በልጁ በኢየሱስ የዘላለም ህይወት ነው" (ሮሜ 6፡23)ን በትክክል ወይም በግልጽ አያውቀውም ማለት ነው።

2. "በህግ የተፃፈው ምንድንነው ? እንዴትስ ታነበዋለህ? (ቁ. 26)"።

በኢየሱስ ዘመን እንደዚህ የህግ አዋቂ ሰው ታዋቂ የሆኑ አይሁዳውያን ልምድ በወገባቸው ጠምጥመው በመያዝ የሚጠቀሙበት ጽሁፍ ነበር። ይህም በቆዳ የተሠራ ሲሆን ከሙሴ መጻህፍት ብዙው ክፍል የተፃፈበት እና የኢየሱስን ጥያቄም የሚመልሰውን ክፍል ያጠቃልላል። ኢየሱስም የህግ አዋቂውን (በዘዳ. 6፡5) እና (ዘሌ. 19፡18) እራሱ ተሸክሞት በሚገኘው ጽሁፍ ላይ ወደ ተጻፈው አመላከተው። እርሱ በወገቡ እንጂ በልቡ ለክርስቶስ





ጥያቄ መልስ አልያዘም ነበር። ኢየሱስ የህግ አዋቂውን የዘላለም ህይወት ህግን የመጠበቅ ጉዳይ ሳይሆን ነገር ግን ያለምንም ገደብ የእግዚአብሔር ፍጥረት የሆነውን ሁሉ የመውደድ ጉዳይ መሆኑን "ባልንጀራ" በማለት በአጭር ቃል አመልክቷል። *ነገር ግን የህግ አዋቂው ባለማወቅ ይሁን በማንአለብኝነት ንግግሩን ሌላ ጥያቄ በመጠየቅ ቀጠለ፤ "ባልንጀራዬ ማን ነው ?" በእምነትና ፀጋ መዳንዎን የሚያሳይ ምን ውጫዊ ማስረጃ አለዎት? በእምነት የፀደቁ መሆንዎ በህይወትዎ የሚታየው በዚህ ሁኔታ ነው?*

## ሐሙስ ግንቦት 20 2007 ዓ.ም

# ፍቅር ሲተረጎም ፤ መልካሙ ሳምራዊ ፤ ክፍል 2

"ነገር ግን እርሱ ራሱን ለማጽደቅ በመፈለግ ባልንጀራዬ ማን ነው በማለት መለሰ"(ሉቃ 10፡29)። የአይሁድ ህግ ሊቅ የሆነው የህግ አዋቂ ለጥያቄው መልሱን ማወቅ ነበረበት። በዘሌ19፡18 ላይ ሁለተኛይቱና ትልቋ ትዕዛዝ በተፃፈበት "ባልንጀራ" የሚለውን የህዝብህ ልጆች ተብሎ ተተርጎሟል። ከዚያም ኢየሱስ ለህግ አዋቂው ጥያቄ የሥነ-መለኮታዊ ትምህርት ዝርዝር ክርክር ወይም አጭርና አፋጣኝ መልስ በመስጠት ፋንታ የህግ አዋቂውንና የሚቀጥለውን ንግግር ምን እንደሆነ ለመስማት የጓጉትን ሰሚዎቹን ከፍ ወዳለው ነገር አመለከታቸው።

*ሉቃስ 10፡30 -37 ን ያንብቡ። የዚህ ታሪክ ዋና ነጥብ ምንድን ነው? ሌሎችን እንዴት መቅረብ እንደሚገባን ምን ያሳየናል?*

__________________________________________________________

__________________________________________________________

*ኢየሱስ "አንድ ሰው" በወንበዴዎች እጅ ወደቀ ያለውን ያስተውሉ (ቁ.30)። ኢየሱስ የሰውየውን ዘርና የኑሮ ሁኔታ ምን እንደሆን ያልገለፀው ለምንድን ነው? የምሳሌውን አጠቃላይ ዓላማ በተመለከተ ይህ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?*

*ከህኑና ሌዋዊው የቆሰለውን ሰው አዩ አልፈውም ሄዱ። እነርሱ ያልረዱበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን ለእኛ ጥያቄ የሚሆነው እውነተኛ የሆነ ሃይማኖት ምንድንነው? እንዴትስ ይገለፃል? ዘዳ. 10፡12-13 ፤ ሚክ. 6፡8 ፤ ያዕ. 1፡27 ።*

በአይሁዳውያንና በሳምራውያን መካከል ያለው ግንኙነት ሁል ጊዜ ጠላትነትን የሚያሳይ ሲሆን በኢየሱስ ዘመን ይሄ ጠላትነት ወደ ከፋ ደረጃ ደርሶ ነበር፡፡ (ሉቃስ 9፡51-54 ፤ ዩሐ4፡9)፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ በዚህ ታሪክ ሳምራዊውን አሸናፊ ገጸ-ባህሪይ በማድረግ እውነታውን ሲገልፅ ለአይሁዶች ጥላቻው ከነበረው የከፋ ሆነ፡፡

ኢየሱስ የሳምራዊውን አገልግሎት በጥልቀት ዘርዝሯል፤ አዘነለት ፤ ወደ እርሱም ሄደ ቁስሉንም በጨርቅ አሠረለት ዘይትና የወይን ጠጅ በቁስሉ አፈሰሰለት፤ ወደ ትንሽ ሆቴልም ወስደው ለቆይታው የሚያስፈልገውን በቅድሚያ ከፈለ ሲመለስም ለእርሱ የወጣውን ወጪ ሁሉ እንደሚከፍል ቃል ገባ፡፡ እነዚህ ሁሉ የሳምራዊው አገልግሎቶች ወሰን የሌለው የእውነተኛ ፍቅር መግለጫ ናቸው፡፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ምናልባትም አይሁዳዊ ለሆነ ሰው ማድረጉ እውነተኛ ፍቅር ድንበር የሌለው መሆኑን ጭምር ይነግረናል፡፡

*ካህኑና ሌዋዊው ይህን ጥያቄ ራሳቸውን ጠይቀዋል፡፡ ቆም ብለን ይህንን ሰው ረድተነው ቢሆን ምን እንሆናለን? ሳምራዊው ግን እኔ ይህንን ሰው ባልረዳው ይህ ሰው ምን ይሆናል? ነበር ያለው፡፡ በእነዚህ ሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድንነው?*

## ዓርብ

ግንቦት 21 2007 ዓ.ም

"ክርስቶስ በህይወቱና በትምህርቱ መሠረት ከእግዚአብሔር የሆነውንና ራስ ወደድ ያልሆነውን ፍጹም ምሳሌያዊ የሆነውን አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ እግዚአብሔር ለራሱ አልኖረም፡፡ አለምን በመፍጠሩ እናም ሁሉንም ደግፎ በማኖሩ ሳያቋርጥ ሌሎችን እያገለገለ ነው፡፡" እርሱ በክፉዎችና በደጎች ላይ ፀሐይን ያወጣል፡፡ በፃድቃንና በኃጢአተኞች ላይ ዝናብን ያዘንባል፡፡ (ማቴ. 5፡ 45)፡፡ እግዚአብሔር ለልጁ የሠጠው ይህን ታላቅ ሥራ አገልግሎት ነበር፡፡ ኢየሱስም የተሠጠው የሰብዓዊ ዘር ሁሉ ራስ በመሆን በምሳሌነቱ ማገልገል ማለት ምን እንደሆነ እንዲያስተምር ነበር፡፡ ህይወቱ በሙሉ በአገልግሎት ህግ ሥር ነበር፡፡ እርሱ ሁሉን አገልግሏል ለሁሉም አገልግሏል፡፡ ስለዚህ እርሱ የእግዚአብሔርን ህግ ኖረ ለኛም እንዴት መኖርና መከተል እንደሚገባን በምሳሌው አሳየን፡፡" *Ellen G. White, The Desire of Ages, p. 649.*

"የመልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ ግምታዊ ሳይሆን በትክክል የሆነና በምሳሌው እንደተገለፀው የተከሰተ ነበር፡፡ የቆሰለውን ሰው አይተው አልፈው የሄዱት ካህኑና ሌዋዊው ክርስቶስ ይህንን ታሪክ ሲናገር ከሚሰሙት መካከል ነበሩ"





## የመወያያ ጥያቄዎች፡-

❶ *በእሁድ ቀን ትምህርት መጨረሻ ላይ የተጠየቀውን አስፈላጊ ጥያቄ እንደገና ያጢኑ፡፡ ሰዎች የሠሩትን በሙሉ ሠርተው እግዚአብሔር አድርግ ብሎኝ ነው ሲሉ ያልሰማ ማን ነው ? እግዚአብሔር ለእኛ የሚናገራቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? የእኛን ሥራዎች ለማስተባበል ስንል የእግዚአብሔር ሥልጣን ያለ አግባብ መንካት ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ምንድን ነው?*

❷ *በሉቃስ 6፡24-26 ላይ ወዳሉት አራቱ ወዮዎች እንደገና ይሂዱ፡፡ ኢየሱስ እዚያ ቦታ የሚለውን እንዴት እናስተውለዋለን? በዚህ ህይወት ሳለን በእውነት እንድንጠነቀቀው እየነገረን ያለው ምንድንነው?*

❸ *የሥልጣንን ጥያቄ በሙሉ ያስተውሉ፡፡ ሥልጣን ምንድንነው? የተለያዩ የሥልጣን ዓይነቶች ምንድንናቸው? የትኛው የሥልጣን ዓይነት ነው ከሌሎች የሚበልጠው? በህይወታችን ከተለያዩ የሥልጣን ዓይነቶች ያለን ግንኙነት እንዴት ነው? ከላያችን ያሉ ሥልጣናት ሲጋጩ በእኛ ላይ ምን ይሆናል?*

# 10ኛ ትምህርት ግንቦት 22-28 2007 ዓ.ም

# በየዕለቱ ህይወታችን ኢየሱስን መከተል

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት ጥናት፡** ሉቃ 11፡37-54 ፤ 12፡ 4-21 ፤ 35 -53 ፤ አሞ 6፡1፤ ሉቃ 8፡4-15 ፤ 22 ፡ 24-27 ን ያንብቡ፡፡

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡-** "ሐዋሪያትም ጌታን እምነትን ጨምርልን አሉት" *(ሉቃስ 17፡5)፡፡*

ምንም እንኳን ታላቅ መምህር ቢሆንም ኢየሱስ የስነ-መለኮት ት/ቤት አላቋቋመም፡፡ የእርሱ ዓላማ "የጠፉትን መፈለግና ማዳን ነበር" (ሉቃስ 19፡18)፡፡ "እርሱ የመጣው በመስቀል ላይ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ባህሪይ ለመደምደም ነበር፡፡ እርሱ እግዚአብሔር የሚወደውን ሰብዓዊነትና ውድቀት የሌለበትን ሁኔታ ለማሳየት ብቻ ሳይሆን የወደቀው ሰብዓዊ ዘር እንዲድን የኃጢአት ቅጣት ዋጋን ከፈለ፡፡

ይህን በማድረግ በእርሱ ሞት የዳኑና የእርሱን ህይወትና ትምህርት ምሳሌነት ለማንፀባረቅ የዳኑ ማህበረሰቦችን ፈጥሯል፡፡





የነዚህ የዳኑ ማህበረሰብ አባል ለመሆን መጠራት የተሻለ በመሆኑ ወደሚመረጥ የኑሮ ደረጃ መጠራት ሳይሆን ነገር ግን ወደ ጠሪው ወደ ክርስቶስ ተጠግቶ ራስን ለመስጠት የሚደረግ ጥሪ ነው፡፡ ክርስቶስ የሚለው የደቀ-መዛሙሩ የህይወቱ ህግ ይሆናል፡፡ " እርሱ የሚመኘው የደቀ-መዛሙሩ ዋነኛ የህይወቱ ዓላማ ይሆናል፡፡ የትኛውም ውጫዊ መልካምነት ወይም የትምህርት ፍጽምና ራስን ፈጽሞ ለክርስቶስ የመስጠትን እና የእርሱን ፈቃድ ሥፍራ መውሰድ አይችልም፡፡

በውስጣችን ለሚኖረው ክርስቶስ ብቻ የምንሰጠው ደቀ-መዛሙርነት የተወሰኑ የግድ ልናከናውናቸው የሚገቡ ነገሮች አሉት፡፡ ማንኛውም ይህንን የሚሻማና የሚተካ ነገርን አይፈቀድም፡፡

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለግንቦት 29 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

## እሁድ ግንቦት 23 2007 ዓ.ም

## ከፈሪሳዊነት ሽሹ

በወንጌላት ውስጥ ከተፃፉት ፈሪሳውያንን ከሚጠቅሱ 80 ነገሮች ወደ 24ፐርሰንት የሚሆኑት የተፃፉት በሉቃስ ወንጌል ነው፡፡ ፈረሳውያን ከሰዱቃውያኑ ነፃ እና እንደፈለግን ከሚለው አስተሳሰብ በተቃራኒው እጅግ ወግ አጥባቂዎች ነበሩ፡፡ ፈሪሳውያን በእግዚአብሔር ፀጋ እናምናለን የሚሉ ሆኖም ግን ህግን በመጠበቅ መዳን ይቻላል ብለው የሚያስተምሩ ህጋውያን ነበሩ፡፡

ሉቃስ 11፡37-54 ያንብቡ፡፡ ኢየሱስ እያስጠነቀቀ ያለው ስለምንድን ነው? ይህ ተመሳሳዩ ነገር ዛሬ የሚታየው እንዴት ነው? እኛ ራሳችን በመንገዳችን እነዚህን ክርስቶስ ያስጠነቀቃቸውን ነገሮች አለማንፀባረቃችንን እርግጠኛ የምንሆነው እንዴት ነው?

*በፈሪሳውያንና በፀሐፍት ላይ የተነገረው ወዮ (ሉቃስ 11፡42-54) እውነተኛው የሃይማኖት ጥሪ እኛን ጨምሮ ትውልድን አልፎ የሚመጣ የመሆኑ ማሳያ የሚሆነው እንዴት ነው?*

________________________________________________________

________________________________________________________

ለምሳሌ አሥራት እግዚአብሔር ለሰጠን በረከት በደስታ የሚመለስ ሲሆን ፤ በምንም ሁኔታ በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን ፍቅርንና ቅን ፍርድን ሊተካ ግን አይችልም፡፡ (ቁ. 42)

እነዚሁ ሰዎች "ቅን ፍርድንና እግዚአብሔርን መውደድ ችላ የሚሉ " በዚህ ፋንታ ግን " በምኩራቦች የከፍታ ሥፍራዎችን ይይዛሉ" (ቁ. 42፡43) ትክክለኛውን እምነት ነጥብ ስለ መሳት ተነጋገሩበት፡፡

ኢየሱስ እውነተኛውን ሃይማኖት ከውጫዊ የልማድ አገልግሎት ጋር እኩል አድርገው የሚያዩትን ልክ ከሙታን ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ሰዎች ንፅህና የጎደላቸው እንደሆኑ አስጠንቅቋቸዋል፡፡ (ሉቃስ 11፡44፤ ዘሌ. 19፡16) በእግዚአብሔር እይታ ቅዱስ የሆነውንና የማይረባ ዋጋ ቢስ የሆነውን ነገር አደናጋሪ አድርጎ ማቅረብ ሰዎች ምን ያህል እንደሚቀላቸው ይመልከቱ፡፡

ኢየሱስ እነርሱ "በአንዱ ጣታቸው ጫፍ የማይነኩትን ሸክም" (ሉቃስ 11፡46) ለመሸከም ከባድ የሆነን የሃይማኖት ሸክም በሌሎች ላይ የሚያሸክሙት የህግ አዋቂዎችን ወዩላቸው አላቸው፡፡

በተመሳሳይ ዘመን ፈሪሳውያን ያለፉትን ነቢያት የሚያከብሩ ሲሆኑ በህይወት ካሉት ጋር ግን ተቃራኒ ነበሩ፡፡ ኢየሱስ እንደተናገረው የሰውን ልጅ ለመግደል ያሴሩ ነበር፡፡ ዋናው ነገር ነቢያትን ማክበር ሳይሆን የእነርሱን ትንቢታዊ የፍቅር፣ የምህረት እና የፍርድን መልዕክት ማስተዋል ነው፡፡

የመጨረሻው ወዮ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ቁልፍ ያለው ሰው በእነርሱ እጅ ወድቋል፡፡ ቁልፉን በጥበብ ተጠቅሞ የእግዚአብሔር ህዝብ ወደ መንግሥቱ በማስገባት ፈንታ በውጭ ዘግተውባቸው ቁልፉን ጥለዋል፡፡

## ሰኞ ግንቦት 24 2007 ዓ.ም

# እግዚአብሔርን ፍሩ

"እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት "(ራዕይ 14፡7) ከሦስቱ መላዕክት መልዕክቶች የመጀመሪያው ሲሆን ለአድቬንቲስት እምነትና ህይወት ማዕከል ነው፡፡ እግዚአብሔርን





መፍራት ብዙውን ጊዜ እንደሚሠጠው ትምህርት ከፍርሃት የተነሳ መስጋት ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን የእርሱን ማንነት ማወቅና እርሱ ከእኛ የሚፈልግብንን መረዳት ማለት ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ ራስን ለኢየሱስ በማስገዛት የእምነት ማሳያ ድርጊት ነው፡፡ እግዚአብሔርም በህይወታችን የግንኙነታችን፣ የአስተሳሰባችን፣ እንዲሁም የፍጻሜአችን ድንጋጌ አውጭና አስታራቂያችን ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት ላይ የቆመ ደቀ-መዝሙርነት በማይንቀሳቀስ መሬት ላይ የፀና ነው፡፡

**ሉቃስ 12፡4-12ን ያንብቡ፡፡ በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ስለ ፍርሃት ምን እያለ ነው?**

__________________________________________________________

__________________________________________________________

ንባቡ ማንን መፍራት እንዳለብንና ማንን መፍራት እንደሌለብን ያሳያል፡፡ በዚህ ዓለም ሥጋን ብቻ የሚጎዱትን መፍራት እንደሌለብን ይገልፃል፡፡ በምትኩ ግን እግዚአብሔርን ልንፈራ ይገባናል ምክንያቱም የእኛ ዕድል ፈንታ በእጁ ነውና፡፡ ነገር ግን ለድንቢጦች (ለወፎች) እንኳን የሚጠነቀቀው አምላክ (ሉቃስ 12፡6) የፀጉራችንን ልክ ቆጥሮ የሚያውቀው (ቁ. 7) እርሱ አፍቃሪና ወዳጅ በመሆኑ እያንዳንዳችን በእርሱ ፊት ለዘለዓለም ውድ ነን፡፡ እኛ ይህን በእውነት ካመንን ምን ያህል የምድር ጭንቀቶች ከእኛ ይወገዱ ይሆን!

ሉቃስ 12፡ 13-21 ያንብቡ፡፡ በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ እያስጠነቀቀን ያለው ስለምንድን ነው?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

ኢየሱስ ንብረት ክፍፍልን በሚመለከት በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል መግባት ባያስፈልገውም የአሥረኛው ትዕዛዝ አስፈላጊነትና (ዘፀ 20፡17) የምኞትን ክፋት በመግለጽ ለዘመናት ሁሉ የሚሆን እውነትን ይህም ህይወት የተሠራው ለቁሳዊ ነገሮች አለመሆኑን (ሉቃ 12፡15) አሳይቷል፡፡ ሰነፍ የሆነ ሀብታም ሰው በዚህች ትንሽ ዓለም ለራሱ ብቻ ተወስኖ ይኖራል፡፡ ለእርሱ ሌላ ነገር ጉዳዩም አይደለም፡፡ በዚህ አይነት ወጥመድ እንዳንወድቅ ምን ያህል መጠንቀቅ ያስፈልገናል፡፡ በተለይም በብዙ ቁሳዊ ነገሮች የተባረኩት፡፡

*ምንም እንኳን ሁላችንም ቁሳዊ ነገሮች የሚያስደስቱን ቢሆንም፤ ከእነርሱ ልናገኝ የምንችለው ደስታ ምን ያህል አነስተኛ መሆኑን ይመልከቱ፤ በተለይም በዘለዓለማዊነት እይታ ታዲያ ኢየሱስ በሉቃ 12፡16-21 በሰጠው ማስጠንቀቂያ ላይ ስህተት ማድረግ እስከ አሁን ድረስ ቀላል የሆነው ለምንድን ነው?*

**ማክሰኞ** ግንቦት 25 2007 ዓ.ም

# የተዘጋጃችሁና የምትጠነቀቁ ሁኑ

*ታማኝነትና ንቃት በዘመናት ሁሉ ለክርስቶስ ተከታዮች አስፈላጊያቸው ነበር፤ አሁን ግን እኛ በዘለዓለም ህይወት ዳርቻ ላይ የምንሠራውን እምነት ታላቅ የሆነ ብርሃን እጅግ አስፈላጊ ሥራ ይዘን ስለምንገኝ ትጋታችንን እጥፍ ልናደርገው ይገባናል፡፡ Ellen G. White, Testimonies for the Church, Vol.5, pp.460,461.*

ሉቃስ 12፡35-53 ያንብቡና በአጭር ሲያጠቃልሉት በተለይም ለረዥም ጊዜ ጌታ ይመጣል ብለው ጠብቀው ከሆነ ለእርስዎ ይህ ጥቅስ ምን ማለት እንደሆነ ይመልከቱ፡፡

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ክርስቲያኖች ግድየለሽና ልፍስፍስ መሆን የለባቸውም፡፡ የመምጣቱ እውነተኛ መሆን የጊዜው አለመታወቅ ልብሳችን የፀዳ እና ኩራዛችን እየበራ መሆኑን እንድንገነዘብ ያስገድደናል፡፡ የክርስቶስ ምፃት ተስፋ የህይወታችንና የሥራችን የዝግጅታችንና የታማኝነታችን ማስጠበቂያ ኃይል ነው፡፡ የታማኝና የከፉው አገልጋዮች ልዩነት የሚሆነውም ይህ ፈቃዱን ለማድረግ ታማኝ መሆን እኛም እርሱን በሰላም ለመገናኘት ተዘጋጅቶ መጠበቅ ነው፡፡

"ጌታዬ ይዘገያል" በሚል ሀሳብ ታማኝነትን መተው (ሉቃስ 12፡45) ራስን አስከፊ በሆነ በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር ያደርጋል፡፡ የተሻለ እድል የበለጠ ኃላፊነት ይጨምራል፡፡ ስለዚህ "ብዙ ከተሰጠው ብዙ ይጠበቅበታል" (ቁ. 48)





የጥንቱ ነቢይ እንዳለው "በጽዮን ተዘልለው ለተቀመጡት ወዮላቸው" አሞ 6፡1 ያለው ኢየሱስ ለክርስቲያን ደቀመዛሙርቱ ለሠጠው ማስጠንቀቂያ ነፀብራቅ ነው፡፡ ጳውሎስ የክርስቲያንን ህይወት በመንፈሳዊ ውጊያ ላይ መሆኑን ያመለክታል (ኤፌ. 6፡12) ዋናው ነጥብ እያንዳንዱ ክርስቲያን በፍጥረተ ዓለም ውስጥ በክርስቶስና በሰይጣን መካከል በሚደረገው ታላቅ ተጋድሎ ውስጥ ተሳታፊ መሆኑ ሲሆን እናም መስቀሉ በሁለቱ መካከል መለያ መስመር መሆኑን ማወቅ ነው፡፡ አንድ ሰው አሸናፊነትን ሊቀዳጅ የሚችለው ሳያቋርጥ በክርስቶስ መስቀል ላይ ባለው እምነት ብቻ ነው፡፡

*"ብዙም ከተሠጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል ብዙ አደራም ከተሠጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል" (ሉቃስ 12፡48) ይህ ጥቅስ ለእኛ አድቬንቲስቶች ምን ማለት ነው?*

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**ረቡዕ** ግንቦት 26 2007 ዓ.ም

# ፍሬያማ ምሥክር ሁን

አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ "ዓለም ከመፈጠሩ በፊት" (ኤፌ. 1፡4) በነበራቸው ምክር የደህንነት ዕቅድ ዘረጉ፡፡ ያም ገና የመጀመሪያው ሰው ሳይፈጠር የመጀመሪያውም ኃጢአተኛ ሰው ኃጢአት ሳያደርግ እግዚአብሔር ዓለምን የማዳን ዕቅድ ነበረው፡፡ የመመስከሩ ኃላፊነት ደግሞ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ላይ ተጥሏል፡፡

"በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማሪያም እስከ ምድር ዳርቻ ምሥክሮቼ ትሆናላችሁ" (ሐዋ. 1፡8) ኢየሱስ በማጠቃለያው አስምሮ የተናገረው ለተከታዮቹ የምሥክርነትን አስፈላጊነትና ሚና የሚያጎላ ነበር፡፡

*ከዘሪውና ከመሬቱ ምሳሌ (ሉቃስ 8፡4-15) የክርስቲያን ምሥክሮች መውሰድ ያለባቸው ትምህርት ምንድን ነው?*

______________________________________________________________

*ምሥክርነት ውጤቱ መቼና ምንድነው? (ሉቃስ 18፡ 24-30)*

*የምናኑ ምሳሌ (ሉቃስ 19፡11-27) ስለ ታማኝነትና ኃላፊነት የሚስተምረን ምንድነው? በእነዚህ ጥቅሶች በእያንዳንዳቸው አደጋው፣ ኃላፊነቱ፣ የምሥክርነትና የእምነት ሽልማቶች ተገልፀዋል፡፡ ታላቅ ኃላፊነት ተጭኖብናል፤ ነገር ግን የተሠጠንን ከግምት ውስጥ ስናስገባ የተጠየቅነው ምን ያህል አናሳ ነው?*

## ሐሙስ ግንቦት 27 2007 ዓ.ም

# አገልጋይ መሪ ሁን

*ሉቃስ 22፡24-27ን ያንብቡ፡፤ ደቀ-መዛሙርት እስከ መጨረሻው ራት ግብዣ ድረስ እንኳ በመንግሥቱ ከእነርሱ ማን ታላቅ እንደሚሆን በውስጣቸው ክርክር ነበር፡፡ ኢየሱስ ለስንፍናቸው የሰጠው ምላሽ ምንድን ነበር? ምላሹ ታላቅ ለውጥ የሚያመጣ የነበረው እንዴት ነው?*

በመሪነት ታሪክ ውስጥ የኢየሱስ ምላሽ የተለየ ነበር፡፡ ፈርኦን ናቡከደናፆር ቄሳርና ናፖሊዮን ሁሉም መሪነትን በሌሎች ላይ የሚተገብር ኃይልና ሥልጣን እንደሆነ ተመልክተዋል፡፡ ይህም ሰዎች ኃይልን በተመለከተ ሁሌም የሚሠሩት እንዲህ ነበር፡፡

"እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ፤ ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን" (ሉቃስ 22፡26)፡፡ የዓለማት ጌታ በዚህ አባባሉ የመሪነትን ትርጓሜ ገልብጦታል፤ "በእናንተስ እንዲህ አይደለም ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሠጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም" (ማቴ. 20፡26-28)

ኢየሱስ በዚህ ስለ አገልጋይነትና ራስን ስለ መካድ በሰጠው መርህ መግለጫ የእርሱ መንገድና መሪነት በሰው ልጆች መካከል ባለው ግንኙነት አዲስና ኃይለኛ የሆነ ነገርን አስተዋውቋል፡፡ ቃልን መጠበቅ የሚመጣው በኃይል ሳይሆን ከአገልጋይነት ነው፡፡ መሪነት ሥልጣንን የሚያገኘው ከተሠጠው ደረጃ ሳይሆን ከአገልግሎት ለውጥ የሚጀምረው በዙፋን ላይ ሳይሆን በመስቀል ነው፡፡ "ለመኖር መሞት" (ዮሐ. 12፡24)፡፡





ሉቃስ 9፡46-48 በመካከላችን ታላቅ ማን ነው? በሚሉ ደቀ-መዛሙርት መካከል ጥያቄ ተነስቶ ነበር፡፡ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ዓለማዊ የሆኑ መመሪያዎች የጌታን ደቀመዛሙርት አእምሮ ጠምዝዞት ነበር፡፡

የጌታም ምላሽ የችግሩን ልብ በመንካት አጠቃላይ የህይወት ግድድሮሽና ችግር የሚሆነውን በተለይም የክርስቲያን ህይወት ውስጥ የሚገኝ ችግርን ቆም የሚያደርግ ነበር፡፡ የኢየሱስ ቃላት በተለይም "ከሁላችሁ የሚያንስ"(ቁ. 48) የሚለው በዓለም ቅድሚያ የሚሠጣቸው ነገሮች ምን ያህል ኃላ ቀር መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

*በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ያስተማረው ሙሉ በሙሉ ከዓለም መመሪያ ተቃራኒ የሆነውን ሲሆን ይህንን በህይወታችን ብንተገብረው አኗኗራችን ምን ዓይነት ይሆን ነበር?*

## ዓርብ ግንቦት 28 2007 ዓ.ም

**<u>ለተጨማሪ ጥናት</u>፡-** "ልብ ያለው ማን ነው? ሐሳባችን ከማን ጋር ነው? ከማን ጋር መነጋገር እንወዳለን? የሞቀ ፍቅራችን እና የተመረጠው ኃይላችን የማን ነው? የክርስቶስ ከሆነስ ሀሳባችን ከእርሱ ጋር ይሆናል፡፡ በውስጣችን የሚኖሩ የሚሞቁ አስተሳሰቦቻችን ከእርሱ ይሆናሉ፡፡ ያለን ሁሉ ለእርሱ የተሠጡ ይሆናሉ፡፡ እኛም የእርሱን ምስል መሸከም እንናፍቃለን የእርሱን መንፈስ እንተነፍሳለን ፈቃዱን እናደርጋለን እናም በሁሉ ነገር እርሱን ደስ እናሰኛለን፡፡" *Ellen G. White, Steps to Christ , p. 58.*

"በዚህ ምድር ላይ በህይወት ስንኖር አስተሳሰባችን በኃጢአት የተገደበ ነው፡፡ ስለዚህ ታላቁ ደስታና ትምህርት በአገልግሎት ውስጥ ነው፡፡ ወደፊት በሚኖረን ሁኔታ ኃጢአተኛ በሆነ ሰብዓዊነት የመንቀሳቀስ ኃይሉ ባልተገደበበት ታላቁ ደስታችንና ከፍተኛው ትምህርታችን ምሥክር ይሆናል እኛም ይህን ለዘላለም ስንመሰክር የታላቁን ሀብትና ክብር ምሥጢርን እናውቃለን፡፡ "ለእነርሱም እግዚአብሔር በአህዛብ ዘንድ ያለውን የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደሆነ ሊያሳውቅ ወደደ" (ቆላ. 1፡27) *Ellen G.White , steps to Christ, p. 58.*

## የውውይት ጥያቄዎች፡-

❶ *ኢየሱስ ሀብታሙንና የተሳካለትን ገበሬ ሰነፍ ብሎ ጠራው (ሉቃስ 12፡20) አንድ ሰው ሀብታምም የተሳካለትም ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር እይታ ሰነፍ የሚያሰኘው ምንድን ነው?*

❷ *በአንዳንዶቹ ቤተክርስቲያኖቻችን ሁለት መደቦችን እናያለን፡፡ የመጀመሪያው እውቀት ያላቸው ገንዘብ ያላቸው የቤተክርስቲያንና የማህበረሰቡ መሪዎች እናም ተፅዕኖ ፈጣሪዎች በሁሉም የሚታዩ ክብር ያላቸው ናቸው፡፡ ሁለተኛው ዝምተኞችና በሰው የማይታዩ ማንም ስለ እነርሱ ሳያስታውስ ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጡና የሚሄዱ ናቸው፡፡ ሁለተኛው መደብ ውስጥ ያሉትን ልክ በመጀመሪያው መደብ ውስጥ እንዳሉት ተፈላጊ መሆናቸውን እንዲያውቁ እርስዎ ምን ያደርጋሉ?*

❸ *ምንም እንኳን ዛሬ ፈሪሳውያንን የእምነትን መንገድ በሌላ በመተርጎማቸው መውቀስ ቀላል ቢሆንም፤ ነገር ግን እኛ የእምነት ግለቱ ያለን ሰዎች በተመሳሳይ አደገኛ ሁኔታ ስህተት አለመፈጸማችንን እርግጠኞች ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው? ፈሪሳዊ ሳንሆን እውነት ለሆነው ነገር መቆም የምንችለው እንዴት ነው? ወይም አስፈላጊና ጠቃሚ የሆነውን ትግል ልንለይ የምንችለው እንዴት ነው?*

❹ *እያንዳንዱ ዓመት ባለፈ ቁጥር ንቁ መሆን እየቀነሰ በሚመጣበት ሁኔታ ውስጥ እያለን ለኢየሱስ ምፃት ንቁና ዝግጁ ሆነን ልንጠብቅ የምንችለው እንዴት ነው?*





# 11ኛ ትምህርት

ከግንቦት 29-ሰኔ 5 2007 ዓ.ም

# የእግዚአብሔር መንግሥት

### ሰንበት ከሰዓት

**ለዚህ ሳምንት ጥናት፡-** ሉቃስ 11፡2፤ ሉቃስ 1፡32፤ 33 ፤ 18፡ 16-30፤ ሉቃስ 17፡23፡24 ራዕይ 21፡1-3 ፤ ሉቃስ 21፡34-35ን ያንብቡ፡፡

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡-** "እነርሱም ከምሥራቅ ከምዕራብ ከሰሜንና ከደቡብ ይመጣሉ፤ በመንግሥቱም ይቀመጣሉ" *(ሉቃስ 13፡29)*

በኢየሱስ ትምህርት ርዕሱና ዋነኛ ቅድሚያ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው፡፡ ይህም ሀረግ በማቴዎስ ወደ 50 ጊዜ በማርቆስ 16 ጊዜ በሉቃስ ወደ 40 ጊዜ እና በዩሐንስ ወንጌል 3 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ በጌታችን ፀሎት ወይም በተራራው ስብከት ወይም በክርስቶስ ስብከቶችና በምሳሌዎቹ ውስጥ በማንኛውም በተጠቀሰበት ሥፍራ ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት እግዚአብሔር በሰብዓዊ ዘር ታሪክ ታላቁን ተጋድሎ ወደ ፍጻሜ ለማምጣትና ኃጢአትንና ተያያዥ የሆኑ ችግሮችን በተመለከተ እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ የሚገልጽ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እስከአሁን ዓለም ከሚያውቃቸው መንግሥታት ሁሉ ይለያል ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት ዓለማዊ መንግሥት አይደለም፡፡

"የእግዚአብሔር መንግሥት በውጫዊ ታይታ የምትመጣ አይደለችም። የእግዚአብሔር መንግሥት የምትመጣው ከቃሉ የተነሳ በሚያነሳሳ በጨዋነት መንፈስ በውስጣችን በሚሠራው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነፍስ ህይወቷ ከሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባላት ህብረት ነው። የእርሱም ታላቅ መገለጫ ክርስቶስን በመምሰል ወደ ፍጽምና በደረሰ በሰው ልጅ ባህርይ ይሆናል።" *Ellen G. White , The Ministry of Healing, P.36*

በዚህ ሳምንት በዚህ ርዕስ እናተኩራለን፤ በተለይም በሉቃስ መጽሐፍ እንደተገለጸው ዓይነት።

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለሰኔ 6 ሰንበት ይዘጋጁ።**

## እሁድ ግንቦት 30 2007 ዓ.ም

## የእግዚአብሔር መንግሥት ባህሪይ ክፍል 1

ወንጌሎች ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት መገለጫ በተመለከተ የተሟሉ ናቸው። ሁሉም በአንድነት በኢየሱስ ክርስቶስና በእርሱ አማካይነት ተመርቆ የተከፈተውን አዲሱን ሥርዓት ይመሰክራሉ።

*ሉቃስ 11፡2 ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምን ይላል? ይህ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው?*

__________________________________________________________

__________________________________________________________

ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው ብሎ መናገር ዝም ብሎ ግልጽ የሆነውን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንግሥት የፍልስፍና ጉዳይ ወይም የሥነ-ምግባር አስተምህሮም ብቻ እንዳልሆነ መስማማት ነው። እርሱም ለተራቡት እንጀራ ለተጠሙት ውኃን እንዲሁም ለተጨቆኑት ነፃነትን የሚያውጅ ዝም ብሎ የማህበረሰብ ወንጌል አይደለም። እርሱ ማንኛውም ሥጋ በለበሰው ሁሉን ቻይ በሆነ እግዚአብሔር ወልድ የመንግሥቱ መልካም የምሥራች መጥቶ በሰበከው በእርሱ ላይ በተመሠረተ ነው። (ሉቃስ 4፡42-44 ፤ ማቴ. 4፡ 23-25)





*ሉቃስ 1፡32.33 ተመርቆ ስለ ተከፈተው የእግዚአብሔር መንግሥት እና የመጨረሻው ውጤትን በሚመለከት ምን ያስተምረናል?*

ንባቡ ለሁለት ታላላቅ ምክንያቶች አስፈላጊ ነው። የመጀመሪያው በብሉይ ኪዳን ተስፋ ተደርጎ የተጠበቀው ከኢየሱስ ሌላ ማንም እንዳልሆነ "የልዑል ልጅ " ሁለተኛ "መንግስቱ ፍፃሜ የሌለው" መሆኑን ነው። ይህም ማለት በእርሱ ሥጋ መልበስ ሞቱና ትንሣኤው ኢየሱስ ሰይጣን በእግዚአብሔር ታላቅነት ላይ ያለውን ግድድሮሽ አፍርሶ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለዘለዓለም መሠረተው። "የዓለም መንግሥታት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች ለዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይነግሣል" (ራዕይ 11፡15)። በክርስቶስ እና በሰይጣን መካከል በነበረው ግጭት ሰይጣን በአዳምና ሔዋን ውድቀት ምክንያት አሸናፊነት የእርሱ እንደሆነ አስቦ ነበር። ነገር ግን የኢየሱስ ተልዕኮ የሰይጣንን ስህተት አረጋግጧል፤ እርሱ ሰይጣንን በእያንዳንዱ ነገር አሸንፎታል። እንዲሁም በሞቱና በትንሣኤው ለዓለማት ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣቱን አረጋግጧል።

*የእግዚአብሔርን መንግሥት እርግጠኝነት በሚገልፅ መልኩ መኖር የምንችለው እንዴት ነው? በተለየ መልኩ ይህንን እውነታ በህይወታችን ልንገልፅ በምንችልበት ሁኔታ መኖር የምንችለው እንዴት ነው? አሁን እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች መኖር ብንችል ልዩነቱ ምንድን ነው?*

__________________________________________________________

__________________________________________________________

## ሰኞ ሰኔ 1 2007 ዓ.ም

## የእግዚአብሔር መንግሥት ባህሪይ፡ ክፍል ሁለት

*በእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች ስለመሆን የሚከተሉት ጥቅሶች ምን ያስተምሩናል?*

ሉቃስ 18፡ 16-30 ____________________________________________

__________________________________________________________

ሉቃስ 12፡ 31-33————————————————————————

————————————————————————————————

ሉቃስ 9፡ 59-62 ————————————————————————

————————————————————————————————

ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት በአንድ ሰው የሥልጣን ደረጃ በሀብቱ ወይም በማጣቱ ላይ የሚመሠረት አይደለም፡፡ ሉቃስ ከሌሎቹ የወንጌል ፀሀፍት ጋር በመሆን አንድ ሰው በማያወላውል ፍጹም ራስን አሳልፎ በሠጠ ባህሪይ ሙሉ በሙሉ በእርሱ በመደገፍ እንዲሁም እንደ ህፃን በሆነ ፍጹም እምነት ወደ ኢየሱስ መምጣት እንዳለበት ይጠቁማል፤ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የገቡ ሠዎች ባህሪያቸው ይህን ይመስላል፡፡ እነርሱ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሁሉንም ነገር ስለ እርሱ ይተዋሉ፡፡ ማንኛውም ሊተውት የማይፈልጉት ነገር ከኢየሱስ ጋር መሻማት ብቻ ሳይሆን በእርግጥ ሊያሸንፋቸው ይችላል፡፡ በማንኛውም የህይወታችን አቅጣጫ ኢየሱስ በህይወታችን የሚፈልገው ነገር በኑሮአችን ከፍተኛውንና የፊተኛውን ሥፍራ ሊይዝ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ በእርግጥ ሁለመናችን ለእርሱ ያስፈልገዋል፡፡

ሉቃስ 18፡ 29፡30 እንደገና ያንብቡ፡፡ ኢየሱስ ለእኛ የሚለውና ተስፋ እየሠጠን ያለው ምንድን ነው? ወላጆቻችንን ሚስቶቻችንን እንዲያውም ልጆቻችንን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እንድንተው ነው? ይህ ታላቅ ዋጋ የሚያስከፍል ነገር ነው፡፡ ኢየሱስ እያለ ያለው እነዚህ ድርጊቶች ከሁሉም አማኞች ይፈለጋሉ ሳይሆን ነገር ግን ምናልባት አንድ ሰው እነዚህን ነገሮች እንዲተው ቢጠራ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእነዚህ ሁሉ ይበልጣል ማለቱ ነው፡፡

*ሙታን ሙታናቸውን ይቅበሩ በሚለው የኢየሱስ አባባል ላይ ይወያዩ፡፡ እርሱ በሚጠራን ጊዜ ምክንያቶቻችን ምንም ያህል ትልቅ ቢሆኑ ምክንያት መስጠት እንደማይገባን ምን አስፈላጊ እውነት እየነገረን ነው?*

————————————————————————————————

————————————————————————————————





## ማክሰኞ ሰኔ 2 2007 ዓ.ም

# የእግዚአብሔር መንግሥት በአሁን ጊዜ እና ገና ወደ ፊት

ኢየሱስ የመጣው የእግዚአብሔርን መንግሥት እያወጀ ነበር፡፡ ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለህዝብ በግልጽ በተናገረበት በናዝሬቱ ምኩራብ (ሉቃስ 4፡ 16-21) በኢሳያስ ትንቢት አማካይነት ስለ መሲሁ እና ስለ መንግሥቱ ስለ እርሱም የነፃ አውጪነት አገልግሎት የተናገረው ትንቢት ተመርቆ መጀመሩን አረጋግጧል፡፡

ሉቃስ መንግሥቱን አሁን እውን መሆኑን የሚመሰክሩ ቃላትና ዘገባዎችን ያቀርባል፡፡ ፈሪሳውያንም የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ እንደምትመጣ ሲጠይቁት ኢየሱስ "የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን በውስጣችሁ ናት" (ሉቃስ 17፡21) በማለት መልሷል፡፡ ሌሎች ትርጉሞች የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን በመካከላችሁ ናት ይላሉ፡፡ ይህን ማለት ኢየሱስ በመጣ ጊዜ መንግሥቱ ያኔውኑ መጥቷል ማለት ነው፡፡ በሽተኞችን መፈወስ (ሉቃስ 9፡11) ወንጌልን መስበክ (ሉቃስ 4፡16) ኃጢአትን ይቅር ማለት (ሉቃስ 7፡48-50 ፤ 19፡9-10) እና የክፉውን ኃይል ማፍረስን በውስጡ አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ መንግሥቱን በግለሰብ ውስጥ በመሆን እርሱን ወደ መምሰል የሚለውጥና አሁን ያለ መሆኑን አሳይቷል፡፡ የእግዚብሔር መንግሥት በአማኞች ማህበረሰብ መካከል ደግሞ የፅድቅና የደህንነት መገለጫ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት የአሁን መገለጫ የፀጋ መንግሥት በመሆን አሁን ተመስርቷል፤ በዚህም ዕለት በዕለት በኃጢአት የተሞሉ ልቦች ወደ እግዚብሔር ኃያልነትና ፍቅሩ ይማባሉ፡፡" *Ellen G,White , Thoughts from the mount of blessing, p. 108.*

የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን የሚለው እውነት የኃጢአትንና የሰይጣንን ሽንፈት እና የኢየሱስ ክርስቶስን በታላቁ ተጋድሎ ላይ የተቀናጀውን አሸናፊነት የሚያሳይ ሲሆን "ገና" የሚለው ደግሞ ወደፊት ሊመሠረት ያለውን አዲሱን ምድር እና የክፋትን መጨረሻ የሚያመለክት ነው፡፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም እስኪመጣ ድረስ የክብር መንግሥቱ በዚህ ዓለም በሙላት አይመሠረትም"

*እነዚህን ጥቅሶች በፍጻሜ ዘመን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምን ያስተምሩናል? ሉቃስ 17፡23፤ 21፡5-36 ፡፡*

የእኛ ዓለም እና ሁኔታ ብጥብጡ ኃዘኑ እና መከራው በእርግጠኝነት ኢየሱስ በቃሉ በዚህ ሥፍራ የተናገረውን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን አንዳንዶች ይህ ዓለም የመከራና የሥቃይ መሆኑ እግዚአብሔር የለም ማለት ነው ቢሉም እኛ ግን ኢየሱስ ከ2000 ዓመታት በፊት እንዳስጠነቀቀው የዚህ ዓለም ሁኔታ የሚያረጋግጠው የእግዚአብሔርን መኖር ብቻ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት ጭምር ነው፡፡ (ዓለማችን አሁን ገነት ብትሆን የክርስቶስ ቃላት ውሸት በሆኑ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በሙላት የሚመሠረተው በመጨረሻ ብቻ ነው፡፡ እስከዚያ ድረስ መጽናት ይገባናል፡፡

**ረቡዕ** ሰኔ 3 2007 ዓ.ም

# የክርስቶስ ዳግም ምፃትና መንግሥቱ

ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲናገር ሁለት እውነቶችን ተናግሯል፡፡ 1ኛ. እግዚአብሔር በታሪክ በኢየሱስ አማካይነት ሰብዓዊውን ዘር ከኃጢአት ለማዳን እያደረገ ያለውን ተግባር እና 2ኛ. እግዚአብሔር የዳኑትን ወደ ቀድሞ እቅዱ በመመለስ የታሪክን ፍጻሜ ማድረጉን ያም አዲስ በተፈጠረችው ምድር ከእርሱ ጋር አብረው ለዘለዓለም መኖር (ራዕ 21፡1-3) የመጀመሪያው ተጠቅሶ እንደነበር በኢየሱስ ተልዕኮና አገልግሎቱ ተከናውኗል፡፡ እኛ አሁን የምንኖረው በእርሱ የፀጋ መንግሥት ነው፡፡ (ኤፌ 1፡4-9)፡፡ ሁለተኛው ክፍል የዳኑት በክብር መንግሥቱ መሰብሰብ በኢየሱስ የሚኖሩት ወደፊት የሚጠባበቁት ተስፋ ነው፡፡ (ኤፌ 1፡10 ፤ ቲቶ 2፡13) ኢየሱስና ሌላው የአዲስ ኪዳን ክፍል የእግዚአብሔር ታማኞች መንግሥቱን የሚወርሱበትን ታሪካዊ ጊዜን ከኢየሱስ ዳግም ምፃት ጋር ያገናኛሉ፡፡

የክርስቶስ ዳግም ምፃት ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደዚህ ምድር መጥቶ ሳለ ያወጀው መልካም ዜና መደምደሚያ ነው፡፡ ያው ኃጢአትንና ሰይጣንን በቀራኒዮ ያሸነፈው ኢየሱስ በቶሎ ክፋትን በማስወገድ ይህችን ምድር ሰይጣን የእግዚብሔር ፍጥረት ላይ ካመጣው ክፉ ነገር ያፀዳል፡፡

*ሉቃስ 21፡34-36 ያንብቡ፡፡ በራስዎ ቃላት መሠረታዊ የሆነውን መልዕክት ያጠቃልሉት፡፡ ይህን ሲያደርጉ ህይወትዎን በመመልከት ይህ እንዴት እንደሚተገበር ያስቡ፡፡ ኢየሱስ በዚህ*





*ሥፍራ እንደሚናገረው እርሱን መከተልዎን እርግጠኛ ለመሆን ምን ማድረግ ይገባዎታል?*

________________________________________________

________________________________________________

የኢየሱስን መመለስ ስንጠባበቅ እንድንጠነቀቅ ተጠርተናል፡፡ የተገባን ሆነን እንድንገኝ ሁልጊዜ መጸለይ ይገባናል፤ በሰው ልጅ ፊት መቆም እንድንችል (ቁ. 36)

እነዚያ የፀጋውን መንግሥት የተለማመዱ ለክብር መንግሥቱ መፀለይ መጠንቀቅና መትጋት ያስፈልጋቸዋል፡፡ በአንዱና በሌላኛው አሁን ባለውና ወደፊት ሊገለጽ ባለው አማኞች በኑሮና በተስፋ በአገልግሎትና በተልዕኮ በምሥክርነትና በማስተማር የተሞሉ ናቸው፡፡ ዳግም ምፃቱን መጠባበቅ በአሁን ኑሮአችን ቅድስናን የሚፈልግ ነው፡፡

**ሐሙስ** ሰኔ 4 2007 ዓ.ም

# ምሥክሮች

*ሐዋ. 1፡1-8 ያንብቡ፡፡ በዚህ ሥፍራ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የተገለፀው አስፈላጊ እውነት ምንድን ነው?*

________________________________________________

________________________________________________

ሉቃስ ወንጌሉን በተከታታይ እየፃፈ ሳለ የእግዚአብሔር መንግሥት ነገር በእርሱ አእምሮ ውስጥ የምድራዊ ቤተክርስቲያን ግልፅ ታሪክ ሆኖ ይታየው ነበር፡፡ በታሪኩ የመጀመሪያ መስመሮች ሉቃስ በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን መንግሥት በሚመለከት ሦስት ዋና ዋና እውነቶችን ይገልፃል፡፡

**የመጀመሪያው፡-** በእርግጥ ኢየሱስ ዳግም ይመጣል፡፡ በትንሣኤውና በእርገቱ መካከል በነበሩ 40 ቀናት ከመስቀሉ በፊት ሲያስተምራቸው የነበረውን ትምህርት ማስተማሩን ቀጠለ፤ "የእግዚአብሔርን መንግሥት ነገር እየነገራቸው" (ሐዋ. 1፡3)፡፡ በመስቀሉ ላይ የተከሰቱት ታላላቅ ክስተቶችና ትንሣኤው የእግዚአብሔርን መንግሥት በተመለከተ አዲስ

ትምህርት አላመጡም፡፡ ይህ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ከሙታን የተነሳው ጌታ በአርባው ቀን ስለ መንግሥቱ ተጨማሪ እውነቶችን ባስተማራቸው ነበር፡፡

**ሁለተኛው፡-** የክርስቶስ ዳግም ምፃት እግዚአብሔር ራሱ በወሰነው ጊዜ እንደሚሆን ነው፡፡ ከትንሣኤው በኋላ ደቀ-መዛሙርቱ ኢየሱስን ጠንከር ያለ ሥጋት ያለበት ጥያቄ ጠየቁት፡፡ "ጌታ ሆይ በዚህ ወራት ለእሥራኤል መንግሥት ትመልሣለህን? (ሐዋ. 1፡6)፡፡ ኢየሱስ የደቀ -መዛሙርቱን አመለካከት አስተካከለ እንጂ መልስ አልመለሰም፤ እግዚአብሔር ሁሌም እግዚአብሔር ነው፡፡ አእምሮውን ለመመርመር፣ ዕቅዱ በትክክል በጊዜው መፈጸሙን ለመተንበይ፣ የእርሱን ሚስጢር ዘልቆ መመርመር የሥጋና የደም ሥራ አይደለም፡፡ እርሱ የክብር መንግሥቱ መቼ እንደሚመጣ ያውቃል ይህንንም በራሱ ጊዜ እንዲፈጸም ያደርገዋል፡፡ (ሐዋ. 1፡7፤ ማቴ. 24፡36) "ነገር ግን የነገሩ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ" (ገላ. 4፡4) እርሱ የጸጋውን መንግሥት ለመጀመር ልጁን ይልካል፡፡

**ሦሥተኛው፡-** ለክርስቶስ ወንጌል ምሥክሮች ሁኑ በማለት ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ስለማይታወቀው ነገር ስለ ክብር መንግሥቱ መቼ እንደሚመጣ ከመገመት ወደ ታወቀውና ሊደረግ ወደሚገባው ነገር እንደገና መራቸው፡፡ የዳግም ምፃቱ ጊዜ አልተገለፀም፣ ነገር ግን ያንን የክብር ቀን እንድንጠብቅ እና እስከዚያ ድረስ ነግዱበት ተብለን ተጠርተናል፡፡ (ሉቃስ 19፡13፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የክርስቶስን ወንጌል "እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ" በመውሰድ ተግባር ድርሻ አለን ማለት ነው (ሐዋ. 1፡8) ይህ የእኛ ኃላፊነት ይሆናል በእኛ ጥንካሬ አይደለም ነገር ግን የሰሙትንና ያዩትን ሊመሰክሩ በተዘጋጁ ሁሉ ላይ እንደሚፈስ ቃል በተገባው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው፡፡ (ቁ. 4-8)

*እነኚህ ታማኝ የሆኑ የክርስቶስ ተከታዮች እስከ አሁን ድረስ ስለ ክርስቶስ ሥራ ያላስተዋሉት ነገር ነበራቸው፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ቢኖሩም እንኳ ጌታ እየጠቀመባቸው ነበር፡፡ እግዚአብሔር እንዲጠቀምብን ሁሉንም ነገር ማወቅ ወይም መረዳት የግድ አስፈላጊ ላለመሆኑ ምን ትምህርት ይሠጠናል?*

__________________________________________________________

__________________________________________________________





## ዓርብ ሰኔ 5 2007 ዓ.ም

**ለተጨማሪ ጥናት፡-** "ኢየሱስ በመንፈስ ደሃ የሆኑትን መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናት ይላል" ይህ መንግሥት የክርስቶስ ሰሚዎች የነበሩት ተስፋ እንደሚያደርጉት ምድራዊ ጊዜያዊ መንግሥት አይደለችም፡፡ ክርስቶስ እየከፈተ የነበረው መንግሥት የእርሱ መንፈስ የፍቅር የእርሱ ፀጋ እና የእርሱ የፅድቅ መንግሥት ነበር፡፡ የመሲሁ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማ የሚለየው የሰውን ልጅ በመምሰል ነው፡፡ የዚህም አባላት በመንፈስ ድሆች የሆኑ፣ ገሮች፣ ለጽድቅ የተሰደዱ ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የእነርሱ ናት፡፡ *Thoughts from the Mount of Blessing , p. 8.*

"እኛ አሁን በእግዚአብሔር የጥገና ህንፃ ውስጥ ነን፡፡ ብዙዎቻችን ድንጋዮች ከሚፈለጡበት ሥፍራ የወጣን ሸካራ ደንጊያዎች ነን፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር እውነት ላይ ስናርፍ የእርሱ ተፅዕኖ ይለውጠናል፡፡ እርሱ ከፍ ያደርገናል እያንዳንዱን ጉድለትና የኃጢአት ባህሪይ ያስወግዳል፡፡ ከዚያም ንጉሡን በውበቱና በክብሩ ልናየውና በመጨረሻም ንፁሓን ከሆኑ ሰማያዊ መላዕክት ጋር በክብር መንግሥቱ ለመሆን እንዘጋጃለን፡፡ ይህ ተግባር ለኛ የሚከናወነው በዚህ ነው፣ አካላችንና መንፈሳችን ለዘለዓለማዊነት ገጣሚ የሚሆነው እዚሁ ነው፡፡" *Ellen G. White , Testimonies for the Church, vol. 2, p.355,56.*

## የመወያያ ጥያቄዎች፡-

❶ *የፊዚክስ ተመራማሪ ስቴቨን ዌይበርግ፤ ስለ ዓለም ሲናገር እንዲህ ፅፏል፡፡" ዩኒቨርስ ለማስተዋል እየተቻለ በመጣ መጠን የበለጠ ፍሬ-ቢስ ሆኖ ይታያል፡፡ " የእርሱ ቃላት ከባድ ብጥብጥ ፈጥረዋል፡፡ እርሱም በተደጋጋሚ የተናገረውን ለማለሳለስ ጥረት አድርጓል፡፡ አንዳንዶች ዩኒቨርስ (ፈለክ) ፍሬ ነገር የለውም በሚለው ምንም የሚጋጭ ምክንያት አላገኙም፡፡ በዩኒቨርስ ፍሬ ያለው ነገር ምንድን ነው? በማለት የከዋክብት ተመራማሪው ሐርቨርድ ማርታ ጌለር ጥያቄ ጠይቋል፡፡ "ምን ፍሬ ነገር ይኖረዋል?" እርሱ ዝም ብሎ የቁስ አካል ሥርዓት ነው በዚህ ምን ፍሬ ይገኛል? በዚህ ዐ.ነገር እኔ ሁሌ ግራ እንደተጋባሁ ነኝ፡፡ ዩኒቨርስ ዝም ብሎ የሆነ ሥርዓት ፍሬ የሌለው ነገር ነው? የክርስቶስን ዳግም ምፃት እንደሚጠብቅና ሙሉና ፍጹም የሆነን የእግዚብሔረን መንግሥት መመሥረት ተስፋ እንደሚያደርግ ክርስቲያን ከዚህ ዐ.ነገር በስተጀርባ ባለው አስተሳሰብ ምን*

*ምላሽ አለዎት?*

❷ *እያንዳንዱ የክርስቲያን ትውልድ የክርስቶስን ዳግም ምፃት በዘመናቸው እንደሚሆን ጠብቀዋል፤ አንዳንድ ፓስተሮችና ወንጌላውያንም የጊዜ ቀመር አስቀምጠው ነበር፡፤ ነገር ግን እያንዳንዳቸው አልተሣካላቸውም፡፡ የጊዜ ቀመር በማስቀመጥ ያለው ችግር ምንድን ነው?*





# 12ኛ ትምህርት

ሰኔ 6-12 2007 ዓ.ም

# ኢየሱስ በኢየሩሳሌም

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት ትምህርት፡-** ሉቃስ 19፡28-40 ፤ ዘካ. 9፡9 ፤ ሉቃስ 19፡45-48 ፤ ማቴ. 21፡ 12-17 እና ሉቃስ 20፡9-26ን ያንብቡ፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "ሲቀርብም ከተማይቱን አይቶ አለቀሰላት" *(ሉቃስ 19፡41)*

የኢየሱስ የመጨረሻው ሳምንት በምድር የነበረው ህይወት በኢየሩሳሌም ግልጽ ሆኗል፡፡ ምን ዓይነት የተራበሸ ሳምንት ይሆን! በድል አድራጊነት መግባት፣ በግድየለሽነት ስለተቀመጠችው ከተማ ኢየሱስ ሲያለቅስ፣ የቤተመቅደሱ ማንፃት፣ እርሱን ለመያዝ የተደረገው ምጢራዊ ዱለታ፣ ልብን የሚነካው የመጨረሻው እራትና የጌተሰማኔው ጭንቀት፣ የሞት የሽረት ትግል ፌዘኛው የፍርድ ጉባኤ፣ ስቅላቱ እና በመጨረሻም ትንሣኤው ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ ዘመን በኋላ ይህንን የመሠለ ወሳኝ የሆነ ታሪካዊ ክስተት በፈለክ (ዩኒቨርስ) ውስጥ ሲካሄድ የነበረን በክፉና በመልካሙ መካከል ሲደረግ የነበረን ተጋድሎ ወደ ጡዘት ያመጣ ይህንን ደግሞ ሌላ ማንም ባያስተውለውም ግልፅ ሊሆን የነበረውን ነገር ምንነትና አስፈላጊነቱን ክርስቶስ አስተውሎት ነበር፡፡

ኢየሱስ በህይወቱ በተለያዩ ጊዜያት በኢየሩሳሌም ከተማ መካከል አልፎ ነበር፡፡ ማቴዎስ ማርቆስና ሉቃስ ኢየሱስ አዋቂ ሰው ሆኖ ኢየሩሳሌምን የጎበኘበትን ዘግበዋል፡፡ በብዛት

የዘገቡት የጭንቀቱን ሳምንት ነው፡፡ ምንም እንኳን ኢየሱስ  በኢየሩሳሌም የተገኘባቸው ጊዜያት የታወቁ ቢሆኑም ህፃኑ ኢየሱስ ወደ ቤተመቅደስ ተወስዷል (ሉቃስ 2፡ 22-28) በ12ዓመቱ በቤተ-መቅደስ ከካህናት ጋር ተከራክሯል (ሉቃስ 41-45) ፈታኙ ኢየሱስን ወደ ቤተ-መቅደስ ጫፍ ወስዶታል (ሉቃስ 4፡9-13) የኢየሱስ አገልግሎት የመጨረሻዎቹ ሳምንታት ግን የወንጌል ፀሐፊዎችን ትልቅ ትኩረት ስቧል፡፡

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለሰኔ 13 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

## እሁድ ሰኔ 7 2007 ዓ.ም

# በድል አድራጊነት መግባቱ

እርሱ በቤተ-ልሄም ተወለደ፡፡ በናዝሬት አደገ፡፡ በገሊላ በሰማሪያ በይሁዳ እንዲሁም በፔሪያ አስተማረ ሰበከ ፈወሰ፡፤ ነገር ግን አንዲት ከተማ የእርሱን የማያቋርጥ ትኩረቱን ያዘች ይህችም ኢየሩሳሌም ናት፡፡ "የሚወጣበትም ወራት በቀረበ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ፊቱን አቀና" (ሉቃስ 9፡51) የእርሱ ወደ ኢየሩሳሌም መግባት በዓለም ታሪክ ውስጥ በጣም ወሳኝና አስደናቂ ሳምንት ነበር፡፡ ይህም ሳምንት የጀመረው በኢየሱስ የንጉሥ ክብር ወደ ከተማዋ መግባት፣ ሞቱን በመስቀል ላይ በማየት ይህም ሞት "እኛ ጠላቶቹ ሳለን በልጁ ሞት የታረቅንበት" (ሮሜ 5፡10) ነው፡፡

*ሉቃስ 19፡28-40 ያንብቡ፡፡ የደቀ-መዛሙርቱን መደነቅ ያስተውሉ፡፡ በዚያን ጊዜ እነርሱ ያሰቡት ንጉሡ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም በምድራዊው የዳዊት ዙፋን ይቀመጣል ብለው ነበር፡፡ ከዚህ ታሪክ ትክክል ያልሆነን ነገር ተስፋ ስለማድረግ ምን ትምህርት እናገኛለን?*

________________________________________________________

________________________________________________________

ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ ሰዎች ከምሥራቅ በመምጣት ኃይለኛ ውስጥን የሚቀሰቅስ ጥያቄ ጠየቁ "የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው?" (ማቴ. 2፡2) አሁን ደግሞ ከመስቀሉ ጥቂት ቀናትን ቀደም ብሎ ደቀ-መዛሙርት እና ብዙ ህዝቦች ሆነው ኢየሱስ ንጉሥ እንዲሆን በሚቀሰቅስ ታላቅ ጩኸት የኢየሩሳሌምን ሰማዮች ሞልተው ነበር፡፡እነሆ በጌታ ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው፡፡ (ሉቃስ 19፡38)





ይህ አስደናቂ ትይንት የትንቢት መፈጸሚያ ነበር፡፡ "አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ እጅግ ደስ ይበልሽ አንቺም የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በይ እነሆ ንጉሥሽ ፃዲቅና አዳኝ ነው፤ ትሁትም ሆኖ በአህያ በአህያ ላይ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ሆኖ ወደ አንቺ ይመጣል፡፡" (ዘካ. 9፡9) ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ይህ ታሪካዊ የሆነውና በሆሳዕና ጩኸት የተጀመረው ጉዞ በአጭር ጊዜ "ተፈጸመ በሚል የአሸናፊነት ንግግር በጎልጎታ እንደሚቋጭ ያውቅ ነበር፡፡

ይሄ ሁሉ ነገር እየሆነ የነበረው ዘለዓለማዊ በሆነው የእግዚአብሔር ዕቅድ ቢሆንም ደቀ-መዛሙርቱ ግን በዘመናቸው በነበረው ባህል ትምህርትና ህዝቡ እንዲህ ይሆናል ብለው ተስፋ ባደረጉት ነገር ላይ ሀሳባቸው የተያዘ ነበር፡፡ እነርሱ በእርግጠኝነትና ሙሉ በሙሉ ቀድሞ የተሠጠውን ማስጠንቀቂያ የረሱና ትርጓሜውንም የሳቱ ነበሩ፡፡

*ክርስቶስ ነግሮአቸው ነበር እነርሱ ግን አልሰሙትም፡፡ ምናልባትም ሰምተውት እነርሱ ቀድመው ተስፋ ካደረጉት ነገር ጋር ስለተጋጨባቸው አልተቀበሉትም፡፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ስንመጣ እኛ ተመሳሳዩን ነገር አለማድረጋችንን እርግጠኛ የምንሆነው እንዴት ነው?*

________________________________________________________

________________________________________________________

## ሰኞ ሰኔ 8 2007 ዓ.ም

# በኢየሩሳሌም ቤተ-መቅደሱን ማንፃት

"እርሱም ቤቴ የፀሎት ቤት ይሆናል ተብሎ ተጽፏል እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው" (ሉቃስ 19፡46)

ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም ባለቀሰበት ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ያደረገው የመጀመሪያ ነገር ወደ መቅደሱ መሄድ ነበር፡፡

*ሉቃስ 19፡45-48 ፤ ማቴ. 21፡12-17 ፤ ማቴ 11፡15-19 ያንብቡ፡፡ ኢየሱስ ካደረገው ነገር ምን ጠቃሚ ትምህርት እናገኛለን? እንደ መቅደስ ለምንጠቅም ለእኛ በግልና እንደ ማህበረሰብ*

*አባልነታችን ይህ ታሪክ ምን እያለን ነው? ኤፌ 2፡21፡፡*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

አራቱ ወንጌላት ሁሉም ስለ ቤተ-መቅደሱ መንፃት ጠቅሰዋል፡፡ ዩሐንስ በ28 ዓ.ም ኢየሱስ መቅደሱን በጎበኘበት ወቅት ያደረገውን የመጀመሪያውን ማፅዳት ሲናገር ሌሎቹ ደግሞ በአገልግሎቱ መጨረሻ ወቅት በ31 ዓ.ም በፋሲካ ጊዜ ያደረገውን ሁለተኛውን ማንፃት ይተርካሉ፡፡ ስለዚህ ሁለቱም መቅደሱን የማፅዳት ተግባራት ኢየሱስ ስለ ቤተ-መቅደሱ ንፅህና  አገልግሎት ምን ያህል ግድ እንደሚለውና እርሱ የመሲህነቱን ተልዕኮ እንዴት ባለ ጥንካሬና ጥንቃቄ እንዲሁም ልዩ በሆነ ስልት ያከናውን እንደነበር ያስታውቃል፡፡

በቤተ-መቅደስ የነበረው ድርጊቱ በተለይም ከሞቱ በፊት የፈጸመው በጣም ደስ የሚል ጥያቄ የሚያስከትል ነበር፡፡ ኢየሱስ እርሱ በቶሎ የሚሞት መሆኑን የቤተ-መቅደሱም አገልግሎት በቶሎ የሚያበቃ እንደሆነ እያወቀ እነዚያን ቤተ-መቅደሱን የሚያረክሱትን አባረራቸው፡፡ *በተለይም አስፈላጊ አለመሆኑንና እንዲያውም ከትውልድ በኋላ እንደሚፈርስ እያወቀ ለምንድንነው እስከነ ቆሻሻው ዝም ብሎ ያልተወው?*

መልሱ ባይሰጠንም በእርግጠኝነት የእግዚአብሔር ቤት በመሆኑና እስከ አሁንም የድነት ዕቅድ የሚከናወንበት ሥፍራ በመሆኑ ይሆናል፡፡ አንድ ሰው ምናልባት በእርሱ ሞት አማካይነት ቤተ-መቅደሱና በእርሱ ውስጥ የሚደረጉት አስፈላጊ አገልግሎቶች ታማኝ ለሆኑ አይሁዶች ኢየሱስ ማን እንደነበር እንዲሁም በመስቀል ላይ መሞቱ ምን ማለት እንደሆነ እንዲያስተውሉ ረድቶአቸዋል ብሎ መከራከር ይችላል፡፡ የደህንነትን አጠቃላይ ዕቅድ በሙላት ማየት የሚቻለው ወደ ኢየሱስ ሲመጣ ነው፡፡ "ዓለም ሳይፈጠር የታረደው የእግዚአብሔር በግ" (ራዕይ 13፡8)

## ማክሰኞ  ሰኔ 9 2007 ዓ.ም

# ታማኝ ያልሆነው

የከፋው የወይን ጠባቂ ምሳሌ (ሉቃስ 20፡9-19) የመዋጀት ታሪክ ውስጥ ታላቅ ትምህርት ተሠጥቶናል፡፡ የዚህ ታሪክ ማዕከላዊ ነጥቡ እግዚአብሔርና እርሱ ለኃጢአተኞች





የሚያሳየው የማያቋርጥ ፍቅር ነው፡፡ እርሱ የተናገረው ምሳሌ በተለይ የሚጠቅሰው የአይሁድ መሪዎችን ቢሆንም "ካህናትና አለቆች ይህንን ምሳሌ በእነርሱ ላይ እንደ ተናገረ አውቀው" ነበር፡፡ ምሳሌው ግን ጊዜ የሚገድበው አልነበረም፡፡ ይህ ምሳሌ ለየትኛውም ትውልድ ለእያንዳንዱ የአማኝ ህብረት የእግዚአብሔር ፍቅርና መታመን ለፈሰሰለትና እግዚአብሔር የታማኝነት ምላሽ የሚጠብቅበትን እያንዳንዱን ሰው የሚመለከት ነው፡፡ እኛ የዛሬው ዘመን ተከራዮች ነን፤ በመሆኑም እግዚአብሔር ታሪክን ስመለከተው እኛም ከዚህ ታሪክ የምንወስደው መልዕክት አለ፡፡

*ሉቃስ 20፡9-19ን ያንብቡ፡፤ በምሳሌው እንደተጠቀሱ ሰዎች ተመሳሳይ ጥፋት ብንፈጽም በዚህ ሥፍራ የተገለጸው አስተምህሮ በእኛ ላይ ተግባራዊ የሚሆነው እንዴት ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

የእግዚአብሔር የወይኑ ቦታ ጭሰኞች ለእርሱ የፍቅርንና የእምነትን ምላሽ በመስጠት ፋንታ እግዚአብሔርን ረሱት እንዲሁም ቸላ አሉት፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔረር እንደ ወይኑ ሥፍራ ባለቤት አገልጋዮችን አከታትሎ ላከ (ቁ. 10-12)፡፡ ነቢያትን አንዱን ከሌላው እያከታተለ (ኤር. 35፡15) ህዝቡን ወደ መጋቢነት ኃላፊነታቸው በፍቅርና እንዲሁም ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሊያሸንፋቸው ሳያቋርጥ ሰርቷል፡፡ ሆኖም ግን እያንዳንዱ ነቢይ ተጠልቷል፡፡ "አባቶቻችሁ ያላሳደዱት ከነቢያት ማን ነው?" (ሐዋ. 7፡52)

የመለኮት ታሪክ ረዥም የሆነ የፍቅር ታሪክ ነው፡፡ መከራና ጭንቀት በየጊዜው ብቅ ብቅ ይላል ሆኖም ውሎ አድሮ ክብር ያሸንፋል፡፡ ትንሣኤ መስቀልን መከተል ያስፈልገዋል፡፡ ያኔ ተጥሎ የነበረው ድንጋይ ዛሬ የዳኑት ሁሉ ሀብታሙና ድኃው አይሁዳዊም አረማዊውም ወንድም ሴትም አንድ ሆነው የሚኖሩበት የእግዚአብሔር መቅደስ የማዕዘን ድንጋይ ሆኗል፡፡ እነርሱ በዘመን መጨረሻው የታሪክ ሂደት ውስጥ በወይኑ ሥፍራ ፍሬ በማፍራት ለዘላለም ፍሬውን ይበላሉ፡፡

*እኛ ዛሬ ምናልባት የምናሳድደው በህይወት ያለ ነቢይ ላይኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔርን መልዕክተኞች እምቢ በማለት እንደ ጥንቱ ሰዎች ነን፡፡ የወይኑን ፍሬ እንድናፈራ የተጠራን እኛ የእግዚአብሔርን መልዕክተኞች መልዕክት አለመቃወማችንን እርግጠኛ የምንሆነው እንዴት ነው?*

**ረቡዕ** ሰኔ 10 2007 ዓ.ም

# እግዚአብሔር የቄሳር ተቃራኒ

*ሉቃስ 20፡20-26 ያንብቡ፡፡ በየትኛውም ሀገር ብንኖር ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ ያስተማረውን ነገር ተግባራዊ ልናደርገው የምንችለው እንዴት ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

በኢየሱስ ዘመን የሮማውያን ቀረጥ ተለዋዋጭ ሁኔታ ነበረው፡፡ በ6ዓ.ም ከይሁዳ ምድር ከገሊላ የነበረው አብዮታዊ መሪ እንደተናገረው ለቄሳር ግብር መክፈል እግዚአብሔርን መክዳትና ከጠላት ጋር ማበር ነው ብሎ ነበር፡፡ ይህ ነገር መሲሁን የሚመለከቱ የተለያዩ ነገሮችን ከሚጠብቁና ከፍተኛ ምኞት ባላቸው ሰዎች ዘንድ በሮማውያን ላይ ተቃርኖ እንዲነሳ አድርጎ ነበር፡፡ ይህን የመሰለ የኋላ ታሪክ ባለበት ሁኔታ ግብር መክፈል በህግ የተፈቀደ ነው ወይስ አይደለም የሚለው የጠያቂዎቹን ሥውር ፍላጎት የገለፀ ነበር፤ አዎን የሚለው ምላሽ ንጉሥ እንዲሆን እየተጠባበቀ ለነበረው ህዝብ እና ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ታውጆ ለነበረው ንጉሥነት የሚያበቃው አይሆንም፡፡ አይደለም የሚል ምላሽ ደግሞ የሮማውያን አስተዳደር ትክክል ወይም ህግን የጣሰ ነው ከሚለው የገሊላውያን አስተሳሰብ ጋር የሚያመሳስለው በመሆኑ የተቃውሞውን ኃላፊነት እርሱ ላይ የሚጥል ይሆናል፡፡ በዚህም ኢየሱስን ማምለጥ በማይቻለው አጣብቂኝ ውስጥ መክተታቸው ነበር፡፡

ኢየሱስ ውስጣቸውን ተመለከተ በሳንቲሙ ላይ ያለውን የቄሳርን ምሥል አመልክቶ ፍርዱን ሠጠ፡፡ "እንኪያስ የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር አስረክቡ አላቸው"(ሉቃስ 20፡25)፡፡ በቄሳር ሥር ለሚኖሩ ምንዛሪውም የዕለት ጉዳዮች የሚውል እስከሆነ ይህ ለቄሳር ይገባዋል፡፡ ነገር ግን ሌላ ደግሞ የሚበልጥ ትዕዛዝ አለ ይህም መነሻውን የሚያገኘው እኛ የተፈጠርነው በእግዚአብሔር አምሳል በመሆኑ ያለንን ሁሉ ለእርሱ ልናስረክብ ይገባናል፡፡

የክርስቶስ መልስ ማድበስበሻ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ለጥያቄው ቅን ምላሽ ነበር እርሱም በሮማውያን አስተዳደር ሥር እስከኖሩ ድረስ የሚፈለግባቸውን ሁሉ ለማሟላት ፈቃደኛ ሊሆኑ እንደሚገባና ይህንን ማድረግ እግዚአብሔር ከሚፈልግባቸው ጋር የማይጋጭ





መሆኑን ገለፀላቸው፡፡ ነገር ግን ለአገሪቱ ህግ ተገዢ እንደሆኑ ቅድሚያውን በዘመናቸው ሁሉ ለእግዚአብሔር መስጠት ይገባቸዋል፡፡ *Ellen G, white The Desire of Ages, p602.*

*በየትኛውም ሀገር ብንኖር ጥሩ ዜጎች እንደሆንን እንዲሁ የእኛ ዜግነት "ሠሪው እግዚአብሔር የሆነ" ከተማ ዜጎች መሆናችንን በማወቅ ለሀገራችን ጥሩ ሆነን መቀጠል የምንችለው እንዴት ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ሐሙስ** ሰኔ 11 2007 ዓ.ም

# የጌታ ራት

*ሉቃስ 22፡13-20ን ያንብቡ፡፡ በፋሲካው ጊዜ የተከናወነው የጌታ ራት አስፈላጊነቱ ምንድነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ኢየሱስ የጌታን ራት የመሠረተው ታሪካዊ ከነበረው የፋሲካ ራት በተቃራኒ ነበር፡፡ የፋሲካው ግብዣ ከእግዚአብሔር ኃይል በተቃራኒ በሰው ድካም ላይ የሚያተኩር ነበር፡፡ እኛ ከኃጢአት ከሚመጣው መቀጮ ራሳችንን ነፃ ማውጣት እንደማንችል ሁሉ እሥራኤላውያንም ራሳቸውን ከግብፅ ባርነት ነፃ ማውጣት አልቻሉም ነበር፡፡ ነፃ መውጣት የእግዚአብሔር ፍቅርና ፀጋ እንዲሁም ነፃ ሥጦታ በመሆኑ እሥራኤላውያንን ለትውልድ ማስተማር የነበረባቸው ይህንን ነበር፡፡ ዘፀ. 12፡25-27 ልክ የእሥራኤላውያንን ነፃ መውጣት በታሪክ ከእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ጋር በጥብቅ የተሣሰረ እንደሆነ እንዲሁ የሰብዓዊ ዘር ከኃጢአት ነፃ መሆንም በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ክስተት ጋር መሠረቱ የተያያዘ ነው፡፡ በእርግጥ "ክርስቶስ ፋሲካችን ነው (1ቆሮ. 5፡7) እናም የእርሱ የመጨረሻው እራት የእርሱ ሞት አስፈላጊነት ወሳኝና ክቡር መሆኑን በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያውጅ ነበር፡፡" *G.C Berkouwer, The Sacraments (Grand Rapids; Wm. B Eerdmans,*

*1969), p. 193.*

የጌታ ራት እርሱን አሣልፈው በሰጡት ዕለት (1ቆሮ. 11፡23) ከስቅላቱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ኢየሱስ ለደቀ-መዛሙርቱ ሁሌም መርሳት የሌለባቸውን ማስታወሻ ሠጣቸው፡፡ ይህም ዳቦውና ወይኑ ስለ እነርሱ የሚሠበረው ሰውነቱና ኃጢአትን ለመደምሰስ ሊፈስ ያለው ደሙ ምሳሌ ነበር (ማቴ. 26፡ 28) ፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መሞት እግዚአብሔር እኛን ከኃጢአት ለመዳን የተጠቀመበት ዋነኛ መንገድ ነበር፡፡ የኢየሱስ ሞት ሰማይ እኛን ለማዳን የሠጠው ታላቅ ዋጋ መሆኑን እንዳንረሳ ለማድረግ ኢየሱስ የጌታን ራት ምሳሌ እርሱ ዳግም እስኪመጣ ድረስ እንድናከብረው አሳሰበ፡፡( 1ቆሮ. 11፡24-26)

ደሜ የሚፈሰው "ለብዙዎች የኃጢአት ይቅርታ ነው" ማቴ. 26፡28 የሚለው የኢየሱስ ማረጋገጫ እስከ ታሪክ ፍጻሜ ድረስ ሊታወስ የሚገባው ነው፡፡ ይህንን ማረጋገጫ የተሠጠበትን የደህንነት መንገድ ችላ ማለት እግዚአብሔርንና እርሱ ያዘጋጀውን የደህንነት መንገድ መካድ ነው፡፡

ከብዙዎች መካከል ሁለት ወሳኝ ትምህርቶች ጎልተው ይታያሉ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሞቷል የሚለው የመጀመሪያው ሊታሰብ የሚገባውና በእግዚአብሔር አጀንዳ ላይ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ሁለተኛው ትምህርት እኛን ሁላችንንም በእርሱ ሞት ምክንያት ወደ አንድ አምልኮ ሥር አምጥቶናል፡፡

በጠረጴዛ ዙሪያ ስንቀመጥ እንኳ በመጨረሻ ዘመን እንዳሉት የዳኑ ማህበረሰቦች ዳግም ምጻቱን እንደሚጠብቁት ሆነን እንቀመጣለን፡፡

*ለእርስዎ የዘላለም ህይወት ተስፋ ለመስጠት ክርስቶስ ሥጋውንና ደሙን ሠጠ፡፡ የማይቋረጥ ተስፋና መተማመኛ እንደሠጠዎት ሊያደርገው ይህንን አስደናቂ እውነት የራስዎ የግል ማድረግ የሚችሉት እንዴት ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________





## ዓርብ

ሰኔ 12 2007 ዓ.ም

**ለተጨማሪ ጥናት፡-** "የክርስቶስን ሥጋ መብላትና ደሙን መጠጣት እርሱን የግል አዳኝ አድርጎ መቀበል፣ እርሱ ኃጢአታችን ይቅር እንደሚል ማመን እናም እኛ በእርሱ ፍጹም መሆናችንን ማመን ነው፡፡ የእርሱን ፍቅር አጥብቆ በመያዝና በእርሱም በመኖር ከእርሱም በመጠጣት የእርሱ ባህሪይ ተካፋዮች እንሆናለን፡፡ ምግብ ለሥጋችን እንደሆነ ሁሉ ክርስቶስ ደግሞ ለነፍሳችን ነው፡፡ ምግብ በልተነው አካላችን ካልሆነ ምንም አይጠቅመንም፡፡ እንዲሁም ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን ካላወቅነው በቀር ዋጋ የለውም፡፡ የቃል ብቻ የሆነ ዕውቀት ለእኛ ምንም አይጠቅመንም፡፡ እርሱን መብላት አለብን፤ ወደ ልባችን ልናስገባው ይገባናል የእርሱም ህይወት የእኛ ህይወት ሊሆን ይገባዋል፡፡ ፍቅሩና ፀጋውን ልንዋሃደው ይገባል" *Ellen G. White , The Desiere of Ages, p.389.*

## የመወያያ ጥያቄዎች፡-

❶ *ኢየሱስ ቤተመቅደሱን ማንፃቱን ልብ ይበሉ፡፡ ታማኝነትንና እውነትን ለሽያጭ የምናቀርበው በምን መልኩ ነው? ከሁሉም የሚበልጥ አስፈላጊ የሆነው በዚህ አይነት ስህተት ውስጥ አለመውደቃችንን እንደ ቤተክርስቲያን ልናስተውል የምንችለው እንዴት ነው?*

❷ *እግዚአብሔር የለም ባዩ ጸሐፊ (Alex Rosenberg) ሁሉም ያለ ነገር የሚታይና እውን የሆነ ነገር ሁሉ ቁሳዊ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ያ ማለት ሁሉም ነገር ቁሳዊ በሆነ ሂደት በእርሱ ብቻ ሊገለጽ ይችላል ይገባልም፡፡ እነዚህም ሂደቶች ደግሞ ንድፍ፣ ግብና ዓላማ ወይም እግዚአብሔር የለሽ ናቸው፡፡ "የዩኒቨርስ ዓላማ ምንድን ነው?" ብሎ ይጠይቃል፡፡ "ምንም የለም፡፡ የትኛው ዓላማ ነው በዩኒቨርስ ውስጥ ሥራ ላይ ያለው ?" የዩኒቨርስ ትርጉም የለሽ መሆኑ እንዲሁም ዓላማ ቢስ መሆኑ ቢያስጨንቅህ ሮሰንበርግ ጭንቀትህን ትኩረት እንዳትሠጠው ያስጠነቅቅሃል፡፡ ለምን? ምክንያቱም ስሜቶቻችን ጭንቀትን ጨምሮ በሰውነታችን የሚገኙ ነርቮችና ኬሚካሎች ቅንብር እንጂ ሌላ ምንም አይደለም እና ታዲያ በዚህ ትኩረት የሚሠጠው ምኑ ላይ ነው? ነገር ግን*

*ሮሰንበርግ ለእነዚህ በህይወታቸው ትርጉም የለሽነት ተስፋ ለቆረጡት ሰዎች መልስ አለው፡፡ ምክንያቱም ጭንቀት ተራ የሆነ የነርቮች ሥርዓት መዛባት በመሆኑ ይህንን መድሃኒቶችን በመጠቀም ማስተካከል ይቻላል፡፡ በጧት ጥሩ ስሜት የማይሰማህ ከሆነ ለሦስት ሳምንታት ከተከታተልክ በኃላ ወደ ሌላው ህክምና ማለፍ ይቻላል፡፡*

❸ *ብዙውን ጊዜ የጭንቀት መድሃኒቶችን እንደ (Prozac, Wellbutrin , paxil, Zoloft, celexa or Luvox) የሚባሉት ከተወሰዱ ሶስት ሳምንት አይቆይም፡፡ አንዱ መድሃኒት አልሠራ ቢል ሌላው ይሠራል፡፡ ስለ እርሱ መልስ የሚገርመው ነገር ቢኖር ይህን የሚናገረው ከምሩ መሆኑ ነው፡፡ በአጭሩ ከተጨነቅህ መድሃኒት ወሰድ ነው፡፡ ይህንን የመሰለውን የኑሮ ዘይቤ ወይም አመለካከት እኛ ኢየሱስ ለእኛ በመስቀል ላይ ያደረገውን ከምናምነው ጋር ያነፃፅሩ፡፡ የእኛ በጌታ እራት መሣተፍ ዩኒቨርስ ትርጉም የለሽ ነው ለሚለው የሮበንሰን እግዚአብሔር የለም ባዩን ትምህርት ስህተትነት እምቢ ማለታችን መሆኑን የሚያሳየው እንዴት ነው?*





# 13ኛ ትምህርት

ሰኔ 13-19 2007 ዓ.ም

# የተሰቀለውና የተነሳው

## ሰንበት ከሰዓት

**ለዚህ ሳምንት ጥናት፡-** የሚከተሉት ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ ዘፍ. 3፡1-6፤ ሉቃስ 22፡39-46፤ 2ቆሮ. 13፡8 ፤ ሉቃስ 22፡53 ፤ ማቴ. 12፡30 ፤ 1ቆሮ. 15፡14፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "የሰው ልጅ በኃጢአተኞ እጅ አልፎሊሠጥና ሊሠቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ ነው፡፡" *(ሉቃስ 24፡7)*

ኢየሱስ ከህፃንነቱ ጀምሮ ወደዚህ ምድር የመጣው የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል (ሉቃስ 2፡41-50)፡፡ በፀናና በማያንገራግር መሰጠት አባቱን በመታዘዝ አስተምሯል ፈውሷል እንዲሁም አገልግሏል፡፡ የመጨረሻውን ራት አብረው ከበሉ በኋላ ለብቻው ለመጓዝ ከእግዚብሔር ጋር ለመስማማት፣ አልፎ ለመሰጠትና ሊካድ፣ ተፈርዶበት ሊሰቀል እና በሞት ላይ ድል ለማግኘት ጊዜው ደረሰ፡፡

በህይወቱ ዘመን ሁሉ ኢየሱስ መሰቀል የማይቀር መሆኑን አውቆታል፡፡ ብዙውን ጊዜ በወንጌል ውስጥ "ይገባዋል" የሚለው ቃል ከኢየሱስ መከራና ሞት ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ሲውል ይታያል (ሉቃስ 17፡25፤ 22፡37 ፤ 24፡7 ማቴ. 16፡21፤ ማር. 8፡31 ፤ 9፡12 ዩሐ. 3፡14) ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ አለበት፡፡ መከራ መቀበል አለበት፡፡ ተቃውሞ ሊደርስበት

ይገባል፡፡ ወደ ላይ ከፍ ከፍ እንዲል ይገባዋል፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ጎልጎታ እንዳይሄድ የሚያግደው ምንም ነገር አልነበረም፡፡ መስቀሉን የሚቃወም ማንኛውም ሀሳብ የሚመጣ በመሆኑ አልተስማማም፡፡ (ማቴ. 16፡ 22-23) ለእርሱ "መሄድ፣ መከራ መቀበል ፣መጓዝ ምርጫ አልነበረም ግድ ነበር" (ሉቃስ 24፡25፣ 26፣ 46) "የመለኮታዊ ሚስጢር ክፍል ነበር፡፡ በዘመናትና በትውልድ መካከል ተደብቆ የተቀመጠ ዛሬ ግን ለእግዚአብሔር ህዝብ የተገለጠው ነው፡፡" (ቆለ. 1፡26)

**የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለሰኔ 20 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

## እሁድ ሰኔ 14 2007 ዓ.ም

# ጌተ ሰማኔ አስፈሪው ትግል

እግዚአብሔር በታሪክ ንጋት አዳምንና ሔዋንን ፈጠረና ደስ ለሚያሰኝ ህይወት በሚያስፈልጋቸው ማንኛውም ነገር በተባረከች ገነት ውስጥ አስቀመጣቸው፡፡ ከዚያም በቶሎ አንድ ከተራ ነገሮች ያለፈ ሁኔታ ተከሰተ ያም ሰይጣን እዚያ ተገኘ (ዘፍ 3)፡፡ የመጀመሪያዎቹን ጥንዶች ፈተናቸው ከዚያም ይህችን ለጋ ምድር በክፉና በመልካም በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል በሚደረገው ታላቅ ተጋድሎ ውስጥ እንድትወድቅ አደረጋት፡፡

አሁን እግዚብሔር በራሱ ጊዜ ሌላኛው የአትክልት ሥፍራ (ሉቃስ 22፡39-46) በእውነትና በውሸት በጽድቅና በኃጢአት፣ እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ባዘጋጀው ዕቅድና ሰይጣን ሰዎችን ለማጥፋት ባስቀመጠው ግብ መካከል የሚደረገው ጦርነት ሜዳ ሆነ፡፡ በኤደን ገነት ዓለማችን ወደ ኃጢአት ጥፋት ተገፋች በጌተ ሰማኔ የዓለም ዋነኛው ድል ማረጋገጫ አገኘ፡፡ ኤደን ገነት ራስ ከእግዚአብሔር ሐሳብ በተቃራኒ መስማማት መከራ አሸነፋት ጌተ ሰማኔ ራስን ለእግዚአብሔር በማስረከብ ኃጢአት ላይ እንዴት ድል እንደሚገኝ አሣይቷል፡፡

*በኤደን የሆነውን (ዘፍ. 3፡1-6) በጌተ ሰማኔ ከሆነው (ሉቃስ 22፡39-44) ጋር ያወዳድሩ፡፡ በሁለቱም የአትክልት ሥፍራዎች በተከሰተው ነገር ያለው ትልቅ ልዩነት ምንድነው?*

________________________________________________

________________________________________________





ጌተሰ ማኔ ለሁለት ወሳኝ ጉዳዮች የቆመ ነው፡፡ አንደኛ፡- ሰይጣን የኢየሱስን ከእግዚአብሔር ተልዕኮ እና ዓላማ አቅጣጫ ለማስለወጥ ተንኮል በተሞላበት ሁኔታ መሞከሩ ሁለተኛ፡- የእግዚአብሔርን ፍቃድና ዓላማ ለማከናወን ጥሩና ፍጹም ምሳሌ የሚሆነውን በእግዚአብሔር ብርታት ላይ ሙሉ በሙሉ መደገፍን የሚያመለክት ነው፡፡ ጌተሰመኔ የሚያመለክተው ፈተናው ምንም ያህል ጠንካራ ቢሆንም ራሱ ምንም ያህል ደካማ ቢሆንም በፀሎት ብርታት ለሚያምኑ ድል ማድረግ ግድ እንደሆነ ነው፡፡ ኢየሱስ እጅግ ታዋቂ በሆነ መንገድ እንደፀለየ "ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ" (ሉቃስ 22፡42) ብሏል፡፡

ሰይጣንና ሠራዊቱ በሙሉ ከኢየሱስ ጋር ለመፋረድ ሲሠለፉ በጣም የሚወዳቸው ደቀ-መዛሙርት ስለ እርሱ መከራ ስሜታቸው የደነዘዙ ነበሩ፡፡ የደም ጠብታዎች አንድ በአንድ እየወረዱበት ነበር፡፡ አሣልፎ የሚሠጠው ሰው ሊስመው በእርምጃ ያህል ርቀት ላይ ነበር፡፡ ዘበኞችና የመቅደሱ ካህናት ዘለው ሊከመሩበት ተዘጋጅተው ነበር፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ፀሎትና ራስን ለእግዚአብሔር መሰጠት የህይወትን ታላቅ ሸክም ለመሸከም የሚያስችል ኃይል ሊሠጠን እንደሚችል አሣይቷል፡፡

*በሚቀጥለው ጊዜ አደገኛ በሆነ ሁኔታ ሲፈተኑ አዳምና ሄዋን በገነት ከነበራቸው በተቃራኒው ኢየሱስ በጌተሰመኔ የነበረውን ዓይነት ልምምድ ሊኖርዎት የሚችለው እንዴት ነው? በሁለቱ መካከል ከፍተኛ ልዩነት ሊያመጣ የሚችለው ወሳኝ ነገር ምንድን ነው?*

________________________________________________

________________________________________________

## ሰኞ ሰኔ 15 2007 ዓ.ም

# ይሁዳ

*"ሠይጣን ከአሥራ ሁለቱ አንዱ በሆነው በይሁዳ አስቆሮቱ ገባ" (ሉቃስ 22፡3)፡፡ ሰይጣን ሁሉንም ደቀ-መዛሙርት ለማግኘት ጥረት እንዳደረገ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ከሌሎቹ በተለየ መልኩ ጠላት በይሁዳ ህይወት ድል እንዲያደርግ የሆነው ምክንያት ምንድን ነው?*

________________________________________________

ሉቃስ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ከመምረጡ በፊት ብቻውን ሌሊቱን በሙሉ እንዴት ሲፀልይ እንደነበር ይነግረናል (ሉቃስ 6፡12-16)፡፡ ኢየሱስ 12 ደቀ-መዛሙርቱ የእግዚአብሔር ሥጦታ መሆናቸውን አምኗል (ዮሐ. 17፡6-9)፡፡ ይሁዳ በእውነት የፀሎት ምላሽ ነበር? በይሁዳ ክህደትና አሣልፎ በመስጠቱ እንኳ የእግዚአብሔር ዓላማ ሊፈጸም እንደነበር በዚህ *ሥፍራ* ያለውን ሁኔታ እንዴት እናስተውላለን? (2ቆሮ. 13፡8ን ያንብቡ)፡፡

በጣም ትልቅ *ሥራ* ለመ*ሥ*ራት የሚችል እምቅ ኃይል የነበረው ሌላውን ጳውሎስ ሊሆን የሚችለው ይሁዳ በዚህ ፋንታ ሙሉ በሙሉ ስህተት በሆነ ጎዳና ሄደ፡፡ *ለይሁዳ የኤደን ውድቀት የሆነበት የጌተሰማኔው ልምምድ ምን ዓይነት መሆን ይችል ነበር?*

"እርሱ የንፉግነትን ክፉ መንፈስ የህይወቱ መሪ እስኪሆን በውስጡ አበረታታ፡፡ ለኢየሱስ ያለውን ፍቅር የገንዘብ መወደድ አሸነፈው፡፡" *Ellen G. White , The Desire of Ages, P. 716.*

"ኢየሱስ በ2 ዓሣና በአምስት እንጀራ 5000 ህዝብ በመገበ ጊዜ (ሉቃስ 9፡10-17) የተደረገውን ተዓምራት ለፖለቲካ ጥቅም እንዲውል በማድረግ ኢየሱስን በግድ ንጉሥ መደረግ እንዳለበት በማሰብ የመጀመሪያውን እርምጃ የወሰደው ይሁዳ ነበር፡፡" ገጽ 718፣ 719፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ይህንን ሙከራ በመቃወሙ የይሁዳ መለየት በዚያ *ሥ*ፍራ ነበር የጀመረው፡፡ "ተስፋዎቹ እጅግ ከፍ ያሉ ነበሩ፡፡ የእርሱ ብስጭትና ቅሬታው መራራ ነበር" ገጽ 719፡፡ ይሁዳ በእርግጥ ኢየሱስ ይህንን ታላቅ የተዓምራት ኃይል ዓለማዊ መንግ*ሥ*ት ለመቋቋም መጠቀም እንዳለበት እንዲያምኑ ሌሎቹን ደቀመዛሙርት ተናግሯል፤ በግልፅ እንደሚታወቀውም በመንግ*ሥ*ቱ *ሥ*ልጣን እንዲኖረውም ፈልጓል፡፡ በጊዜያዊው መንግ*ሥ*ት *ሥ*ፍራ እንዲኖረው በውስጡ የተፈጠረው ምኞት ሲገለጥ እውን ከሆነው ዘላለማዊ መንግ*ሥ*ት ያለውን *ሥ*ፍራ እንዲያጣ ምክንያት መሆኑ ምን ያህል አሳዛኝ ነገር ነው፡፡

ሌላ ጊዜ ደግሞ ለኢየሱስ ራሷን የሠጠች ተከታይ እግሩን በውድ ሽቱ ስትቀባ ይሁዳ ይህን ድርጊት እንደ ብክነት ነበር የቆጠረው (ዮሐ. 12፡1-8)፡፡ ይሁዳ ማየት የሚችለው ነገር ብቻ ስለነበር የገንዘብ ፍቅሩ ለኢየሱስ ያለውን ፍቅሩን ጋርዶበት ነበር፡፡ ይሁዳ ከገንዘብና ከ*ሥ*ልጣን ጋር የነበረው ቁርኝት ዋጋው በማይተመነው የሰማይ *ሥ*ጦታ ላይ የዋጋ ማሳያ እንዲለጥፍ አደረገው (ማቴ. 26፡15)፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ "ሰይጣን በይሁዳ ገባ" (ሉቃስ 22፡3) ይሁዳም የጠፋ ነፍስ ሆነ፡፡





*በሥልጣንና በገንዘብ ምንም ችግር የለበትም፡፡ ችግሩ የሚመጣው እነዚህ ነገሮች የእግዚአብሔርን ፍቅር ሲጋርዱብን ነው፡፡ እንደ ይሁዳ ራሳችንን የማናታልል መሆናችንን ሁል ጊዜ እርግጠኛ መሆን በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?*

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ማክሰኞ** ሰኔ 16 2007 ዓ.ም

## በእርሱ ወገን ወይም በተቃራኒው

በታሪክ መስቀል ለሁሉም ታላቅ ልዩነት የሚፈጥር ነው፡፡ በእምነትና ባለማመን መካከል አሣልፎ በመስጠትና በመቀበል እንዲሁም በዘላለም ህይወትና በሞት መካከል ልዩነትን የሚፈጥር ነው፡፡ መስቀልን በተመለከተ ለማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር የመካከል *ሥ*ፍራ የለም፡፡ በመጨረሻ ሁላችንም ከሁለት በአንድ ወገን እንሆናለን፡፡ "ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል ከእኔ ጋርም የማያከማች ይበትናል" (ማቴ. 12፡30)፡፡ እነዚህ ትንሽ ምቾት የሚያሳጡን ቃላት ናቸው ነገር ግን ኢየሱስ ትክክል የሆነውን በክርስቶስና በሰይጣን መካከል ባለው ታላቅ ተጋድሎ ውስጥ ራሳቸውን ያስገቡት ሁሉ ላይ የሚሠራውን እየገለፀ ነው፡፡ እኛ ከኢየሱስ ጋር ወይም ከሠይጣን ጋር ነን፡፡ ጉዳዩ ይህን ያህል ጠንካራ ነው፡፡

*የሚከተሉት ሰዎች ከኢየሱስ ጋር ያላቸው ዝምድና እንዴት ነበር እና እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት እንዲረዳን ከእነርሱ ልናገኘው የምንችለው ምሳሌ ምንድን ነው? ይህንን ከመስቀሉ ጋር ልናዛምደው የምንችለው እንዴት ነው?*

*ፀሐፍት (ሉቃስ 22፡53) እነዚህ ሰዎች ያደረጉት ስህተት ምንድንነው? እነዚህን ሥህተቶች ለምን ፈጸሙ? እኛ ተመሳሳይ ስህተት እንዳንሰራ ልንጠነቀቅ የምንችለው እንዴት ነው?*

____________________________________________________________

*ጲላጦስ (ሉቃስ 23፡1-7 ፤ 13-25) ጲላጦስ በዚህ ሰው ምንም ጥፋት አላገኘሁበትም እንዲል ያደረገው ምንድንነው? (ዮሐ. 19፡4) በዚያው አፉ እንዲሠቀል የፈረደበት ለምንድን*

*ነው? ያወቀውን ትክክለኛ ነገር ማድረግ ካቃተው ከእርሱ ምን ትምህርት እንማራለን?*

________________________________________________________________

*ሔሮድስ (ሉቃስ 23፡6-12) የእርሱ ትልቁ ስህተት ምንድን ነው ከእርሱ ሞት ምን ትምህርት እንማራለን?*

________________________________________________________________

*ሁለቱ ሌቦች (ሉቃስ 23፡39-43) ሁለቱ ሌቦች መስቀሉን ሲመለከቱ የተለያዩ ምላሾችን ነበር የሠጡት ይህ ስሜት እኛ በታላቁ ተጋድሎ ውስጥ ደህንነትን በተመለከተ በአንድ ወይም በሌላ ወገን የምንሆን መሆናችንን የሚያመለክተው እንዴት ነው?*

________________________________________________________________

**ረቡዕ** ሰኔ 17 2007 ዓ.ም

# እርሱ ተነስቷል

እሁድ ቀን ጧት ሴቶች አንድን ዓላማ ይዘው የቀብር ሥነ-ሥርዓት ልማድ ለመፈጸም ወደ መቃብር ሄዱ፡፡ ምንም እንኳን ከኢየሱስ ጋር አብረው ጊዜ ያሳለፉ ቢሆንም ሊሆን የተገባውን ነገር ግን አልተረዱትም ነበር፡፡ እነርሱ ባዶ መቃብር ለማየት ወይም በሰማያዊ መልዕክተኛ "እርሱ ከዚህ የለም ነገር ግን ተነስቷል" የሚለውን መልዕክት ለመስማት ዝግጁ አልነበሩም፡፡

*በሐዋሪያት መጽሐፍ ብቻ በመጀመሪያዎቹ ምዕራፋት ስለ ትንሳኤው ወደ 8 የሚሆኑ ማጣቀሻዎችን እናገኛለን፡፡ ሐዋ. 1፡22 ፤ 2፡14-36 ፤ 3፡14-15 ፤ 4፡1-2 ፤ 10 12 33 ፤ 5፡ 30-32. የኢየሱስ ትንሣኤ በቀደምቷ የሐዋሪያት ቤተክርስቲያን እምነትና ስብከት ውስጥ በጣም አስፈላጊ የነበረው ለምንድንነው? ዛሬ ለእኛስ ወሳኝ የሚሆነው ለምንድነው?*

________________________________________________________________

________________________________________________________________





ሴቶቹ ለኢየሱስ ትንሣኤ የመጀመሪያዎቹ የዓይን ምሥክሮች ነበሩ፡፡ እነርሱ ይህንን እውነት ለሌሎች ለማድረስ ፈጠኑ፣ ነገር ግን ማንም አላመናቸውም (ሉቃስ 24፡11) በምትኩ ሐዋሪያት ታላቁን የደህንነት ታሪክ እንደ" ተራ ተረት" ወዲያ ጣሉት፡"፡ (ቁ. 10፡11)

በምን ያህል አጭር ጊዜ ስህተት እንደነበሩ ተረዱ! የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ለክርስትና እምነት መኖር አጠቃላይ ማንነቱና የእግዚአብሔር የደህንነት ተግባር መሠረቱ ነው፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህንን ግልፅ ያደርገዋል፡፡ "ክርስቶስ ከሙታን ካልተነሣ የእኛ ስብከትና የእናንተም እምነት ከንቱ ነው" (1 ቆሮ 15፡14) የእኛ የሆነውን ተስፋ የምናገኘው በኢየሱስ ትንሣኤ ብቻ በመሆኑ ከንቱ ይሆናል፡፡ ያ ተስፋ ከሌለን ህይወታችን በዚሁ ለዘላለም ያበቃል፡፡ የክርስቶስ ህይወት በመቃብር አላበቃም ስለዚህ ታላቁ ተስፋችንም የእኛም ህይወት በዚህ አያበቃም፡፡

"ክርስቶስ ከሙታን ባይነሳ ኖሮ እጅግ ረዥም የሆነው እግዚአብሔር ሰውን ለመዋጀት የፈጸመው ተግባር በሙሉ በቀጥታ በመቃብር ውስጥ ይቀር ነበር፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መነሳት እውነት ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔር ህያው ስለመሆኑ ማረጋገጫ ባላገኘን፣ ሞትም የመጨረሻ ቃል በሆነ ነበር፡፡ እምነት ራሱን የህይወት ጌታ ሆኖ ነጻ አውጪነቱን ካላሳየ ዝም ብሎ ድካም ይሆናል፡፡ የእግዚአብር ከፍተኛው የማንነቱ መገለጫ የሆነው እግዚአብሔር በኢየሱስ የሚለው የክርስቲያን እምነት በመቃብር የታሠረ በሆነ ነበር በእርግጥ ኢየሱስ ሞቶ ቢቀር ኖሮ፡፡" *Geolge Eldon Ladd, ATheology of New Testament 1974 , p. 318.*

**ሐሙስ** ሰኔ 18 2007 ዓ.ም

# "ሁሉም ነገር ሊፈጸም ይገባዋል"

*ሉቃስ 24፡13-49ን ያንብቡ፡፡ የኢየሱስን ትንሣኤ ተከትለው የተደረጉ ነገሮችን ያመለክታሉ፡፡ በተለያዩ ሁኔታዎች ኢየሱስ ምን ደርሶበት እንደ ነበር ለሰዎቹ ለማስረዳት የጠቀሳቸው ነገሮች ዛሬም ድረስ እና ለዓለም ምሥክር እንዲሆን ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ለምንድንነው?*

________________________________________________________________

የኢየሱስ ትንሣኤ ለመሲህነቱ በቂ ማስረጃ መሆን በቻለ ነበር፡፡ ከመስቀሉ በፊት የተደበደበው እና የተጨከነበት እንዲሁም ጎኑ የተወጋው ኢየሱስ በመጨረሻም በጨርቅ ተጠቅልሎ በመቃብር ተደረገ፡፡ አንዳንዶች በሚያስቅ ሁኔታ አስተያየቶቻቸውን ሲሠጡ እርሱ መስቀሉን እና ጭካኔውን፣ መድማቱንም፣ በአደጋው እጅግ መጎሳቆሉን እና ድካሙን መቋቋሙ እንዲሁም ኢየሱስ ከመቃብሩ መውጣቱ የማንም ሐሳብ ሳይሆን የመሲሁ አሸናፊነት ነው፡፡

የሆነ ሆኖ ኢየሱስ ጥቂት ማይሎችን ከኤማሁስ መንገደኞች ጋር አብሮ ለመጓዝ በቂ ጥንካሬና ህይወት ነበረው፡፡ ራሱን ከመግለጹ በፊት ኢየሱስ ጠንካራ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የእምነት መሠረት እንዲኖራቸው ለማድረግ ጥቆማ እየሠጣቸው ነበር፡፡

ከዚያም ለደቀመዝሙርቱ በተገለጠ ጊዜ ሥጋውን አሣያቸው፣ እናም ከእነርሱ ጋር በላ፣ እናም ከዚህ የበለጠ ወደ እግዚአብሔር ቃል አመለከታቸው "እንዲህም አላቸው ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሳል በስሙም ንሥሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለአህዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ ተጽፏል፡፡ እናንተም ለዚህ ምሥክሮች ናችሁ፡፡"(ሉቃስ 24፡ 46-48)

በዚህ ሥፍራ በተጨማሪ ኢየሱስ ወደ ቅዱሳት መጻህፍት መጠቆም ብቻ ሳይሆን በመካከላቸው ህያው ሆኖ ከመገኘቱ ማስረጃ በተጨማሪ ነገር ግን በትክክል በእርሱ ላይ የተፈጸመው ምን እንደሆነ እንዲያስተውሉ ለማድረግ ቅዱሳት መጻህፍትን ተጠቀመ፡፡ ደግሞም ትንሣኤውን በቀጥታ የወንጌልን መልዕክት ለዓለም ሁሉ ከመሰበክ ተልዕኮ ጋር በቀጥታ አገናኝቶታል፡፡

*ስለዚህ ኢየሱስ ምንም እንኳን በጣም ኃይለኛ የሆኑ የእርሱን ማንነት ሊያሣዩ የሚችሉ ማስረጃዎች ቢኖሩም እርሱ ደቀ-መዛሙርቱን ወደ እግዚአብሔር ቃል ይጠቁማቸው ነበር፡፡ በአጠቃላይ ዛሬ በእኛ መካከል የእግዚአብሔር ቃል ሣይኖር ወንጌልን ለዓለም የመስበክ ጥሪና ተልዕኮ ያለን መሆናችንን እንዴት እናውቃለን? እንዲያውም ወንጌል ምን እንደነበረ በምን እናውቃለን? ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ለደቀ-መዛሙርቱ ዋናና ማዕከላዊ እንደነበረ ለእኛም እንዲሁ ነው፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ምን ያህል ጊዜ ያሳልፋሉ? የሚያደርጉትን ነገር የሚመርጡትን ምርጫ እና ሌሎች ከሚሠጡት አገልግሎት ላይ ምን ተፅዕኖ ያሳድርብዎታል?*

---





## ዓርብ ሰኔ 19 2007 ዓ.ም

**<u>ለተጨማሪ ጥናት</u>፡-** "የኢየሱስ ሞት አስፈላጊነት በቅዱሳንና በመላዕክት የሚታይ ነው፡፡

አለም ሳይፈጠር በታረደው በግ አማካይነት ካልሆነ የወደቀው ሰብዓዊ ዘር በእግዚአብሔር ገነት ሥፍራ ሊኖረው አይችልም፡፡ ታዲያ የኢየሱስን መስቀል ከፍ ከፍ ልናደርገው አይገባንምን? የሰማይ መላዕክት ለኢየሱስ ክብርን እየሠጡ እነርሱ እንኳን የእግዚአብሔረርን ልጅ መከራ በማየት ካልሆነ በቀር ነፃነት አይሠማቸውም፡፡ የሰማይ መላዕክት እንኳን ከክህደት የሚከላከሉት በመስቀሉ ብቃት ነው፡፡ ያለ መስቀሉ እነርሱም ከሰይጣን ውድቀት በፊት እንደነበሩቱ መላዕክት እንዳይወድቁ የሚከላከላቸው ነገር የለም፡፡ የመላዕክት ፍጽምና በሰማይ ውድቀት አግኝቶታል፡፡ የሰው ፍጽምና በኤደን ተድላና ደስታ ሥፍራ ወድቋል፡፡ደህንነትን የሚፈልግ ሁሉ በሰማይና በምድር ወደ እግዚአብሔር በግ ይመልከት፡፡" *Ellen G. White, The SOA Bible Commentary , Vol. 5 , p.1132.*

## የመወያያ ጥያቄዎች፡-

❶ *እንደ ክርስቲያን በእምነት ልንኖር ይገባናል፤ ያ ማለት ደግሞ በእርግጠኝነት ሙሉ በሙሉ ማረጋገጫ ባይኖረንም ልናምን ይገባናል፤ እንዲሁም ቀጥተኛ የዓይን ምሥክር ማስረጃ ባይኖረንም ጭምር ማለት ነው፡፡ በእርግጥ ሰዎች በብዙ ነገሮች እንዲህ ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ እንደ ሳይንስ ግንዛቤ አንድ ደራሲ እንዲህ ጽፏል፡፡ "በአጠቃላይ ከምናምናቸው ነገሮች እጅግ ጥቂት ለሆኑ ነገሮች ብቻ ቀጥተኛ ማስረጃ እናገኛለን ብሏል " Richard Dewilt world views; An Introduction to the history and philosophy of since.*

የሆነ ሆኖ እኛ ስለምናምናቸው ነገሮች እጅግ ብዙ የሆኑ ምክንያቶች ይኖሩናል፡፡ ለምሳሌ በታላቁ የወንጌል ተልዕኮ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ያለውን ይዩት፤"ምሥክር ይሆን ዘንድ የዚህ መንግሥት ወንጌል ለዓለም ሁሉ ይሰበካል ከዚያም መጨረሻ ይሆናል" (ማቴ 24፡14) ኢየሱስ እነዚህን ቃላት የተናገረበትን ጊዜ ያስተውሉ፡፡ እርሱን የሚከተሉ ሰዎች ብዛታቸው እንዴት ነው?ምን ያህል

ሰዎች አመኑት ወይም እርሱ ማን እንደሆነና ምን ሊያከናውን እንደመጣስ የተረዱት ስንቶች ናቸው? የቀደምት ቤተክርስቲያን በሮማ ግዛት ሥር ለብዙ መቶ ዓመታት የገጠማትን ችግር ይዩ፡፡ እነዚህን ሁሉ እውነታዎች በአእምሮ በማስቀመጥ ኢየሱስ ስለተናገረው ወሳኝ የሆነ ትንቢት እኛ በእርሱ ቃል እንዴት ማመን እንደሚገባን ተወያዩበት፡፡

❷ *ከዚህ በላይ ባለው የኤለን ጂ. ኋይት ንባብ ላይ ያተኩሩ፡፡ ይህ የኃጢአት ጉዳዮች አለም አቀፋዊ መሆናቸውን እንድንረዳ እንዴት ያግዘናል? መላዕክት እንኳን ኢየሱስን በማየት ካልሆነ እነርሱም ነፃ አይደሉም፡፡ ይህ ማለት ምን ማለት ነው?*





# አለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬድዮ አገልግሎት

| ቋንቋ | ሰዓት | አየር ሞገድ | | አድራሻ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | khz | ሜ.ባንድ | ስልክ | ፖ.ሳ.ቁ. |
| ትግርኛ | ጠዋት 12፡00-12፡30 | 7315 | 41 | +251115511199- የውስጥ መስመር 205 ወይም +251910145105 | 145 አዲስ አበባ |
| | ማታ 1፡30 -1፡57 | 11850 | 25 | | |
| ኦሮምኛ | ጠዋት 12፡00-12፡30 | 15500 | 19 | +251115511199- የውስጥ መስመር 237 ወይም +251921600938 | |
| | ማታ 2፡30-3፡00 | 15155 | 19 | | |
| አማርኛ | ጠዋት 12፡30-1፡00 | 15500 | 19 | +251115511199- የውስጥ መስመር 242 ወይም +251911137222 | |
| | ማታ 2፡00-2፡30 | 9490 | 31 | | |

የተላለፉ ፕሮግራሞችን እንደገና ለማድመጥ ከመረጃ መረባችን www.awr.org ላይ በመግባት እንደገና ማድመጥ ይችላሉ፡፡

የአለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬድዮ የ24 ሰዓት የአማርኛ ቋንቋ ስርጭትን በክርስቲያን ቻናል ጣቢያ ውስጥ ከዚህ በታች በተቀመጠው መሰረት ያገኙታል፡፡

HC The Voice Of Hope
Frequency: 12575
Symbol Rate: 09698
Polarity : Horizontal or Auto
Satellite : Pas 7/10
LNB: KU BAND

**ለበለጠ መረጃ ባለሞያ ያነጋግሩ. . .**

የአለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬድዮ፤ የተስፋን ድምጽ ያድምጡ፡፡ ለወዳጆችዎ በማስተዋወቅና በመጋበዝ የበረከቱ ተካፋይም ይሁኑ፡፡

## የትንቢት መንፈስ መጻሕፍትን ተርጉሞና አሳትሞ ማሰራጨት ለሚፈልጉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የተሠጠ

# <u>ማሳሰቢያ</u>

*የትንቢት መንፈስ (Spirit of Prophecy - SOP) መጻሕፍት በሙሉ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ንብረት ናቸው፡፡*

*እነዚህን ጽሁፎች በከፊልም ሆነ በሙሉ ወደ አማርኛም ሆነ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ቋንቋዎች በማስተርጎምና በማሳተም ለማዳረስ የሚፈልግ ግለስብም ሆነ ድርጅት፣ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ለኢትዮጵያ ዩኒየን ሚሽን የጽሁፍ ክፍል ጥያቄውን በጽሑፍ በማቅረብና በአካልም ቀርቦ በመወያየት ወደ ሰምምነት ከተደረሰ በኋላ ትርጉሙ፣ ህትመቱና ስርጭቱ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተከናውኖ ሥራውን መፈፀም ይቻላል፡፡*

*በዚሁ መሠረት የትንቢት መንፈስ ጽሁፎችን በማሳተም ወንጌልን ለማዳረስ የሚጥሩ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች በእጅጉ ይበረታታሉ፡፡*

*ሆኖም ግን ይህንን በመተላለፍ ያለ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ በቤተክርስቲያኗ ስም የትንቢት መንፈስ ጽሁፎችን አሳትሞ ማስራጨት፣ በአገሪቱም ሆነ በዓለም ዓቀፍ የሥነ ጽሁፍ ህግ ያስጠይቃል፡፡ በተጨማሪም ድርጅቱ እያስተረጎመ ያለውን መጽሐፍ ሌላ አካል ተመሳሳዩን መጽሐፍ በመተርጎም ላልተፈለገ የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ወጪም ይዳርጋል፡፡*

*ሰለሆነም የቤተክርስቲያኗ ህግና መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ሁላችንም ጽሁፎችን በማሳተምም ሆነ በማሰራጨት የሶስቱን መላዕክት መልዕክት ለማዳረስ እንድንችል ጌታ ይርዳን፡፡*

***ድርጅቱ***

## Namoota dhuunfaadhaanis ta'e Jaarmiyaa (Dhaabbataan) Caaffatoota Raagaa (Hafuura Raajii) Hiikuu fi Maxxansuu; Akkasumas Raabsuu barbaadan hundaaf-

# <u>YAADACHIISA!</u>

Caaffanni Hafuura Raajii *(Spirit Of Prophecy-SOP)* qabeenya dhaabbataa Waldaa Adiveentistii Guyyaa 7[ffaa] Addunyaawaati.

Kanaafu, kitaabota kana guutummaa isaas ta'e gartokkeeisaa, namni dhuunfaas ta'e dhaabbantni gara Afaan biyyattii keessatti dubbatamu kamiitti iyyuu hiikee maxxansuu fi raabsuu yoo barbaade hojii isaa utuu hin eegalin dursee qaamaanis ta'e barreeffamaan Waajjira Olaanaa Mana Maxxansaa Yuuniyen Miishinii Itiyoophiyaa ayyamsiisuudhaan erga waliigaltee irra ga'ee booda hojii isaa itti fufuu ni danda'a

Haala kanaan , dhaabbatnis ta'e namni dhuunfaan kitaabota raagaa (Hafuura Raajii) kana maxxansee wangeela biyya lafaatiin ga'uu kan barbaadu hunduu ni jajjabeeffama.

Haata'u malee garuu; ayyama Waldaa Adveentistii Guyyaa 7[ffaa] Addunyaawaatiin ala maqaa waldattiitiin caaffata Hafuura Raajii kana maxxansiisanii raabsuun akka seera biyyattiittis ta'e akka mirga maxxansaa addunyaatti kan itti nama gaafachiisu ta'uu isaa ibsaa, itti dabalee immoo kitaaba dhaabbatni kun hiiksisaa jiru qaamni biraan immoo hiikee dubbistootaaf dhiyeessuun qisaasama dinagdee, humnaa fi yeroo hordofsiisa.

Sababa kanaaf, hundumti keenya iyyuu akkaataa Seeraa fi Danbii ittiin Bulmaata Waldattiitiin barreeffamoota keenya maxxansiisuudhaanis ta'e raabsuudhaan Ergaa Ergamoota Sadanii ariifachiisuu akka dandeenyuuf Gooftaan nu haagargaaru.

*DHAABBATICHA IRRAA!!!*